


## በፍትሕ ጋዜጣ ላይ ለምንጽፍ ሁሉ እየተናገሩ አለማነጋገር፣ እያሰቡ አለማሳሰብ

ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም 3



## ስለነፃነት ባህል ለመናገር ምክንያት የሆነን መፅሐፍ

በብርሀኑ ደቦጭ (የታሪክ ተመራማሪ) 7

## ለ/ወሮ አዜብ መስፍን ...ያንን ነገር እንዴት አደረጉልኝ?

አቤ ቶኪቻው 13






ቅፅ 5 ቁጥር 186 አርብ ሚያዝያ 26 2004 ዓ.ም | www.fetehe.com Addis Ababa-Ethiopia | ዋጋ 7.00 ብር

# ጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ <<የመለስ አምልኮ>> የሚል መጽሐፍ አሳተመ

*የ4 ወር እስር ወይም 2000 ብርም ተፈረደበታል*

-ክንፈሚካኤል ደበበ (አበበ ቀስቶ) የ8 ወር እስራት ተፈረደበት 11

# ኮሎኔል መንግስቱ ኃ/ማርያም እየመጣ ነው?



4

# በመህል ፒያሳ ራሱን ያቃጠለው ግለሰብ ሕይወቱ አለፈ 15

## የእስክንድር ነጋን ሽልማት ባለቤቱ ሠርካለም ፋሲል በኒውዮርክ ተገኝታ ተቀበለች 15

## ፕሮፌሰር ገብሩ ታረቀ ከኃላፊነታቸው ተነሱ 15

## ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ስለኢትዮጵያ ፖለቲካ ለማስተማር ወደ ጀርመን አቀኑ 15



## አጋር ያጣ ህዝብ

አቶ አስገደ ገ/ስላሴ (የቀድሞ የህወሓት መስራች) ከመቀሌ 12

## የጠቅላይ ሚኒስትሩ የልማት ሰራዊት የሀገሪቱን አንጡራ ሃብት ሲያባክን

ከኢንጂነር ዓብደልወሃብ ቡሽራ መቀሌ 12



## ከሁመራ ከ50 በላይ ሰዎች በድጋሚ ታፍነው ተወሰዱ

-አንድ ሰው ሞቷል 15

## ‹‹የኦሮሚያ ፍ/ቤቶች ከተፅዕኖ ሙሉ በሙሉ ነፃ ናቸው ማለት አይቻልም››

/የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት አቶ ታደለ ነጊሾ/ 15

## ከጉራፈርዳ የተባረሩት 47 አባወራዎች ወደ ደብረብርሃን ተጓዙ 15

## በኦሮሚያ መንጃ ፍቃዱ የሚያሽከረክሩ ፍቃዳችንን ተነጠቀ አሉ 15

## ‹‹ሠማያዊ›› ፓርቲ ህጋዊ መሆኑን ይፋ አደረገ 15

# ኦጋዴን - የኢትዮጵያው ዳርፉር?



ኃይለመስቀል በሸዋምየለህ

ልክ የዛሬ አምስት ዓመት ግድም በቀደመው ዓመት በሽብርተኝነት የተፈረጀው የኦጋዴን ነፃ አውጪ ግንባር /ኦብነግ/ በነዳጅ ቁፋሮው ላይ የተሰማሩትን 65 ኢትዮጵያውያንን እና 9 ቻይናውያንን በድቅድቅ ጨለማ በተኙበት ጨፈጨፋቸው። ይህን መራር ዜና ተከትሎ አለም አቀፍ ሚዲያዎች አንዳች ከባድ ነገር በምስራቁ የኢትዮጵያ ክፍል እየተካሄደ ስለመሆኑ መናገር ጀመሩ። በዚህ ዜና ምሪት ክልሉን ለመፈተሽ የኒውየርክ ታይምስ ጋዜጠኛ ጄፍሪ ጄትል ማን ወደ ኢትዮጵያ ገባ። ወደ ኡጋዴን ክልል በማምራት ጥቃቱን ፈፅሟል የተባለውን ታጣቂ ቡድን ጨምሮ የኢትዮጵያ መንግስት በክልሉ ፈፅሞታል ስለሚባለው የሰብዓዊ መብት ጥሰት ለማረጋገጥ የተለያዩ ነዋሪዎችን ለማወያየት ሲሞክር ነገሩ ያላማረው የኢትዮጵያ መንግስት በቁጥጥር ስር አዋለው። እርሱን ጨምሮ አብረውት የተጓዙት የፎቶግራፍ እና የቪዲዮ ባለሙያዎች ከአምስት ቀናት እስር በኋላ ለጉዞው ይዘዋቸው የነበሩት ቁሳቁሶችን ሁሉ ተቀምተው ወደ ሀገራቸው እንዲመለሱ ተደረገ። ይህ በሆነ በወሩ ‹‹ራሱን ለአደጋ በማጋለጥ በችጋር እና በጦርነት በሚናጠው በአፍሪካ ቀንድ ተዟዙሮ ለሰራቸው ዘገባዎች›› የታዋቂውን የቹልተዘር ሽልማት ከጥቂት ቀናት በፊት የተሸለመው ጄትልማን “In Ethiopia desert, fear and cries of Army Brutality” በሚል ርዕስ በሱማሊያ ክልል ተፈፅመዋል የሚባሉትን አስገድዶ መደፈሮች፣ ድብቅ ግድያዎችን እና ጥልቅ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን ያካተተ ፊቸር በኒዮዮርክ ታይምስ ላይ አሳተመ። ይህን ዘገባ መታገስ ያልቻለው የኢትዮጵያ መንግስት ከሌላው ጊዜ በተለየ ቁጣውን በቀድሞው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ስዩም መስፍን አማካኝነት ገልጿል። አቶ ስዩም ዘገባው በወጣ በተከታዩ ቀን መንግስታቸው በሀገር ውስጥ እንዳይነበብ በከለከለው ኢትዮ-ሚዲያ በተባለው ድረ-ገፅ ላይ ባወጡት ፅሁፍ ጋዜጠኛው ሰሜን ኢትዮጵያን ለመጎብኘት በሚል በቱሪስት ቪዛ ወደ ሀገር ውስጥ እንደገባ በመግለፅ፤ እርሳቸው ‹‹ደመ ቀዝቃዛ ነፍሰ ገዳዮች›› ካሏቸው የኦብነግ ታጣቂዎች ጋር ለመወያየት ሲሞክር በመያዙ ተቆጥቶ የሀገሪቱን መልካም ገፅታ ለማበላሸት የተጋበት ፅሁፍ መሆኑን ተናገሩ። በክልሉ ያለውን አንድ ዩኒቨርስቲ በመጥቀስ ጄትልማን አፍሪካን በቅኝ ከገዙት ቀደምቶቹ የተሻለ ዕይታ እንደሌለው በመናገር ዘገባው ከቀሰቀሰው ቁጣ መንግስታቸውን ተከላክለዋል። የአቶ ስዩም መከራከሪያ ይህን ቢመስልም እርሳቸው ይህን ባሉ በወሩ በክልሉ ለአስራ ሁለት ዓመታት ሰብዓዊ ግልጋሎት ሲሰጥ የከረመው የአለም አቀፉ ቀይ መስቀል ማህበር ከሽብርተኛው ኦብነግ ጋር ተባብራችኋል በሚል ክስ በሰባት ቀናት ውስጥ ክልሉን ለቆ እንዲወጣ በኢትዮጵያ መንግስት ተወስኗል።ከሶስት ሳምንታት በፊትም የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የደህንነት ሰራተኛ የሽብርተኝነት ክስ ተመስርቶባቸዋል። አሁን የኡጋዴን ክልል ለተቋማትም ሆነ ለአገር ውስጥ እና የውጪ ጋዜጠኞች የማይደፈር ሆኗል።

### ሁለቱ ጫፎች

በሱማሊያ ክልል ያለው ነባራዊ ሁኔታ ይህን መልክ መያዙ የበለጠ አስቸጋሪ ያደረገው ለመዘገብ ለሚሹ ጋዜጠኞች ብቻ ሳይሆን የክልሉን የፖለቲክ-ማህበራዊንም ሆነ ኢኮኖሚያዊ አውዶች ለማጥናት ለሚፈልጉ ምሁራን ጭምር ነው። በከፊልም ቢሆን ይህን የክልሉን ወታደራዊ አጥር ተሻግረው የኡጋዴንን ፖለቲካ በማጥናት ቀዳሚ የሆኑት ስዊዘር ላንዳዊው ቶብያስ ሃግማን ናቸው። ዶ/ር ሃግማን ከጅጅጋ እስከ ቆላፎ፤ ከጎዴ እስከ ሀርሺን በመጓዝ የሶስተኛ ዲግሪ ማሟያ ፅሁፋቸውን ጨምሮ በጉዳዩ ላይ ወደ አንድ ደርዘን የሚቆጥሩ ጥናታዊ ፁሁፎችን በጆርናሎች እና በአካዳሚያዊ ስብሰባዎች ላይ አቅርባዋል። የክልል አምስትን የድህረ-ደርግ ፖለቲካዊ ጥምዝምዞሽ የተመለከቱ ጥናቶችን አስመልክቶ ዶ/ር ሃግማን ሁለት ጠርዝ እና ጠርዝ የቆሙ ፖለቲካዊ አውዱን መተርጎሚያ ጫፎች እንዳሉ ይናገራሉ።

የመጀመሪያው በተለምዶ ‹‹ጎሳ ተኮር መላምት›› /clan Hypothesis/ ተብሎ የሚጠራው ነው። በዋናነት ኢትዮጵያውያን ባልሆኑ ፀሐፊዎች የሚቀነቀነው የጎሰኝነት መላምት ለኡጋዴን የፖለቲካ ችግር የብሄሩን የአርብቶ አደርነት ባህል ተጠያቂ ያደርጋል። ፋሲል ሮቤል የተባሉ ፀሐፊ “The death of an era and the demise of the community: EPRDF'S manipulation of Somalia Clans” በሚለው ፅሁፋቸው ይህ ምልከታ የኢትዮጵያውያኑን ሱማሌያዊ ማንነት ከተለምዶው የኢትዮጵያ ብሔራዊ መለዮ ጋር የሚቃረን፣ በማይቀለበስ የአማፂነት መንፈስ የተገራ እና ፖለቲካዊ ረብሻኝነት የተጠናወተው አድርጎ እንደሚተረጉመው ያወሳሉ።ሀሳቡን በከፊልም ቢሆን ምሁራዊ ድጋፍ የሰጡት ፕ/ር ጆን ማርካኪስ፣ የኡጋዴን የፖለቲካ ችግር መነሾ በነቢብም ቢሆን የራስን እድል ለመወሰን በሚያስችለው የኢህአዴግ ፌዴራሊዝም ግድ ለሚለው የዘመናዊ ተቋማት ግንባታ የብሔሩ ልሂቃን ከባህላዊ ማንነታቸው አንፃር የተመቹ ባለመሆናቸው እንደሆነ ይጠቅሳሉ። ፕ/ር ማርካኪስ “The Somalia in Ethiopia” በሚለው ፅሁፋቸው ‹‹ሊተገበር የተሞከረው የብሔር ፌደራሊዝም የክልሉን የጎሰኝነት ባህል መግራት አልቻለም›› ሲሉ ለክልሉ ያለመረጋጋት የብሔሩን ባህል በምክንያትነት አስቀምጠዋል።

ከዚህ በተፃራሪ የቆመው ትርክት በክልሉ ልሂቃን በኩል የሚሰማው የቅኝ ግዛት ሀቲት ነው። የዚህ ሀሳብ ዋነኛ አራማጅ ከሆኑት የብሄሩ ወካዮች አንደኛው ሰይድ የሱፍ አብዲ እንደሚሉት ብሪታንያ፣ ጣልያን እና ፈረንሳይ በአፍሪካ ቀንድ የነበራቸውን ዓይነት የቅኝ ገዢነት መልክ የኢትዮጵያ ተከታታይ መንግስታትም ይጋሩታል። “Self-determination for Ogaden Somalis” በሚለው ፅሁፋቸው ሰይድ የሱፍ የኡጋዴን ችግር ‹‹በቅኝ የመገዛት ተግብሮት ውጤት›› ስለመሆኑ ይከራከራሉ። በእርሳቸው ትይዩ የቆሙት አብዱራህማ ማህዲ ሀቲቱን ወደ መሬት ለማውረድ በመሞከር የክልሉ ያለመረጋጋት ‹‹ማዕከላዊውን መንግስት የመሩ ገዢ ቡድኖች የብሔሩን አባላት ሰብዓዊ መብቶች በመጣሳቸው›› እንደሆነ “The Ogaden people: past and present” በሚል መጣጥፋቸው ያወሳሉ። ለዚህ አቋም ተሟጋቾች በተለያዩ ተቋማት ዘገባ በክልሉ የተስተዋለው የሰብዓዊ መብት ጥሰት፣ የመሰረታዊ ምግብ ዕጦት እና ተቋማዊ መፈራረስ መግፍኤም ሆነ መፍትሔ መታየት የሚኖርበት በቅኝ በመገዛት እና ያለመገዛት ማዕቀፍ ውስጥ ነው።

እኒህን ሁለት ሙግቶች የመረመሩት ዶ/ር ሃግማን የትኞቹም መተንተኛ ጫፎች ምልዑነት እንደሚጎድላቸው ያምናሉ። የመጀመሪያው ሙግት ጉድለት የኡጋዴንን አባላት ፖለቲካዊ አተያይ ከጥንተ-ነገር ማንነቶች /Primordial/ ጫፍ ለመገንዘብ መሞከሩ ነው። ይህ አካሄድ በበኩሉ ግለሰቦች ለጎሳቸው የሚኖራቸውን ታማኝነት ለፖለቲካዊ ተቋማት ከሚኖራቸው መታመን እጅግ ብልጫ ያለው አድርጎ ያቀርበዋል። በተራዛሚውም በክልሉ በተከሰተው የተቋማት መድቀቅ በገዢው ፓርቲ የፖለቲካ አተገባበር ይልቅ የጎሳውን ባህል በተጠያቂነት ይከሳል። በሌላ በኩል ሁለተኛው የቅኝ ግዛት ሀቲት ከታሪክ ከላሽነቱ ውጪ ሁለት ተግዳሮቶችን መሻገር እንደሚሳነው ዶ/ር ሀግማን “Beyond clannishness and colonialism: understanding political disorder in Ethiopia's Somali region” በሚል ርዕስ ባሳተሙት ጥናታዊ ፅሁፍ ይሟገታሉ። የመጀመሪያው የትኞቹም የዘመናዊት ኢትዮጵያ መንግስታት እንደሌሎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች በክልሉ ሰፋ ያለ የተቆጣጣሪነት አቅም ያልነበራቸው መሆኑ ነው። በክልሉ ለተከሰተው ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ግልጋሎት ክስረትም ይህ መንግስታዊ አቅማቸው መዳከም የተሻለ ገላጭ መሆኑን አጥኚው ይናገራሉ። ሁለተኛው የሌሎች ዘውጎች ልሂቃን እንደሚስቱት ሁሉ እነዚህም ብሔርተኞች የኡጋዴን ልሂቃን ከሀገሪቱ ማዕከላዊ መንግስት ጋር ከነበራቸው ግኑኝነት አንፃር ሁሉም ስርዓቱን በመቃወም የጋራ የሆነ አንድ ወጥ ማንነት እንዳላቸው አድርገው ማቅረባቸው ነው።

### የድቃይ መንግስትነት ዕዳ

የኢህአዴግን የሃያ አንድ ዓመታት የፖለቲካ ስርዓትን ያጠኑ መምህራን ፖለቲካዊ ይዘቱን ለመረዳት የመንፈቀ-ጥቅማዊ ግንኙነት / Neo-patrimonalism/ን ኃልዮት በማብራሪያነት ይጠቀሙበታል። በዚህ ሙግት ከገፉት መሀከል ከላይደን ዩኒቨርስቲው ጆን አቢቢኒክ እስከ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲው ጳውሎስ ጫኔ ያሉ ፀሐፊዎች በቀዳሚነት ይጠቀሳሉ። የኃልዮቱን የፖለቲካ ክዋኔ አፍታችነት በአፍሪካ አገራት ላይ ከሞከሩ አጥኚዎች አንዱ ሽንዲ ዋሌ ከሚልተን ብራተን ጋር በመተባበር “Neo-patrimonial regimes and political transition in Africa” በሚል ርዕስ ባሳተሙት ጥናት፤ ግለሰባዊ ግንኙነቶች፣ የስርዓቱ መሪ ፖለቲከኞች በፍጥነት መቀያየር አልፎም የተቋማት አለመረጋጋት አንድን የፖለቲካ ስርዓት በጥቅመኝነት መሰረት ላይ ለመቆሙ ወሳኝ መበየኛ ተለዋጮች ናቸው።

የሱማሌ ክልል ላይ የፃፉ እንደሚያወሱት የክልሉ ፖለቲካ በአንድ በኩል ፖለቲካዊ ይዘት ባለው ጎሰኝነት፤ በሌላ ጫፍ ደግሞ በገዢው ፓርቲ እና በሚመራው መንግስት ተጋቦት የሚዘወር ስርዓት ሆኗል። ይህንን ለማሳየት ዶ/ር ታቢያስ ሃግማን የክልሉን መሪዎች አመራረጥ ያነሳሉ። የሱማሌ ክልልን የሚመራውን ገዢ ፓርቲ ለመዘወር እድል የሚያገኙት ፖለቲከኞች በክልሉ ውስጥ ያሉ ዞኖችን እንዲያስተዳድሩ የሚጠበቁትን በአብዛኛው ከራሳቸው ጎሳ አባላት የሆኑትን ይመለምላሉ። የዞኖቹ መሪዎች በበኩላቸው የወረዳ አስተዳዳሪዎችን፤ እነርሱም በተራቸው የቀበሌ ሊቀ መናብርትን በዚሁ የአንድ ጎሳ መስፈርትነት ወደ አስተዳደር ቦታዎች ያመጣሉ። በዚህ መንገድ በክልሉ ፖለቲካ ከላይ እስከታች ያሉ ተቋማትን የሚመሩ ግለሰቦች ከአንድ ጎሳ የተሰባሰቡ ይሆናሉ። ዶ/ር ሃግማን እንደሚከራከሩት ከዚህ ሁነት በተዛመደ በክልሉ የሚስተዋለው በፓርቲ እና በክልል ስልጣን መሀከል ያለው ጥብቅ ትስስሮሽ ነው። በየትኛውም የክልሉ አስተዳደራዊ ስልጣን ላይ ለመቆየት በኢህአዴግ ዓይን ተወዳጅ ሆኖ መስገኘት ያስፈልጋል። የክልሉን ስልጣን መያዝ ቁሳዊ እና ቁሳዊ ያልሆነ የጥቅም ዕድሎችን መስጠቱ በክልሉ ልሂቃን መሀከል ከፍተኛ ጎሳ ተኮር ፉክክሮች እንዲደረጉ መንገድ ከፍቷል። ልሂቃኑ ይህን የስልጣን መተጋተግ በአሸናፊነት ለመወጣት ከበታቾቻቸው ጠንካራ የሀይል መሰረትን መገንባት ግድ ስለሚላቸው፣ በፉክክሩ ቢያሸንፉ የሚከሰተውን ተቋማዊ ጥቅም የጎሰኝነት መልክ በመስጠት ደጋፊዎቻቸውን ከራሳቸው ጎሳ ብቻ ይመለምላሉ። የዚህ አካሄድ አደገኝነት የሚገለፀው ‹‹ደህንነት ለማስጠበቅ›› በሚል መነሻ የክልሉ መሪዎች የየራሶቻቸውን ጎሳ አባላት መሳሪያ ማስታጠቃቸው ሲሆን ይህም ‹‹በእኛ ጎሳ በክልሉ መዋቅር አልተወከለም›› ብለው የሚያስቡ የጎሳ መሪዎች ከሌሎች አቻዎቻቸው ጋር በቀላሉ ወደ ከፋ ግጭት እንዲገቡ ይገፋቸዋል። የእነዚህ ሁለት ሁነቶች (የፓርቲ ፖለቲካ እና ጎሳ ተኮር ጥቅማዊ ግንኙነት) በአንድ ላይ መከሰት የክልሉን ተቋማትም ሆኑ ህጎች ተተግባሪነት ይገታል። ፕ/ር አብዲ ሳማተር “Ethiopian federalism: autonomy versus control in the Somali region” በሚለው ጥናታዊ ፅሁፋቸው እንደሚከራከሩት እነዚህ ክስተቶች ስርዓቱን በጥቅማዊ ግንኙነት ለማብራራት በቂ ከመሆናቸውም በላይ የክልሉን ህጋዊ ተቋማት አሽመድምዷቸዋል።

የጥቅመኛ መንግስት መለዮ ተቋማዊ አለመረጋጋት እንደመሆኑ የኃልዮቱ ተንታኞች ለዚህ በምክንያትነት የሚያነሱት የየተቋሞቹን መሪዎች በአጭር ጊዜ ውስጥ የሚከወን የመተካካት ሂደት ነው። እነ ቫንዲ ዋሌ እንደሚሉት የማዕከላዊ መንግስቱን የሚመሩ ፖለቲከኞች በየትኛውም ክልል የሚገኙ የፓርቲ መሪዎች ፖለቲካዊ መደላደሎችን በመፍጠር የጌታና ሎሌ /Patron-client/ ትስስሮሹን ያላሉ ከሚል ስጋት በስልጣን ላይ ረዘም ላለ ጊዜ እንዲቆዩ አይፈቅዱላቸውም።

ዶ/ር ሃግማን እንደሚያወሱት የትኛውም የክልል 5 ፕሬዚዳንት ከሶስት ዓመታት በላይ አልቆየም። ‹‹ከዚህ ውስጥም ቢሆን ግማሹን በፌደራል መንግስቱ ጥልቅ ምርመራ ሲደረግባቸው የፈጁት ነው››ይላሉ ዶ/ር ሃግማን ከላይ በተጠቀሰው ስራቸው። ፕ/ር ማርካኪስ በበኩላቸው ሙስና እና ስልጣን ያለአግባብ መጠቀም የሚሉት ክሶች ልሂቃኑ በሚመሯቸው ተቋማት ጠንካራ ድጋፍ እንዳያሰባስቡ በሰበብነት የሚቀርቡ ማስወገጃ ምክንያቶች መሆናቸውን ይጠቅሳሉ። ዶ/ር ቶብያስ ሀግማን “Challenges of decentralization in Ethiopian's Somali region” በሚለው ሌላኛው ጥናታዊ ስራቸው፤ በክልሉ የሚገኙ ልሂቃን ይህን መገንዘባቸው የየራሳቸውን ጎሳ በመቀስቀስ ‹‹ለእኛም ወረዳ ይገባናል›› የሚል ጥያቄ ማንሳታቸውን ይኸም የክልሉን የወረዳዎች ብዛት እያናረው እንደመጣ ይናገራሉ። ፀሐፊው በጥናታቸው እንደሚደመድሙት አሁን አሁን የነዋሪዎቹ ጥያቄ እየሆነ የመጣው የአዲሱ የክልል መንግስት ምን የተሻለ ነገር ያደርግ ይሆን? ከሚል ይልቅ ‹‹አዲሱ ፕሬዚዳንት ምን ያህል በስልጣን ይቆይ ይሆን?›› ወደሚል የስልጣን አለመረጋጋት ስጋትን የሚናገር ሆኗል። ለነዶ/ር ሀግማን ክርክር ተጨማሪ ነጥቦችን የሚያነሱ ፕ/ር ሳማተር በበኩላቸው ኢህአዴግ በተለይም ህወሓት በ‹‹አማካሪነት›› ስም ወደ ክልሉ የሚልካቸው ከፍተኛ ካድሬዎቹ ከላይ የተጠቀሱትን የክልሉን ልሂቃን ዝውውር ይወስናሉ። እንደ ዶ/ር ሳማተር ከጥቂት ዓመታት በፊት የአለም ባንክ “Ethiopia: country financial accountability assessment” በሚል ርዕስ ባወጣው ሪፖርት ክልሉ በሰው ኃይልም ሆነ በመሰረተ ልማት ይሄ ነው የሚባል አቅም ያለማጎልበቱ ምክንያት በመሪዎቹ መቀያየር መሀከል የሚፈጠረው ክፍተት ተቋማቱን ካለሰራተኛ ማስቀረቱ ነው።እነዚህ ሁነቶች በጥልቀት የሚተነትኑት ሞሀመድ ካሽሊፍ እና ዶርንቦስስ “The Somali region in Ethiopia: a neglected human rights tragedy” በሚል ርዕስ ሪቪው ኦፍ አፍሪካን ፖለቲካል ኢኮኖሚ ጆርናል ላይ ባሳተሙት ጥናት የሱማሌ ክልል ፕሬዝዳንቶቹን ህወሓት ‹‹እንዳላቂ ቁስ›› እንደሚያያቸው ይናገራሉ።

### ኡጋዴን ‹‹እንደዳርፉር››?

ኢህአዴግ ወደ ስልጣን በመጣ ማግስት ያዘጋጀውን የሽግግር መንግስት ተከትሎ ቁጥራቸው በዛ ያለ ጎሳ ተኮር የሆኑ ፓርቲዎች የሱማሌ ክልልን ነዋሪዎች ድጋፍ ለማግኘት ሞክረዋል። በሽብርተኝነት የተሰየመው ኦብነግ የመጀመሪያውን ምርጫ በከፍተኛ ውጤት ማሸነፉን ተከትሎ የክልሉን መንግስት መመስረቱ ኡጋዴኒያን ባልሆኑት የሌሎች ጎሳዎች አባላት ዘንድ ፍርሃትን ፈጠረ። የወቅቱ የፍርሃት ምንጭ ግልፅ ነው። ኦብነግ በጊዜው የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት ለኡጋዴን ጎሳ እንዲሰጥ መጠየቁ የሌሎቹን የሶማሊያ ክልል ነዋሪዎች ዕጣ ፈንታ አደጋ ውስጥ የሚከትበት እድል የሰፋ ነበር። አህመድ ፋራህ የተባሉ ፀሐፊ “report on the peace and development” በሚል ርዕስ ለተባበሩት መንግስታት ባዘጋጁት ሪፖርት ላይ እንደሚያትቱት የኢትዮጵያ መንግስት ከሽብርተኛው አሊትሃድ ጋር በገጠመው ግጭት እና ተያያዥ ምክንያቶች ኦብነግ ከሽግግሩ መንግስት ወጥቶ አመፅን አማራጩ አደረገ። የታጣቂውን ቡድን የክልሉን ፖለቲካዊ ስልጣን ጥሎ መውጣት ተከትሎ ከኡጋዴን ውጪ ያሉ ጎሳዎችን የወከሉ ልሂቃን የመሰረቱት የኢትዮጵያ ሱማሌ ዴሞክራሲያዊ ሊግ /ኢሰዴሊ/ የክልሉን መምራት ጀመረ። የክልሉ ዋና መቀመጫም ለኡጋዴንያውያን ከምትቀርበው ጎዴ ወደ ጅጅጋ ተዛወረ። ፕ/ር አብዲ ሳማተር ከላይ በተጠቀሰው ጥናታዊ ፅሁፋቸው እንደሚሉት ኢሱዴሊ ከሌሎች ለዘብተኛ የቀድሞ የኦብነግ አባላት ጋር በመሆን የሱማሌ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ/ሱህዴፓ/ን በመመስረት በተከታታይ የመጡትን ክልላዊ ምርጫዎች በማሸነፍ ክልሉን በብቸኝነት መምራት ያዘ።

የሶማሊያ ክልልን ፖለቲካ ወደ ከፍተኛ ጡዘት ያናረው ኦብነግ ነዳጅ በማውጣት ላይ በተሰማሩት ዜጎች ላይ ግድያ ከፈፀመ ወዲህ ስለመሆኑ ሁኔታውን የተከታተሉ ተቋማትም ሆኑ የጉዳዩ ተንታኞች ይስማማሉ። ክስተቱ የኢህአዴግን የመንግስትነት አቅም የፈተነ አድርገው የሚያቀርቡ ቢኖሩም ብዙዎቹ ፌዴራል መንግስቱ ለታጣቂው ቡድን ተግባር የሰጠው ምላሽ ኢ-አግባብነት ላይ ያተኩራሉ።

ገዢው ፓርቲ በወሰደው እርምጃ የተቃጠሉ መንደሮችን እና የተፈፀሙ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን በስፋት የዘገበው የኢንዲፐንደት ጋዜጣ ዘጋቢ ስቲቭ ብሎምፊልድ “Ethiopia's 'own Darfur as villagers flee government violence” በሚል ርዕስ ባሳተመው መጣጥፍ ኦጋዴንን ‹‹የኢትዮጵያው ዳርፉር›› ብለው ለመጥራት ለደፈሩ ተንታኞች የትርክት ድገፋ ሰጥቷቸዋል። ከብሎምፊልድም ሆነ ከጄፍሪ ጄትልማን ዘገባዎች ውጪ ሁነቱን በተመለከተ የእንግሊዙ ቻተም ሀውስ “Conflict in the Ogaden and its regional dimension” በሚል ርዕስ ባዘጋጀው ሪፖርት በገዢው ፓርቲ ተፈፀመ ያላቸውን ጥልቅ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን ይዘረዝራል። ገዢው ፓርቲ ታጣቂውን ቡድን ለመምታት በሚል የወሰዳቸው እርምጃዎች ፓርቲው ያቀደውን ግብ ከማሳካት ይልቅ የኡጋዴንያውያንን ልብ እያሳጣው እንደሆነ የተቋሙ ሪፖርት ያስጠነቅቃል። ይህን መሰሉን የኡጋዴንን የመከራ መንገድ ለመግራት አንዳንድ ተንታኞች በመፍትሔነት የአሜሪካንን ሚና ያነሳሉ። የቀድሞ በኢትዮጵያ የአሜሪካ አምባሳደር እና የጆርጅ ዋሽንግተኑ መምህር ፕ/ር ዴቪድ ሺን በአፍሪካ ባሉ የታጠቁ ሃይሎችን በሚመለከት በተዘጋጀ ዓለም አቀፍ ኮንፈረንስ ላይ “Ethiopian Armed groups” በሚል ርዕስ ባቀረቡት ፅሁፍ በአቶ መለስ እና በኦብነግ መሪዎች መሀከል ተሞክረው የከሸፉትን ድርድሮች በመዘርዘር ኢህአዴግ ኦጋዴንን ለአለም አቀፍ ተቋማት እና ሚዲያዎች ክፍት እንዲያደርግ ‹‹አሜሪካ መወትወት አለባት›› ሲሉ ተናግረዋል። ፕ/ር ሺንም ሆኑ ሌሎች የፖለቲካው ተከታታዮች የአሜሪካንን የመፍትሔ ሰጭነት ሚና አጉልተው ቢያነሱም ሀገሪቱ በአፍሪካ ቀንድ የምትከተለውን ፖሊሲ በማጥናት የሚታወቁት ቴሬንሴ ሊዮንስ ሀሳቡን ‹‹ተጨባጭነት የጎደለው›› ሲሉ ያጣጥሉታል። እንደእርሳቸው ይህ ሙግት የኢትዮጵያ መንግስት ከቻይና ጋር የጀመረውን ግንኙነት ግንዛቤ ውስጥ ያልከተተ ከመሆኑ በዘለለ በዚህ ወቅት የኢህአዴግ ዋነኛ የሀይል መሰረት የአሜሪካ ድጋፍ እንዳልሆነ ይዘነጋል። ተመራማሪው “Ethiopia: Domestic and regional challenges” በሚለው ጥናታዊ ፅሁፋቸው እንደሚሉት ዋሽንግተን ስርዓቱን የሚጎዳ አንዳች ነገር ብትፈፅም ኢህአዴግ ወደ ቻይና ይፈጥናል።

አሁን በኡጋዴን መሬት ወታደራዊ መንግስት የሰፈነ ይመስላል። አካባቢው ከስርዓቱ መሪዎች ውጪ ላሉ የሀገር ውስጥ ጋዜጠኞችም ሆነ ክልሉን ማጥናት ለሚፈልጉ ምሁራን የማይፈቀድ ሆኗል። ይህ የገዢው ፓርቲ አካሄድ ያስቆጣው የሚመስለው የኒውዮርክ ታይምስ ዘጋቢ ኒኮላስ ኪርስቶፍ “What's he got to hide?” በሚል ርዕስ ከጥቂት ወራት በፊት በተካሄደው የዳቮሱ የአለም የኢኮኖሚ ፎረም ‹‹አምባገነን›› ብሎ የጠራቸውን አቶ መለስን ስለኡጋዴን እና ስለምን ስርዓታቸው ባለፈው አስር ዓመት ጋዜጠኞችን ለእስር ከዳረጉት ሀገራት ቀዳሚ ሆነ መሰል ጥያቄዎችን ለአቶ መለስ ለማቅረብ ፈልጎ ሊሳካላት ስላለመቻሉ ኃይለ-ቃል የሞላበት መጣጥፍ አሳትሟል። እርሱ እንዳለው አቶ መለስ ኦጋዴንን አስመልክቶ ለየትኞቹም ጋዜጠኞች መናገር የፈለጉት አንድ ነገር ነው፦ “Don't you dare Mess with me!”.

# በፍትሕ ጋዜጣ ላይ ለምንጽፍ ሁሉ

# እየተናገሩ አለማነጋገር፣ እያሰቡ አለማሳሰብ



ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም

ይህ ጽሑፍ ለእኔም የተጻፈ በመሆኑ አንድ ቀልድ እንደመግቢያ ልናገር፤ አማኑኤል ሆስፒታል ሕመምተኛው ውጭ ፀሐይ እየሞቀ ይጽፋል፤ ሀኪሙ ይመጣና ‹‹ከበደ፣ እንደምናደርህ?›› ብሎት ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ፣ ሀኪሙ ምን እየጻፍክ ነው? ይልና ይጠይቃል፤ ህመምተኛው ‹‹ደብዳቤ›› ይላል፤ ሀኪሙ ‹‹ለማን ነው?›› ብሎ ሲጠይቅ፣ ሕመምተኛው ‹‹ለራሴ›› ይላል፤ ሀኪሙ የሕመምተኛውን የውስጥ ስሜት ለማወቅ ጓጉቶ ‹‹ምን ይላል?›› ብሎ ይጠይቃል፤ ሕመምተኛው በመደነቅ ዓይኑን በልጠጥ አድርጎ ‹‹ዶክተር መቼ ተላከና፣ መቼ ደረሰኝና!›› አለው፤ እኔም…

በኢትዮጵያ ውስጥ እያሰቡ ለወደፊት ማቀድ አያዋጣም፤ ለሁሉም ሰው የወደፊቱን የሚወስኑት ወንበሩ ላይ ተቀምጠው ሰይፉን የጨበጡት ብቻ ናቸው፤ ከአንድ ዓመት በኋላ ይህንን አድርጌ፣ ከሁለት ዓመት በኋላ ደግሞ ከዚህ ደረጃ ደርሼ… እያለ በራሱ ሀብት፣ በራሱ ጉልበትና በራሱ እውቀት ሥራውን እያቀነባበረ ከዓመት ወደ ዓመት በእቅድ የሚሄድ የተፈቀደለት ብቻ ነው፤ ፈቃዱም ቢሆን ለአንድ ዓመት የተሰጠው በሌላው ዓመት ይሰረዝ ይሆናል፤ ለባል የተፈቀደው ለሚስት አይሠራም ይሆናል፤ ምክንያቱ ግልጽ ነው፤ አንድ ሰውም ሆነ አንድ ድርጅት እቅድ እያወጣ እየተሳካለት ከአደገ በራሱ የሚተማመንና በራሱ ኃይል እየተራመደ የሚያድግ ሲሆን ላልተደላደለው ሥልጣን አስፈሪ ይሆናል፤ በቋፍ እንዲኖር የሚገደደው ደካማ ሆኖ በልመናና በመለማመጥ እንዲኅብጥ ስለሚፈለግ ነው፤ አንድ ሰው ራሱን ችሎ ብቅ ሲል በኩርኩም አናቱን እያሉ ማኮማተር ባህል ነው፤ አልፎ አልፎ እንዲህ በኩርኩም ልኩን እንዲያውቅ ካላደረጉት ኅበዙ ኅበዝ እየሆነ ኅበዝ ያፈራል፤ ከርሞ ጥጃ ከመሆን ይወጣል! ከርሞ ጥጃነት በሚፈለግበት ሥርዓት እድገት እንዴት ይመጣል?

ሀሳብን በጋዜጣ ማውጣት አደባባይ መውጣት ነው፤ አደባባይ የሚወጡበት ጉዳይ የግል ሳይሆን የአገርና የሕዝብ ነው፤ መሆን አለበት፤ አደባባይ በወጣው ጉዳይ ላይ በአገርና በህዝብ ጉዳይ ያገባኛል የሚል ዜጋ ሁሉ ባለቤት ሊሆንበት ይችላል፤ በባለቤትነት ሊተችበት ይችላል፤ በጉዳዩ ላይ የሞቀ ክርክር ቢደረግበት ሁላችንም በብዙ መንገድ ተጠቃሚዎች ልንሆን እንችላለን፤ ነገር ግን እስከዛሬ የሚታየው አዲሱ ልምድ ከላይ ባለስልጣኖች እንደልባቸው ይናገራሉ፤ በግድም ይሁን በውድ አብዛኛው ሰው ይሰማቸዋል፤ ባለሥልጣኖቹን በማስተጋባት ቴሌቪዥኑና ራዲዮው ደጋግመው እስቲሰለች ድረስ ያሰማሉ፤ በግድም ይሁን በውድ የባለሥልጣኖቹ ንግግር ለብዙ ሰዎች ጆሮ ይደርሳል፤ ግን ጆሮ የደረሰ ሁሉ ወደልብ መተላለፉን እርግጠኛ መሆን አይቻልም፤ በአንጻሩ በግል ጋዜጦች ላይ የሚወጡት የተለዩና የተለያዩ ሀሳቦች በተለያዩ ጉዳዮች ላይ አመራሩን የሚተቹ ናቸው፤ እነዚህን ጋዜጦች የሚያነብቡ በጣም ጥቂቶች ናቸው፣ ጋዜጦቹን የሚያገኙዋቸው በገንዘባቸው እየገዙ በመሆኑ የሰዎችን ቀልብ መሳባቸው ይታወቃል፤ እነዚህን ትችቶች ባለሥልጣኖቹ ጉዳያቸው አድርገው የሚያነቡዋቸው አይመስለኝም፤ የእነሱ ንቀት ሚስትህ አረገዘች ወይ ቢሉት፣ ማንን ወንድ ብላ! እንዳለው ነው መሰለኝ፤ ባለሥልጣኖቹ ሁለት ጥቅሞችን ያጣሉ፤ አንደኛ የተቺዎቹን ሀሳብ መረዳትና ከራሳቸው ሀሳብ ጋር የማመዛዘን ዕድሉ ያመልጣቸዋል፤ ሁለተኛው ሕዝቡ በነፃነትና ያለምንም ግዴታ ትችቱን በማንበቡ ብቻ የሚያስተላልፈውን መልእክት ሳያውቁት ይቀራሉ፤ የዚህ ውጤት የአገር ጉዳት ነው፤ እንግዲህ እነሱ የሚናገሩትን ይናገራሉ፤ ሌላውም የሚናገረውን ይናገራል፤ በሁለቱም ወገን የሚነገረው ስለአንድ አገርና ስለአንድ ሕዝብ ነው፤ በሁለቱም በኩል የተያዘው ፈሊጥ ሳያነጋገሩ መናገር ነው፤ ክፉ ሕመም ነው።

የሳያነጋገሩ መናገሩ ፈሊጥ የሚታየው በባለስልጣኖችና በተቺዎቻቸው መሀከል ብቻ አይደለም፤ በተቺዎቹም መሀከል ያው ነው፤ ተቺዎቹም መናገሩን እንጂ እርስበርሳቸው መነጋገሩን ገና የለመዱት አይመስልም፤ እንደታዘብሁት እስካሁን ድረስ በፍትሕ ጋዜጣ ላይ በየሳምንቱ የሚናገሩት ሁሉ እርስበርሳቸው እምብዛም አይነጋገሩም፤ ይህ ሊሆን የሚችለው እያንዳንዱ በሚናገረው ሁሉም ፍጹም ስምምነት ካላቸው ብቻ ነው፤ ወያኔ/ኢህአዴግም እንደዚህ ያለ ፍፁም ስምምነት ያለው አይመስለኝም፤ ወይም በጋዜጣው ላይ የሚናገሩት ሁሉ ይፈራራሉ ማለት ይሆናል፤ ለመፈራራታቸው ብዙ ምክንያቶችን መጥቀስ ይቻላል፤ ነገር ግን አንዱም ምክንያት ለአገርም፣ ለወገንም፣ ለራስም ጠቃሚ አይመስለኝም፤ እንዲያውም የባለስልጣኖቹን ባሕርይ ወደመውረሱ የሚያስጠጋ ይመስለኛል፤ ይህ እውነት ከሆነ፣ ማለት በእኩልነት መነጋገር የማንችል ከሆነ መጀመሪያ ማድረግ ያለብን እያንዳንዳችን ለየራሳችን ተገንዝበን ካረጋገጥን ራሳችንን የምናስተካክልበትን መንገድ መከተል ግዴታ ይሆንብናል።

የፍትሕ ጋዜጣ የተሟላና የተዋጣለት ነው ባይባልም፣ በጣም ተፈላጊና ብዙ ሰውም የሚያነብበው ነው፤ ሆኖም በማስፈራራት የተካኑ ሎሌዎች አቤ ቶኪቾን ለስደት ከዳረጉት ወዲህ ፍትሕ ትንሽ ደረቅ ብሏል! በሀሳብ፣ በአስተያየትና እውቀትን በማስፋት የሚቀርቡት መጣጥፎች አብዛኛውን ጊዜ ፀሐፊው ከራሱ ጋር ብቻ የሚያወራባቸው መስለው ይታያሉ፤ የአንባቢን አእምሮ የመኮርኮር፣ ክርክር እንዲከፍት የማድረግ ኃይል ያላቸው አይመስሉም፤ ይህ የመጣጥፎቹ ጉድለት አይመስለኝም፤ ጠጥቶ ዝም፣ የጋን ወንድም! የሚባለው ዓይነት አንባቢና ፀሐፊ ነው፤ በጋዜጣው ላይ ብዙ ሰዎች መጣጥፎችን ቢያቀርቡም እርስበርሳቸው ሲነጋገሩ ወይም ሲከራከሩ አይታዩም፤ ይህ የሕመም ምልክት ይመስለኛል፤ አንድ ሰሞን ከአቶ ስብሐት ነጋ ጋር፣ አንድ ሰሞን ከፕሮፌሰር ገብሩ ታረቀኝ ጋር ክርክር ቢጤ ተጀመረና ሁሉም እየሮጠ በየምሽጉ ገብቶ ተቋረጠ፤ በዚያን ጊዜም ቢሆን ክርክሩን ከመሩት ሰዎች ውጭ የገባ አንድ ወይም ሁለት ሰው ብቻ ይመስለኛል።

በተለያዩ መንገዶች ደጋግሜ እንደገለጥሁት በእኩልነት ደረጃ ሆነን ለመነጋገርና ለመከራከር ያቅተናል፤ በየፊናችን ስንናገር ራሳችንን ላይ አውጥተን ሰሚውን ከታች አድርገን መደመጥን እንጂ እኛ በተራችን ሌሎችን ማድመጥ እንዳለብን አናውቅም፤ እኛ ለመናገር የምንደፍረውን ያህል ለተናገርነው መልስ የሚሰጠው ድፍረት እንዲያገኝ አንፈልግም፤ እንዲያውም መልስ ከተሰጠን እናኮርፋለን፤ ከመሳፍንት አገዛዝ የወረስነው ባህል ነው፤ ለዚህ ነው ክርክር የማንጀምረው፣ ቢጀመርም የማይቀጣጠለው።

አሁን ደግሞ ስለኢትዮጵያና ጃፓን፣ ስለአጼ ቴዎድሮስና ስለአንድ የጃፓን ንጉሥ ክርክር እየተካሄደ ነው፤ አዝማሚያው የተለመደውን ባሕርያችንን የያዘ ይመስለኛል፤ አንዱ ስለሁነት ሲናገር አንዱ ስለዓላማ ሉዓላዊነት እየተናገረ፣ አንዱ ስለአጼ ቴዎድሮስ ተግባር ሲናገር፣ ሌላው ስለአጼ ቴዎድሮስ ዓላማ መልስ ቢሰጥ መግባባት አይኖርም፤ ክርክሩን እያሻከረው ነው፤ በበኩሌ ሁለቱ ሰዎች የከፈቱት ክርክር ብዙ ቁም-ነገሮችን የያዘ በመሆኑ ብዙ ሰዎችን ይስባል የሚል እምነት ነበረኝ፤ አሁን እንደሚታየው ግን ሁለቱ ሰዎች እንደተለመደው እየተናገሩ ነው እንጂ እየተነጋገሩ አይደለም፤ ስለዚህም አንዳንዶቻችን ክርክር ውስጥ ገብተን የታሪክን አስተሳሰብና ታሪክን የማጥናትና የማጽዳት ኃላፊነታችንን ብንወጣ ጠቃሚ ይመስለኛል።

በክርክሩ ውስጥ ብዙ ሰዎች የሚያውቁትን እየያዙ ቢገቡበት ስለቴዎድሮስና ስለዚያ ዘመን ከፍተኛ ትምህርት እናገኝበት ነበር።

# የዳግማዊ ቴዎድሮስን አገርዓቀፍ እንድምታ ለመመልከት ‹‹ከፍታ››

ዓለማየሁ ገላጋይ

ከዕውቀት ወደ ጭፍን እምነት፣ ከማሳወቅ በደፈናው ወደ ማጥመቅ፣ ከማስማማት ወደ ግትር ግዝት… ያዘነበለውን የበዕውቀቱ ስዩም መከራከሪያ ፅሁፍ ሳምንት አነበብኩ። ‹‹ዳግማዊ ጃፓን፣ ዳግማዊ ቴዎድሮስ›› ከተሰኘው ከዚህ ዳግማዊ ፅሁፍ የተረዳሁት አንድ ነገር ብቻ ነው። በዕውቀቱ በተለይ አፄ ቴዎድሮስን በተመለከተ አንዳች ጥርጣሬ እውስጡ በቅሏል። ዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስን ውሸት ያገዘፋቸው፣ ስህተት ዘላለማዊነት ያጐናፀፋቸው፣ ማለባበስ ያከበራቸው፣ ስለመሆኑ ጠርጥሯል። ለጥርጣሬው ማረጋገጫ ሳያገኝ ደምድሟል። በድምዳሜውም ፅኑ አቋም ይዟል። ይሄን ፅኑ አቋም በዕውቀትና በምርምር ከማስደገፍ ይልቅ የሰብዓዊነትን ስስ ብልት ለመምታት ማነጣጠርን የክርክሩ አዋጪ መንገድ አድርጐ ወስዷል። እንዲህ ይላል፦

‹‹በቴዎድሮስ ዘመን የኖረው ህዝብ በንጉሱ የደረሰበት ግፍ ተገቢ አለመሆኑን ያውቅ እንደነበር የምንገነዘበው

‘አንድ እግር በርበሬ መንቀል አቅቷችሁ
አንድዶ ለብልቦ አቃጥሎ ይፍጃችሁ’

የሚለውን የምንትዋብ ግጥም ስንሰማ ነው። ዓለማየሁ ገላጋይ ነበልባሉ ከማይደርስበት ዘመን ላይ ተወልዶ የጭካኔውን ተገቢነት ሊያፀድቅ ይሞክራል። ያልተመለሰው ጥያቄ የርህራሄን ትርጉም የሚያውቁ ሰዎችን ማግኘት በማይቸግርበት በዚያን ዘመን ዳግማዊ ቴዎድሮስ በርበሬ (Barbaian) የሚል ቅፅል ያስለጠፈባቸው ጭካኔ ውስጥ ለምን ገቡ የሚል ነው።››

የበዕውቀቱ ፅሁፍ ‹‹ልብ›› ያለው እዚህ አንቀጽ ውስጥ ነው። …‹‹ዳግማዊ ቴዎድሮስ… ጭካኔ ውስጥ ለምን ገቡ?›› ይቺ ጥያቄ የብዙ ‹‹ንፁሃን›› እና ‹‹ጨዋዎች›› የፍርድ መሰናከያ ጉድባ ናት። ‹‹ለምን?›› ሰውን ከሰው ብቻ ሳይሆን ሰውን ከፈጣሪው ጋር ጭምር ለማቃቃር ጉልበት ያላት ጥያቄ። በነባሩ ትውፊታችን ብንመለከት የእግዚአብሔር ሕልውና ላይ በጠርጣሪነት (Agnosticism) እንዲህ የሚያገነግን ግጥም አለ።

‹‹የለህም እንዳልል ይመሻል ይነጋል፣
አለህም እንዳልል እንዲህ ይደረጋል፤››

በዕውቀቱ ስዩም ይሄንን የእግዚአብሔር ህልውና ግብረገባዊ ማረጋገጫ (Moral argument) ለአፄ ቴዎድሮስ የታሪክ ህልውና መለኪያ በማድረግ የመጀመሪያውን ስህተት ፈጽሟል። በመሆኑም ያ‹‹ንፁሃን እና ጨዋዎችን›› ለሚያጠቃው የፍርድ መሰናከያ ጉድባ እራሱን አጋልጧል። የበዕውቀቱ መሰናከያ ጉባ ጥቂት የጭካኔ ተግባራትን በማስረጃነት አቅርቦ አፄ ቴዎድሮስ ያላቸውን መልካም የታሪክ ሀብት ሁሉ የመውረስና የማደህየት፤ ዘመናዊነት የሌለው ጥንታዊ የበቀል ፍርድ ነው። በዕውቀቱ በነባሩ የትውፊት ወግ በአፄ ቴዎድሮስ ታሪክ ላይ ያለውን የተጠራጣሪነት አዝማሚያ በግጥም ቢያቀርብ እንዲህ የሚል ይመስላል፦

‹‹የሥልጣን አውራ ብለው ይጠሩሃል፣
እንዳልቀበለው እንዲህ አድርገሃል፤››

የአፄ ቴዎድሮስ የሥልጣኔ አውራነት ‹‹እንዲህ በማድረጋቸው›› ሊመዘን አይገባውም። በዚህ ጉዳይ ላይ የዘመኑን መከራከሪያ እናቅርብ ብንል አፄ ቴዎድሮስ ‹‹እንዲህ ማድረጋቸው›› የአፈፃፀም ችግር ነው ብለን እንዘጋው ነበር። ከዚያ ባሻገር አፄ ቴዎድሮስ የቴክኖሎጂ ሆነ የሥነ-ምግባር ስልጣን አርአያነታቸው እንዳለ ለብቻው ተመዝኖ ክብደቱና ቅለቱ የሚረጋገጥ እንጂ ‹‹እንዲህ ከማድርጋቸው›› ጋር ተደብሎ የሚወራረስ አይደለም።

አፄ ቴዎድሮስ ውሸት እንዳላገዘፋቸው፣ ስህተት ዘላለማዊነት እንዳላጐናፀፋቸው፣ ማለባበስ እንዳላከበራቸው፣ ከንቱ መታበይ እንዳላጐለመሳቸው… ለማረጋገጥ የሚያስችል ብዙ የታሪክ መረጃዎች አሉ። በዕውቀቱ ከሀሳብ ጨለማ ባሻገር ብርሃናማ የታሪክ ቅንጣቶችን እንዲለምድ ቢያስችለው ከብዙ በጥቂቱ እንጥቀስ። የሥነ-ምግባር ሥልጣኔን እናስቀድም።

ጳውሎስ ኞኞ Hennery Dutton የፃፈውን ጠቅሶና ተርጉሞ ‹‹አጤ ቴዎድሮስ›› የተሰኘ መፅሐፍ ላይ እንዲህ ይላል፦

‹‹…ድሆችን እራሳቸው እየተቆጣጠሩ ይጠብቃሉ። ድንኳናቸው በተተከለበት ቦታ ሁሉ የድሆችን አቤቱታ መስማት ይወድዳሉ። ሁልጊዜ ስራ ከመጀመራቸው በፊት የድሆችን ጉዳይ ይሰማሉ። በጉዞም ላይ በሳምንት በሺዎች የሚቆጠር ብር ለድሆች ይሰጣሉ። ይኸንንም ስጦታ በሚሰጡበት ጊዜ ‹‹ድሆችን ባልረዳ ለእግዚአብሔር ያሳጡኛል። እኔም እራሴ ደሃ ነበርኩ ይላሉ››

እንኳን ንጉስ ያለፈለት ተራሰው ‹‹እኔም እራሴ ድሃ ነበርኩ›› ለማለት ይደፍራል? ያውም በዚያ ደሃ በሚነወርበት፣ በሚናቅበት፣ በሚረገጥበት እና በአጥንተ ሰባራነት በሚንቋሸሽበት ዘመን ነው አፄ ቴዎድሮስ ይሄንን ከአፋቸው ሲያወጡ የተሰሙት። ድሆችን እንደወገን መቁጠር ብቻ ሳይሆን ከእነሱ እንደአንዱ አድርጐ እራስን ማሰብ ከቴዎድሮስ ብንማር በዚህ ዘመን አስተዳደር ላይ ስንት የሥነ-ምግባር ችግር ይቀረፍ ነበር? ይሄ ነው አፄ ቴዎሮስን የሥነ-ምግባር ሥልጣኔ አባት



የሚያሰኛቸው። ከዚያው ከጳውሎስ ኞኞ መጽሐፍ ይሄን እንጥቀስ፦

‹‹ቴዎድሮስ ጋይንት ላይ ሠፍረው ሳለ ወታደሮቻቸውን በባላገሩ ላይ ተሰሪ አገቡ። ባላገሩ እንዲቀልብ በየቤቱ ማስገባት ማለት ነው። ተሰሪ ከገቡት ወታደሮች መካከል አንዱ ወታደር አንዱን ባላገር ገደለው። የሟች ወገንም ከቴዎድሮስ ዘንድ መጥቶ አመለከተ። ቴዎድሮም ወታደራቸውን ሁሉ አፈርሳታ አስቀምጠው ገዳዩን አውጣ ብለው ያዙ። ወታደሩም በመላው አድሞ ገዳዩን አላየንም እያለ በቁስ እየተገዘተ ወጣ። የሟች ገዳይ ወታደር በመጥፋቱ ቴዎድሮስ ተናደው፦

‹‹ወታደር ብላ፣ ባላገር አብላ ያልሁ እኔ ነኝ። ደመኛህም እኔ ነኝና እኔን ግደል›› ብለው ተነስተው ለከሳሹ ነገሩት። ከሳሹም ‹‹እኔ ንጉስ መግደል አይቻለኝም›› አለ። ቴዎድሮስም እንዲያውስ ደም በከንቱ አይቀርም ብለው ለሟቹ ወገን የደም ገንዘብ ዋጋ ሰጥተው ሸኙት።››

በዕውቀቱ ስዩም ከዚህ የአፄ ቴዎድሮስ የዳኝነት ሥነ-ምግባር እርቆ እንኳንስ ያላግባብ ለገደለ ወታደራቸው ቀርቶ ልክውትም ለገደለው ኃላፊነት ለማይወስዱት ባለሥልጣናት መፍትሔ ሥራይ መሆኑን መቀበል አይሻም። ሌላ አንድ መሰል የዳኝነት ሥነ-ምግባር እንጥቀስ፦

ይሄንን ሽራፊ ታሪክ የሚነግሩን አቶ ገሪማ ታፈረ ናቸው አንድ ጊዜ ቴዎሮስ አንድ ታማኝ ወታደራቸውን ጠርተው ‹‹በፍርቃ በር በኩል እርጉዝ ሴት እንኳን ብትሆን እንዳታልፍ ጠንክረህ ጠብቅ›› ብለው አዘዙ። በሌላ ቀን ደግሞ ሌላውን ወታደር ጠርተው ‹‹ፈረስ እያለዋወጥክ ይህን ወረቀት የጁ ሰጥተህ በአስቸኳይ በስድስት ቀን ውስጥ ተመልሰህ እንድትመጣ›› ብለው ላኩት።

በተላኪና በጠባቂ መካከል የ‹‹አልፋለሁ፣ አታልፍም›› ፀብ ተነስቶ ጠባቂው ተላኪውን ገደለው። የሟች ወገኖች ቴዎድሮስ ፊት ቀረቡ። ‹‹በችሎቱ ላይ›› ይላሉ አቶ ገሪማ ‹‹በችሎቱ ላይ የተቀመጠው ፈራጅ ሁሉ እየተነሣ ገዳዩን ‹‹በደለኛ ነህ ስትሞት ይታየናል›› እያሉ ፈረዱ። አንድ ፈራጅ ግን ከተቀመጡበት ተነስተው ‹‹…ማየት የሚገባን በመጀመሪያ ከንጉሱ የተሰጠውን ትእዛዝ ነው። አንዱን ጠርቶ በዚህ በር ያለኔ ፍቃድ ወንድ ይቅርና የፀነሰች ሴትም ብትሆን እንዳታልፍ ብሎ ማዘዝ፤ እንደገና ሁለተኛውን ወታደር ጠርቶ ቀንና ሌሊት ሳታርፍ በስድስት ቀን የጁ ደርሰህ እንድትመለስ ብሎ ማዘዝ አግባብ ስላልሆነ ጥፋቱ የሚመለከተው ንጉሠ ነገሥቱን ነው። ነገር ግን ብርሃን ናቸውና ምን ይደረግ›› ብለው ተቀመጡ።

አጤ ቴዎድሮስ ይህንን ንግግር ሲሰሙ ከመቀመጫቸው ብድግ ብለው ‹‹እንዲህ ነው መሸምገል፣ ሁለት ጠጉር ማብቀል። በደለኛው እኔ ነኝ። ፍረዱብኝ›› ብለው ከተከሳሹ ወታደር ቦታ ወርደው ቆሙ። ወዲያውም ፈራጆች በፈረዱት ፍርድ መሠረት ለሟች ወገን 500 ብር የደም ዋጋ ቴዎድሮስ እንዲከፍሉ ተፈርዶ በስምምነት አለቀ። ለዚያን ዘመን ዋጋ በቴዎሮስ ላይ የተፈረደው 500 ብር አጠፌታ ዋጋ መሆኑ ነው።››

በዕውቀቱ ስዩም! በኢንተርኔት ለተጠየቀ ማብራሪያ ስንትና ስንት የግልምጫ ጡጫ የሚያወርድ መሪ ያለበት የዚህ ዘመን ተሳታፊ ነህና፤ የአፄ ቴዎድሮስን ከዙፋን ተነስቶ ተከሳሽ ሳጥን ውስጥ መቆም ልትኖርበት ባይሆንልህ ለምኞትህ ማሟያ በተቀበልከው በተገባ ነበር። ግን አልሆነልህም። የአፄ ቴዎድሮስን የሥነ ምግባር ሥልጣኔ አርአያነትን የሚያረጋግጡ ብዙ፣ እጅግ ብዙ የታሪክ ቅንጣቶችን እዚህ ማቅረብ ይቻላል።

ወደ ገፅ 14 ዞሯል

# ኮሎኔል መንግስቱ ኃ/ማርያም እየመጣ ነው?

በኮሎኔል መንግስቱ ኃ/ማርያም ይመራ የነበረው አምባገነኑ የደርግ ስርዓት በኢህአዴግ መራሹ ጦር በሀይል ከተገረሰሰ እነሆ ከቀናቶች በኋላ ድፍን ሃያ አንድ አመት ይሞላዋል፡፡ ግንቦት ሃያ ሺ ዘጠኝ መቶ ሰማንያ ሶስት አመተ ምህረት፡፡

የኮሎኔል መንግስቱ መንግስት ከስልጣን መውረድን ተከትሎ አዲሱ የኢህአዴግ መንግስት የቀድሞ መንግስት በአዋጅ የሻራቸውን ህዝባዊ መብቶች በአዋጅ እንደተፈቀዱ ይፋ አደረገ፡፡ ከዚህ ባሻገር በ1987ዓ.ም. በፀደቀው ህገ-መንግስት አብዛኞቹ መብቶች (ሰብዓዊ እና ዴሞክራሲያዊ መብቶች)ተካተቱና ዘላቂ ዋስትና አገኙ፡፡

ከእነዚህ ተፈቃጅ መብቶች አንዱ ኮሎኔል መንግስቱ በአዋጅ ደንግገውት የነበረው የሳንሱር /የቅድመ ምርመራ/ ስራን በአዋጅ መሻሩ መታወጁ ነው፡፡ ይህንንም ተከትሎ በርካታ የፕሬስ ውጤቶች በህትመት ላይ ውለው ለማየት ተቻለ፡፡ በእርግጥ በአሁኑ ወቅት በስራ ላይ ያሉት የህትመት ውጤቶች /በተለይም የጋዜጦች ቁጥር/ በእጅጉ አናሳ ነው፡፡ ይህ የሆነውም በራሱ ፍቃድ በሰጠው መንግስት የእጅ አዙር ጥቃት ነው፡፡ ነገር ግን የነበሩትን ነፃ ጋዜጦች እንዲዘጉ ሲያደርግ የተለያየ የመወንጀያ ህግ በማዘጋጀት እንጂ እንዲህ እንደዛሬው በጠራራ ፀሐይ ህገ-መንግስቱ መገርሰሱን ያረጋገጠውን ቅድመ ምርመራ /ሳንሱር/ በመመለስ አይደለም፡፡

ይህ የህገ-መንግስት ጥሰት የተከሰተው በመንግስት የሚተዳደረው ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ሰሞኑን ለአሳታሚዎች ‹‹የህትመት ስራ ስታንዳርድ ውል›› በሚል ርዕስ በበተነው ሰነድ ላይ ከአስቀመጠው አንቀፆች ውስጥ ህገ-መንግስቱን የሚፃረሩ በመኖራቸው ነው፡፡ በተለይ ደግሞ በአንቀጽ 10- ‹‹ህግን የተላለፈ ይዘትን አለማተም›› በሚል ርዕስ የሰፈረው ሀሳብ እንዲህ ይላል፡-

10.1 አሳታሚ በአሳታሚው እንዲታተም የቀረበለት የፅሁፍ ስክሪፕት ሕግን የሚተላለፍ ስለመሆኑ ለማመን በቂ ምክንያት ካለው አላትምም የማለት መብት አለው፡፡

10.2 አታሚ አሳታሚው የህግ ተጠያቂነትን የሚያስከትል የህትመት ይዘት የማውጣት ዝንባሌ ያለው መሆኑን ለማመን በቂ ምክንያት ካለው በማናቸውም ጊዜ ውሉን ለማቋረጥ ወይም ለመሰረዝ ይችላል፡፡

እነዚህ አንቀፆች በግልፅ ህገ መንግስቱን የሚፃረሩ ቢሆኑም ከመንግስት በኩል እስከአሁን ድረስ ምንም የተባለ ነገር የለም፡፡ ሁላችንም እንደምናውቀው መንግስት ተቃዋሚዎቹን እና ተቺዎቹን እስር ቤት ሲያስገባ ሁልጊዜም የሚሰጠው ምክንያት ተመሳሳይ ነው ‹‹ህገ መንግስቱን ለማስከበር ነው›› የሚል፡፡ አሁን ደግሞ በስሩ የሚተዳደረው ተቋም በግልፅ ህገ-መንግስቱን ተፃርሮ አፋኝ ውል አቅርቦአል፡፡ ይህን እንድንል ያስቻለን በህገ-መንግስቱ አንቀፅ 21 ንዑስ አንቀፅ 3(ሀ) ‹‹የቅድሚያ ምርመራ በማንኛውም መልኩ የተከለለ መሆኑን›› በማስታወስ ነው፡፡ ከህገ-መንግስቱ በተጨማሪ ስለመገናኛ ብዙሃን ነፃነት የሚናገረው አዋጅም ተመሳሳይ አንቀፆች አሉት፡፡

ህዳር 25 ቀን 2001 ዓ.ም. የወጣው ነጋሪት ጋዜጣ በአዋጅ ቁጥር 590/2000 ‹‹የመገናኛ ብዙሃን እና የመረጃ ነፃነትን ለመደንገግ የወጣ አዋጅ›› በሚል ርዕስ በገለፀው መሰረት በክፍል አንድ በቁጥር አራት ላይ ‹‹መገናኛ ብዙሃን ነፃ ስለመሆናቸው›› በሚለው ርዕስ ስር እንዲህ ይላል፡-

1. የመገናኛ ብዙሃን ነፃነት በህገ መንግሥቱ ዕውቅና አግኝቷል፡፡ ቅድመ ምርመራ በማንኛውም መልኩ የተከለከለ ነው፡፡

እንግዲህ መንግስታዊው ተቋም ብርሃንና ሰላም ደግሞ ፅሁፉን አንብቤ ካልጣመኝ፣ ካልተመቸኝ ወይም ዝንባሌው ህግ የሚጥስ መስሎ ከታየኝ አላትምም፣ በማናቸውም ጊዜ ውሉን ለማቋረጥም የሚከለክለኝ የለም እያለ ነው፡፡ በአንድ ሳምንት ውስጥም ይህንን ውል ካልፈረማችሁ ጋዜጣችሁን አላትምም ሲል ከትላንት በስቲያ ለሁሉም ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ደብዳቤ ልኳል፡፡ ይሄኔም ነው እስከዛሬ ድረስ ‹‹ህገ-መንግስቱን አደጋ ላይ ሊጥሉ፣ ሊቃወሙ፣ ሊያፈርሱ….›› ሲያሴሩ ደረስኩባቸው እየተባለ የሚታሰሩ ተቃዋሚዎች እና ጋዜጠኞች ጉዳይ የእስራቸው ምክንያት ይበልጥ ግልፅ የሚሆነው፡፡

መቼም መንግስት ራሱን እንደ ጲላጦስ ነፃ አድርጎ ‹‹ጉዳዩ የአታሚውና የአሳታሚው ነው፣ እኔን አይመለከተኝም›› የሚል ቀልድ ይቀልዳል ብለን አናስብም፡፡ ምክንያቱም የሞያ አጋሮቻችንን ጨምሮ ፖለቲከኞችን ሲያስር ጆሮአችን እስኪደነቁር ድረስ የሚነገረን ‹‹ህገ መንግስቱን ለማስከበር ነው›› የሚል ምክንያት ነውና፡፡

ለዚህም ነው አሁን ብርሃንና ሰላም ከመንግስቱ ኃ/ማርያም የስልጣን እድሜ ጋር አብሮ ያከተመውን ‹‹ቅድመ ምርመራ››፣ ህገ መንግስቱን ጥሶ በስራ ላይ ሲያውል ሲሞክር መንግስት ህገ-መንግስቱን የማስከበር ግዴታውን ይወጣል ብለን የምናስበው፡፡

ይህ ሁኔታ በዚሁ የሚቀጥል ከሆነ በፍትህ እምነት የደርግን ሸንጎ የአንድ ፓርቲ ፓርላማን ጨምሮ የሚያስታውሰንን በብዙ ሺህ ኢትዮጵያውያን ሰማዕታቶች የወደቀው የኮሎኔል መንግስቱ ኃ/ማርያም አገዛዝ በሌላ ባርኔጣ እየተመለሰ እንደሆነ ነው፡፡ ምንም እንኳን በኢህአዴግ እና በደርግ መካከል ያለው ልዩነት ጠባብ ቢሆንም ኢህአዴግን ከደርግ የተሻለ የሚያደርገው ብቸኛ ምክንያት ቅድመ ምርመራ /ሳንሱር/ በአዋጅ እንዲሻር መድረጉ ነው፡፡ ይኸውም ከ20 አመት የስልጣን ዘመኑ በላይ በማንም ሳይነካና ሳይሸረፍ ቆይቶአል፡፡ ዛሬ ግን ይህ መብት ቅርቃር ውስጥ ሊወድቅ ከአፋፍ ቆሟል፡፡ እናም በፍትህ ዕምነት የመንግስት አማራጭ ሁለት ብቻ ይሆናል፡፡ የመጀመሪያው ህገ-መንግስቱን ለመገርሰስ ቆርጦ የተነሳውን ብርሃንና ሰላምን ህገ-መንግስቱን እንዲያከብር ማስገደድ፣ አሊያም በብርሃንና ሰላም በኩል ህገ-መንግስቱን በትብብር ንዶ ሙሉ በሙሉ የኮሎኔል መንግስቱን ኃ/ማርያም አገዛዝ መመለስ፡፡ መንግስት የሚወስደውን አማራጭ በቀናቶች ውስጥ የምናየው ይሆናል፡፡

አስተያየት

# መቼ ጉልበት አጣን

በአዳም ጌታ
(adamgeta89@yahoo.com)

የፍትህ ጋዜጣ ቀበኛ አንባቢ ነኝ ብል ማጋነን አይሆንብኝም፡፡ ሁሌም አርብ ጋዜጣዋን በእጄ ለማስገባት ፒያሳና አራት ኪሎ መሄድ የአርብ ቀን የመጀመሪያ ስራዬ ነው፡፡ የሚወጡ ርዕሰ ጉዳዩችን አንብቦ ለመቀመጥ ሳይሆን ከነባራዊ ሃቅ ጋርም ለማመሳሰል ጥምር አነባለሁ፡፡ ለወጡ አንዳንድ ፁሁፋችም የራሴን አቋም /ግንዛቤ/ በጽሁፍ በማስቀመጥ ለዝግጅት ክፍሉ ለመላክ ባስብም በራሴ የተለያዩ ምክንያቶ ጽሁፎቹ ለአንባቢው ሳይደርሱ እኔው ጋር ቀርተዋል፡፡ በፍትህ ጋዜጣ ቅጽ 5 ቁጥር 180 አርብ መጋቢት /2004/ ዓ.ም ዕትም በአስተያየት አምድ የቀረበውንና ለውይይት የተዘረጋውን “የተከፋፈለ ህዝብ ጉልበት ይባክናል፤” አስተያየት ተመልክቼ ሀሳቤን ለማስቀመጥ እንደበፊቱ ሁሉ ጽፎ ከማስቀመጥ ይልቅ ለአንባቢያን እንዲደርስ ለማድረግ ወሰንኩ፡፡ በጽሁፉ ወስጥ የተካተቱ ሀሳቦችን ሚዛናዊነትና ለመልካም አስተዳደርና ልማት እምርታ(Quantum leap) ያላቸውን ጎታች ባህሪም ለመመልከት ሞክሬአለሁ፡፡ ክፍተትን አይቶ በመጠቆም ገዥውን ፓርቲ ማነቃቃትና ማገዝ የሚደገፍ ቢሆንም በጽሁፉ የተመለከትኩት ሁሉንም በድፍኑ የመንቀፍ / Criticize/ ዝንባሌን ነው፡፡ አስተሳሰቡ ሁሌም መንቀፍ የሚመርጥና ክፍተት የሚያድን ፣በራስ ላይ እና በሌሎች ላይ ጭንቀት የሚዘራ ፣ ሀይልን የሚሠልብ እና ነባራዊውን ሁኔታ በችግር መነፅር የሚመለከት ነው፡፡ ይህ ከየትም የሚመጣ አይደለም ፤ምንጩ የአመለካከት ነውና፡፡ ፁሁፍ በሃገራችን የተከፋፈለ ህዝብ መኖሩን ገልፆ የክፍፍሉን ደረጃም በአምስት ዋና ዋና ነጥቦች ለማስቀመጥ ሞክሯል፡፡ እነዚህ ደረጃዎች ግን ለእኔ ውሃ የማይቋጥሩ መሆናቸውን እንደሚከተለው ተገንዝቤአለሁ፡-

1. ጽሁፉ በክልሎች ክፍፍል ሀገራዊ የአብሮነት ስሜት እንደከሰመ ያስቀምጣል፡፡ ይህን ነጥብ ስንመለከት የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔርሰቦችና ህዝቦች የጋራ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ታሪካዊ ጥቅሞቻቸውን ለማስጠበቅ ሲሉ የየዘመናቱን ሀገር በቀል የገዡ መደቦችንም ሆነ የውጭ ወራሪ ሃይሎችን ተፋልመው ድል በመንሳት በራሳቸው ስነ-ልቦና ታዳሽ የነፃነት ችቦ በመለኮስ ትውልደ የሚቀባበለው እሴት ባለቤት ለመሆን በታሪክ ታድለዋል፡፡ ከቅርብ ታሪካችን ብንነሳ እንኳን ባልተደራጀ መልኩ የተቀጣጠለው የ66ቱ የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዬታዊ የትግል ንቅናቄ ዘውዳዊ አገዛዙን ከስልጣን ማውረድ ቢችልም የህዝብን የመሬት ላራሹ ጥያቄ አድበስብሶ በመመለስ አብዬቱን አንኮላሽቶ ወታደራዊው ደርግ ወደ ስልጣን ወጣ፡፡ ይህ ወታደራዊ ሀይልም የብሔር ብሔረሰቦችን እውቅና በመንፈግ ብሄራዊ ጭቆናው ከኢኮኖሚያዊ ብዝበዛና ከመብት አፈና ጋር ተቆራኝቶ በከፋ መልኩ ተገለፀ፡፡ በወቅቱም ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ የትግል አግባብ ዝግ ሆነ፡፡ የህዝቦችን ጥያቄ በወታደራዊ ሀይል ማፈንና መጨፍለቅ ይቻላል የሚለው አምባገነኑ የደርግ መንግስት ኢትዮጵያን ወደ ተመሰቃቀለ የታሪክ ምዕራፍ አስገባት፡፡ በዚህም ዘመን ነበር የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች መሰረታዊ የዴሞክራሲ፣ የሰላምና የፍትህ ጥያቄዎችን በማንገብ ታግሎ ማታገል ይቻላል በማለት ትግሉ የተጠነሰሰው፡፡ በዚህም የኢትዮጵያ ህዝቦች የድል ቁንጮ የሆነው ዴሞክራሲያዊ ህገ-መንግስት ባለቤት እንዲሆኑ በማስቻል ሁነኛ ሚና በሃገራችን መጫወት የተቻለው፡፡

ይህ ህገ-መንግስትም የብሔር ብሔረሰቦችን ጥያቄ የመለሰና ዋስትናቸውን ያረጋገጠ መሆኑ ነው “የድል ቁንጮ” በሚል አግባቡ መግለጽ ያሻኝ፡፡ ህገ-መንግስቱ ያስቀመጣቸው ሰብዓዊና ዴሞክራሳያዊ መብቶች ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ የሚሆኑበት ምቹ ሁኔታ ተፈጥሮ እንደ አንድ ጀማሪ ሀገር የመልካም አስተዳደር ዳገቱን መውጣት የተጀመረው፡፡ ዜጋም እድሉ በነፃ የመደራጀት ምቹ ሁኔታዎች ተጠቅሞ በመድብለ ፓርቲ ስርዓቱ ተጠቃሚ የሚሆንበት ሁኔታ ተፈጠረ፡፡ በየጊዜው በተለያዩ መስፈርቶች አንፃር እየተመነደጉ ያሉ አራት ምርጫዎችንም አካሂደናል፡፡ እነዚህ ምርጫዎች ምልዓተ-ህዝቡን ያሳተፉና ህዝቡ ይሆነኛል ያለውን የፓለቲካ ፓርቲ የመረጠበት የአደባባይ ሃቅ ባለበት ሁኔታ “በህዝብ ይሁንታ ስልጣን የያዘ መንግስት ኢትዮጵያ አይታ አታውቅም” ብሎ መፃፍ በምርጫዎቹ በንቃት ተሳትፎ በካርዱ መቅጣት ፣ ማስጠንቀቅና ፍቃድ መስጠት የቻለውን ህዝብ መናቅ መስሎ ይሰማኛል፡፡ በሚሊዬኖች ኮፒ የተሸጠውና “The Ultimate Secrets of Total Self Confidence” የተባለው መጽሃፍ ፀሐፊ የሆኑት ዶ/ር ሮበርት አንቶኒ “Beyond Positive Thinking” በሚለው መጽሃፋቸው ነገሮችን የምናይበት መነፅር ባለፉ ማንነታችን በከፍተኛው ተፅዕኖ እንሚሞገት ሲገልፁ “ ከተወለድንበት ጊዜ ጀምሮ ስለራሳችን የተለያዩ መጥፎና ጥሩ፣ ጠቃሚና እሴት የማይጨምሩ ሀሳቦችን እንሰማለን፡፡ እነዚህ የተሳሳቱ ወሬዎች ሲደጋገሙም ማንነታችን ይሆናሉ፡፡ እርሱም ማንነታችንን እንደዚህ ነን ብለን ስለን የምናስቀምጠው ነው፡፡ ይህም ለራሳችን የምንሰጠው ግምት ብሉኘሪንት ይባላል፡፡ ሆኖም ግን ብሉኘሪንቱ የሆነው ሳይሆን የምናስበው ነው፡፡ ብዙ ጊዜ የምናገኛቸው መረጃዎችን ከየትና እንዴት እንዳገኘናቸው በሰከነ አዕምሮአችን ማሰብ ይሳነናል፡፡ በጥሬው እውነት አድርገን እንቀበለዋለን፡፡ እውነት ባይሆኑም እውነት እንደሆኑ እናምናለን፡፡”

ጽሁፉ በመልካም አስተዳደርና በልማት ዙሪያ ብሔር ብሔረሰቦች አብሮ በመኖር፣ በመልካም አስተዳደርና በልማት ዙሪያ አጀንዳቸው የላላ እንደ ሆነ አድርጎ ያስቀምጣል፡፡ ይህም ሀሳብ ውሃ እንደማይቋጥር ሩቅ ሳንሄድ በቅርቡ ዓመት የሞላው የታላቁ ህዳሴ ግድብ ኘሮጀክት በኢትዮጵውያን ፋይናንስና ዕውቀት እንደሚገነባ ሲገለጽ ግድቡ ቤንሻንጉል ስለሆነ “ለኔ ምኔ ነው” ብሎ የተቀመጠ አንድም ኢትዮጵያዊ አልነበረም፡፡ ዳር እስከ ዳር ሆ ብሎ ወጥቶ ድጋፉንና ደስታውን ብቻ ሳይገድብ ከሌለው ኪሱ የገንዘብ ድጋፍ ለማድረግ ወሰነ፡፡ ከዚህም አልፎ ግድባችን በደለል እንዳይሞላ በየቀየው የተፈጥሮ ልማት ስራውን በትጋት ሲያከናውኑ ተመልክተናል፡፡ ከዚህ የበለጠ አንድነት፣ ድህነትን ለማንበርከክ “ድር ቢያብር…” ብሎ የተነሳ ለትውልድ የሚተላለፍ የማያልፍ ቅርስን ለማስቀመጥ በጋራ የተመመን ህዝብን የተለያየ ነው ብሎ መፈረጅ ምንአልባት ከላይ የዶክተሩን ፁሁፍ ለማጣቀሻነት እንዳመጣነው ሊሆን ይችላል፡፡

የብሔር ብሔረሰቦች ቀን ፋይዳው መጨፈር፣ የባህል ምግቦችን መጎራረስና በጋራ መፈክሮች በማሰማት ታጥሮ፣ የ “አንድ ሆነናል” መማማል ሳይሆን ፀሀፊው እንደገለፀው ለሀገራችን አልፋና ኦሜጋ የሆነው የልማትና ዴሞክራሲን አጀንዳ ማሳካት ነው፣ በልዩነትና መቻቻል አንድነትን መፍጠር ነው፣ አንዱ የሌላውን እሴት ማክበር ነው፡፡ አንድ መሆን በሀገራዊ ራዕይ ላይ የጋራ መግባባት መያዝ ነው፤ አንድ መሆን ሁሉም ኢትዮጵያዊ አንገቱን ለዘመናት ያስደፋውን ድህነት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ አውልቆ ለመጣል እያንዳንዱ ሌሊት እሾህ ሆኖ ሲወጋው ነው፤ ከዚህ ውጭ የሚሆን አንድነት ዳቦ የማይጋግር ሆኖ ይሰማኛል፡፡ የኢትዮጵያ ህዝቦች ምቹ ሁኔታ ተፈጥሮላቸው ድንጋዩን ፈጭተው አፈር አድርገው በወኔና በሙሉ ልቦና መተማመን ሲሠሩ ድህነትም መንበርከክ ይጀምራል፡፡ ስደትና አንገት መድፋት ይቆማል፡፡ መፍትሔው ሁሉም ክልሎች ውስጣዊ የመልማት አቅማቸውን ሲያጎለብቱ መሆኑ ደግሞ ሁላችንንም የሚያስማማ ይመስለኛል፡፡ ያኔ አይደለም ከክልል ክልል የሚደረግ ፍልሰት ይቅርና ከኢትዮጵያ ውጭ የሚደረገውም ይቆማል፡፡ “የባሌ ደን ሲቃጠል ….” ይህ ብሔር እንደዚህ ሆነ ይህኛው አልሆነም የሚለውና ሌሎች ማሳያ ምክንያቶች ፀሃፊው በውል ቢፈትሻቸው እርሱ ባቀረበው በተቃራኒ ሆነው ያገኛቸዋል፡፡ የባሌ ደን ሲቃጠል ሁሉም የዩንቨርስቲ ተማሪ ለጉዳዩ ትኩረት የሰጠበትና የአቅሙን ያደረገበት ሆኔታ እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው፡፡ ዋናው ጉዳይ ክልሎች ራሳቸውን በራሳቸው እንዲያስተዳድሩ መደረጉ ከሌሎች ብሔር ብሔረሰቦች ጋር አብሮ በመስራት ልማትና ዴሞክራሲን እውን የማድረግን ትግል አጠናከረ እንጂ አልከፋፈለም፡፡

2. በየክልሎች ያለውን ክፍፍል በሚመለከት የተቀመጠውን ስንመለከት ኢህአዴግ ያልመረጠውን አካባቢ እንደሚጨቁን ተደርጎ የተገለፀው አሁንም ፀሐፊው ጉዳዩን በሠከነ ሁኔታ የተመለከቱት አይመስልም፡፡ የኢህአዴግ ባህሪ የሚመነጨው ከድርጅቱ ኘሮግራም ነው፡፡ የድርጅቱ ኘሮግራም ለተመረጠና ላልተመረጠ በሚል የቀረበ ሽራፊ ሀሳብም የለውም፡፡ ለዚህ እንደማስረጃ መመልከት የምንችለው በ1997ቱ ምርጫ አዲስ አበባ ኢህአዴግ ሙሉ በሙሉ

ወደ ገፅ 6 ዞሯል

ፍትህ ጋዜጣ

በማስተዋል ህትመት ማስታወቂያ ስራድርጅት በየሳምንቱ የሚታተም

የአሳታሚው አድራሻ
አራዳ ክ/ከተማ ቀበሌ 11/12
የቤት ቁጥር አዲስ
ፒያሳ ራስ መኮንን
ድልድይ አጠገብ

ሥራ አስኪያጅ
ማስተዋል ብርሃኑ

ዋና አዘጋጅ
ተመስገን ደሳለኝ
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ ጀሞ
ሳይት የቤ.ቁ. 012

አዘጋጆች
ሙሉነህ አያሌው
ኃይለመስቀል በሸዋምየለህ

ከፍተኛ ሪፖርተሮች
መሐመድ ነስሩ
ኤልያስ ገብሩ

ሪፖርተር
ሰውዓለም ታዬ

አምደኞች
ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም
አለማየሁ ገላጋይ
ጌታቸው ታምራት
ዳንኤል ተፈራ
ቅጣው እጅጉ
ታዲዮስ ታንቱ
አናንያ ሶሪ

ግራፊክስ ዲዛይን
ሀብታሙ ታደሰ
ቤቴልሄም አመነሸዋ

የሽያጭ ሰራተኞች
ደለለኝ ሙሉጌታ
ታመነ ደገፋ

0911 928401
0911 712361
011 8951856
✉ 110744

E-mail:
fetih_gazeta@yahoo.com

www.fetehe.com

አታሚ
ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት
ክ/ከተማ:- አራዳ
ቀበሌ:- 17
የቤት:- 984

## አንድ በሉ

በዚህ አምድ ስር ሀገራዊ የፖለቲካ ጉዳዮች ይዳሰሳሉ

# የሹክሹክታው ክፍል ሁለት ገፅታ



ተመስገን ደሳለኝ

ከዚህ ቀደም ‹‹ሹክሹክታው ምንድር ነው?›› በሚል ርዕሰ ጉዳይ አንድ ፅሁፍ ፅፌ ነበር፡፡ የፅሁፉ ጭብጥ የሚያጠነጥነው የአረብ ሀገራት የተሳካ አብዮትን ተከትሎ በኢትዮጵያም ሁለት ዓይነት ሹክሹክታዎች ነፍስ መዝራታቸው ላይ ነበር፡፡ በገዢው መደብ እና በተገዢው መደብ ወይም ‹‹ስልጣን በቃችሁ›› እና ‹‹እንዴት ተደርጎ! ከዚህ በኋላም አርባ እና ሃምሳ አመት በስልጣን መቆየት እንፈልጋለን›› በሚሉ ኃይሎች መካከል ማለቴ ነው፡፡ በእርግጥ ሁለቱም በቂ ምክንያት አላቸው፡፡ ለምሳሌ የኢህአዴግ አመራር ከነጀሌዎቹ ‹‹ህዝቡ ይነሳብን ይሆን? ይጮኽብን ይሆን? መራራ ጉዲና የተራበ ህዝብ የሚበላው ሲያጣ መሪውን ይበላል የሚለው ይህ አይነቱን ተቃውሞ ይሆን?...›› የሚሉ የድንጋጤ ሹክሹክታ ቢያንሾኳሹክ አይፈረድበትም፡፡ ሁለተኛው ደግሞ በተገዥው መደብ ያሉ የጭቁን ኢትዮጵያውያን ሹክሹክታ ነው፡፡ ፍሬ ሃሳቡም ‹‹መቼ ይሆን እንደቱኒዚያውያን ወይም ግብፃውያን በሀገራችን ታላላቅ አደባባዮች በኩራት የምንጎማለለው? የምናምንበትን ሃሳብ የምናንፀባርቀው? በመረጥነው መንግስት የምንተዳደርበት ቀንስ እየመጣ ይሆን? የመንግስት የዘራፊነት እና የአስፈራሪነትስ ጀንበር እየጠለቀች ይሆን?...››› የሚሉ ተስፋ የሰነቁ ሹክሹክታዎችን ቢያናፍሱ ለዘመናት የናፈቁት ነውና ምክንያታዊ ነው፡፡ ዛሬ ደግሞ የሹክሹክታውን ሁለተኛ ክፍል ወይም የዕድገት ደረጃ በደምሳሳው እናየዋለን፡፡

ስለሹክሹክታው ከወደታች እመለስበታለሁ፡፡ በዚህ አጋጣሚ ምንአልባትም ድርጊቱ ተደጋግሞ የሚቀጥል ከሆነ ይውደም!፣ ይገደል! ያልነውን ‹‹አናርኪዝም››ን ሊያሰፍን ስለሚችል አንድ ጉዳይ ላንሳ፡፡ ፍትሃዊ ስላልሆነ ዳኝነት፡፡ መቼም ህግ የለም ካልን መንግስትም የለም ማለታችን እንደሆነ ግልፅ ነውና፡፡ ዳፉስ የፍትህ መፌክር ራሱስ ‹‹ፍትህ የአንድ አገር የማዕዘን ድንጋይ ነው›› አይደለምን? እናም የማዕዘኑ ድንጋይ ፈርሶ ከማለቁ በፊት ብንነጋገርበት ምን ይለናል?

...ዕለተ ሰኞ ሚያዝያ 22 ቀን 2004 ዓ.ም. በከፍተኛው ፍርድ ቤት 3ኛ ወንጀል ችሎት የአራት ወር እስራት ወይም የ2000 ብር ቅጣት ተፈርዶብኝ፤ ሁለተኛውን አማራጭ ተቀብዬ ለሰዓታት ከቆየሁበት በተለምዶ ‹‹የአንበሳ ቤት›› ከሚባለው ማረፊያ ቤት ተለቀኩ፡፡ በቅድሚያ ለምን ተከሰስኩ? ለምን ተፈረደብኝ? የሚል ቅሬታ እንደሌለኝ አስገነዝባለሁ፡፡ ምክንያቱም ቅሬታዬ ክሱ ላይ ሳይሆን ዳኝነቱ ላይ ነውና፡፡ ነገሩም እንዲህ ነው ሚያዝያ 11 ቀን 2004 ዓ.ም. አቃቤ ህግ ‹‹ከላይ በተጠቀሱት በከሳሽና በተከሳሾች (የፌዴራል ዓቃቤ ህግ እና እነአንዷለም አራጌ) መካከል በተከበረው ችሎት እየታየ ያለውን የወንጀል ክስ አስመልክቶ በፍትህ እና ነጋድራስ በተባሉ ሳምንታዊ ጋዜጦች እየወጣ ያለውን የተዛባ የችሎት ዘገባ አስመልክቶ የቀረበ አቤቱታ ነው›› በሚል ርዕስ የፃፈው ቅሬታ ደረሰኝ፡፡ ልብ በሉ ዓቃቢ ህግ ያቀረበው ክስ አይደለም አቤቱታ ነው፡፡ እናም ዓቃቤ ሕግ አቤቱታውን ከዘረዘረ በኋላ በመጨረሻም ከችሎቱ የሚፈልገውን ዳኝነት እንዲህ ሲል ጠየቀ ‹‹የተከበረው ችሎት ለወደፊቱ ከተመሳሳይ ድርጊት እንዲቆጠቡና ያወጡትንም ፅሁፍ የአንድ ወገን መረጃን ብቻ የያዘ መሆኑ ታውቆ ማስተባበያ እንዲሰጡበት እንዲደረግ በአክብሮት እናመለክታለን››

እንግዲህ የፍትህ ምላሽም በዚህ ማዕቀፍ ውስጥ ተገድቦ ነው የቀረበው፡፡ ፍርድ ቤቱም ተለዋጭ ቀጠሮ ሰጠ፡፡ በተለወጠው የቀጠሮ ዕለትም ፍርድ ቤቱ አቃቤ ሕግ አቤቱታውን ካቀረበባቸው የአራት ሰዎች ፅሁፍ ውስጥ አንዱ የሆነው ክንፈ ሚካኤል ደበበ (አበበ ቀስቶ) በችሎቱ ፊት ቀርቦ ፅሁፉ የእርሱ መሆኑንና አለመሆኑን እንዲያረጋግጥ ትእዛዝ ሰጠ፡፡ በእርግጥ የአቃቤ ሕግ አቤቱታ ውስጥ ‹‹ፅሁፉ የተከሳሾቹ የራሳቸው መሆን አለመሆኑ ላይም ጥርጣሬ አለኝና ይጣራልኝ›› የሚል ነገር ባለመኖሩ፣ እንዲሁም ከአራቱ ተከሳሾች በግሉ ጠበቃ ማቆም ያልቻለው (ሌሎቹ ጠበቃ ቀጥረዋል) አበበ ቀስቶ ብቻ እንዲቀርብ መታዘዙ ግራ ቢገባኝም በቀጠሮው ቀን አበበ ቀስቶ ቀርቦ ‹‹ፅሁፉ የራሴ ነው፡፡ የአዘጋጀሁትም እዚሁ ፍርድ ቤት በንባብ ላቀርብ ነበር፡፡ ሆኖም ስላልቻልኩ ለጋዜጣው ላኩት›› ሲል መሰከረ፡፡ እኔም ከአሁን አሁን አቤቱታው ውድቅ ሆኖ፣ በነፃ ተሰናብቼ ተግሳፅ ለአቃቤ ሕግ ይሰጣል ብዬ ብጠብቅም ሌላ ቀጠሮ ተሰጠ፡፡ እንደተለመደው በዚህም ቀን ቀረብኩ፡፡ ችሎቱም ‹‹ትእዛዝ›› ለመስጠት (የቅጣት ውሳኔ አይደለም ያለው ትዕዛዝ ነው፡፡ በትእዛዝ እና በቅጣት ውሳኔ መካከል ልዩነት መኖሩን ልብ ይሏል) የግድ አበበ ቀስቶ መቅረብ አለበት አለና የእለቱ ችሎት ለከሰዓት በኋላ ተቀጠረ፡፡ ከሰዓት በኋላም አበበን ጨምሮ ሁላችንም በችሎቱ ተገኘን፡፡ ፍርድ ቤቱም ትእዛዝ ሰጥተናል አለና ጉዳዩን በሶስት ከፍሎ እንዳየው ገለፀ፡፡ የአንዱአለም አራጌ እና የእስክንድር ነጋ ፅሁፍ ላይ አቃቤ ህግ ያቀረበውን አቤቱታ ውድቅ አድርገናል አለ፡፡ የናትናኤል መኮንን እና የክንፈ ሚካኤል ደበበ ፅሁፎች ላይ የቀረበው አቤቱታ ደግሞ ተገቢ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ እንዳመነበት ከገለፀ በኋላ በዚሁ ጉዳይ ላይ ‹‹ፍርድ ቤት ቀርበህ መስክር›› የተባለው አበበ ቀስቶ በዚሁ በመሰከረበት ጉዳይ ‹‹ችሎት በመድፈር›› ጥፋተኛ ተባለና የ8 ወር እስራት ተፈረደበት፡፡ በእኔ ላይ ደግሞ የአራት ወር እስራት ወይም የ2 ሺህ ብር ቅጣት እንደተወሰነ የመሀል ዳኛው በአክብሮትና በትህትና ገለፁ፡፡ የናትናኤል መኮንን ፅሁፍ ችሎት መድፈር መሆኑን ፍርድ ቤቱ አምኖበት እንደሆነ የተገለፀ ቢሆንም ስለናትናኤል ግን የተባለ ነገር የለም፡ ፡ መጠየቅ አለበትም የለበትምም አልተባለም፡፡ ሁለት ተመሳሳይ ጥፋት ካጠፉ ሰዎች መካከል አንዱ ተለይቶ የሚቀጣበት አካሄድ ለእኔ ግልፅ አይደለም፡፡ (ምንአልባት አበበ ቀስቶ ‹‹ፅሁፉ የእኔ አይደለም›› ብሎ ክዶ እኔን እንዲወነጅል ተፈልጎ ስላልተሳካ ይሆናል አበበ ከናትናኤል ተለይቶ የተቀጣው የሚል ክፉ ጥርጣሬ የለኝም፡፡ ሆኖም ይህ ሁኔታ ማብራሪያ ያስፈልገዋል)

ትልቁ ስጋቴ በፍርድ ሂደቱ ላይ የተስተዋሉ ሁለት ግዙፍ ነገሮች ናቸው፡፡ የመጀመሪያው አቤቱታ አቅራቢ አቃቤ ሕግ እኔን ወደፍርድ ቤት ያስጠራኝ ‹‹ማስተባበያ›› አወጣለት ዘንድ ፍርድ ቤቱ ትእዛዝ እንዲሰጥ ነው፡፡ በግልፅ በደረሰኝ የመጥሪያ ደብዳቤ ላይም ‹‹ማስተባበያ እንዲሰጡ ይደረግልኝ›› ሲል ገልፆአል፡፡ ነገር ግን አቤቱታ አቅራቢው ከጠየቀው ዳኝነት በእጅጉ የተለየ የቅጣት ውሳኔ ነው የተወሰነብኝ፡፡ ለእኔ እንደሚገባኝ ‹‹የእጅ ¬ጥብቅ ዋስ ይጥራልኝ›› ብሎ አቤቱታ ላቀረበ ሰው የቅጣት ውሳኔ እንደማስተላለፍ አይነት ሆኖ ነው፡፡ ሌላው ቀርቶ የቅጣት ውሳኔ የሚሰጥ እንኳን ከሆነ በየትኛውም ፍርድ ቤት ካለው አካሄድ አንፃር አቃቤ ሕግም ሆነ እኛ ተከሳሾች የቅጣት አስተያየት ልንጠየቅ ይገባ ነበር፡፡ ይህም አልተደረገም፡፡ የተደረገው ምንድን ነው? በደፈናው ‹‹ትዕዛዝ እንሰጣለን›› ተባለ፡፡ የተነበበው ግን ትእዛዝ ሳይሆን የቅጣት ውሳኔ ነው፡፡ ይህም ለፍትህ ስርዓቱ ቀጣይነትና ተቀባይነት አደጋ ይመስለኛል፡፡

ሌላው በእጅጉ አስገራሚ የሆነው ጥፋተኛ የተባልንበት አንቀጽ ነው፡፡ ፍርድ ቤቱ ‹‹የወንጀለኛ መቅጫ ህግ አንቀጽ 449/1 ላይ የተገለፀውን ተላልፋችኋል›› ብሎ ነው ፍርድ የሰጠው፡፡ ሆኖም ለአንባቢያን እና ለሚመለከተው አካል ግልፅ ይሆን ዘንድ አንቀፁ የሚለውን እንየው፡-

አንቀጽ 449 -ፍርድ ቤትን መድፈር

1. ማንም ሰው በፍርድ ቤት ምርመራ በሚደረግበት ወይም የፍርድ ሥራ በሚከናወንበት ጊዜ፡-

ሀ. ፍርድ ቤቱን ወይም የዳኝነት ስራ በማከናወን ላይ ያለውን ዳኛ በማናቸውም መንገድ የሰደበ፣ ያወከ ወይም በነዚሁ ላይ ያፌዘ ወይም የዛተ እንደሆነ ወይም

ለ. የፍርድ ቤቱን ሥራ በማናቸውም ሌላ መንገድ ያወከ እንደሆነ፤

ከአንድ አመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም ከሶስት ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል ይላል፡፡

እንግዲህ በእኔም ሆነ በአበበ ቀስቶ ላይ ዓቃቢ ህግ ያቀረበው አቤቱታ በዚህ አንቀፅ እንደተብራራው የፍርድ ቤት ምርመራ በሚደረግበት ወይም የፍርድ ስራ በሚከናወንበት ጊዜ ‹‹ችሎት ደፈራችሁ›› የሚል አይደለም፡፡ ከችሎት ውጭ በጋዜጣ ላይ ችሎቱን ደፈራችሁ የሚል ነው፡፡ የወንጀለኛ ህጉም ይህንን አይነት ጥፋት የሚዳኘው በአንቀጽ 449/1 ሳይሆን በአንቀጽ 449/2 እንደሆነ በግልፅ እንዲህ ሲል ይደነግጋል፡-

አንቀጽ 449/2 ‹‹ወንጀሉ የተፈፀመው ከችሎት ውጭ ሆኖ ዳኛው ሥራውን እያከናወነ ባለበት ጊዜ ከሆነ፣ ቅጣቱ ከስድስት ወር የማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም ከአንድ ሺህ ብር የማያበልጥ መቀጮ ይሆናል››

ታዲያ የተከበረው ፍርድ ቤት፣ ያውም ከፍተኛው ፍርድ ቤት፣ ያውም ሶስት ዳኞች የተሰየሙበት፣ ሌላው ቀርቶ ዜጎች በጠቅላይ

ወደ ገፅ 6 ዞሯል »

## ኤች ኬ አሳታሚ ኃ/የተ/የግል ማህበር
## HK Publisher P.L.C

አድራሻ፡- 0911-23-80-57 ☎ 0118601464 S/C Yeka Kebele 17 H.No923 TIN 0005959043
አዲስ አበባ/ Addis Ababa, Ethiopia
ዋና አከፋፋይ ኤደን መጽሐፍት ቤት ፡- ለም ሆቴል ከፍ ብሎ ☎ 0118601464

Reference Books:
TOP BIOLOGY 7-8
TOP PHYSICS 7-8
TOP PHYSICS 9-10
TOP PHYSICS 11-12
TOP CHEMISTRY 7-8
TOP MATIMATICS 7-8
TOP ENGLISH 5-8
TOP ENGLISH 1-4

ስለህክምና:
NURSING ART COC
NURSING MODALE

ለእንግሊዘኛ ንግግር የሚጠቅም:
GATEWAY SPOKEN WITH CD
BEST SPOOKEN ENGLISH

አፈ-ታሪክ:
Mythology
(የአማልክትና የጀግኖች ታሪክ)

አጋዥ:
መሠረታዊ ሳይንስ 1-4
መሠረታዊ ሳይንስ 5-6

ወርቃማ የፍቅር ጥቅሶችና አባባሎች ቁጥር 1 እና2

አጋዥ:
አዲሱ ሂሳብ አጋዥ 5-6
አዲሱ ሂሳብ አጋዥ 3-4
አጠቃላይ አማረኛ 1-4
ዘመናዊ ስነ-ዜጋ 5-8

ሳይኮሎጂ:
የመኖር ክህሎት
በራስ መተማመን
የጥበብ ፊለግ
የመኖር ጥበብ
አይፈራም ጋሜው
የብቃት መንገዶች
የጣፋጭ ህይወት ሣይንሳዊ ጥበብ

ልቦለዶች:
የእንስቷ ትንቅንቅ
አስኳል ቁጥር 3
በቀለኛ ፍቅር

በቅርብ ቀን ተሻሽለው የሚወጡ መጽሐፍት

ተረቶች:
ምርጥ የአለም ተረቶች 1
ምርጥ የአለም ተረቶች 2
ምርጥ የአለም ተረቶች 3
ቶሚና ኳሱ
ብልጢ ዝንጀሮ

በቅርብ ቀን የሚወጡ
Top Biology 11-12
Top Chemistry 11-12

(የመኖር ጥበብ (አሻ)



ክቡራንና ክቡራት ደንበኞቻችን መጽሐፍቶቻችን ለማንኛውም ደረጃ ለሚገኝ ተማሪ አጋዥና የወቅቱን ስርዓት ትምህርት አሞልተው የያዙ በመሆናቸው ማንኛውም ወላጅ ለልጆቹ ሊገዛቸው የሚችሉ መጽሐፍት ናቸው፡፡ መጽሐፍቶቹን ለማግኘት በማንኛውም የመጽሐፍት መሸጫ መደብሮች ያገኞቸዋል፡፡

ኤች ኬ አሳታሚ ኃ/የተ/የግ/ማህበር የተለያዩ መጽሐፍት በገበያላይ ካዋለቸው ከብዙ በጥቂቱ



# ለህግ ተገዢ መሆን ሲባል

### ውድ ዶ/ር አድለር

መልካም ዜጋ የህጉን ትክክለኛነት አረጋገጠም አላረጋገጠም ለህግ ተገዢ ሆኖ መገኘት እንዳለበት ይታሰባል። ህግን በገዛ እጃችን እንደፈለግን ለማድረግ ከመሞከር ይልቅ ስህተት ነው ብለን ያሰብነውን ለማስቀየር መሥራት ተገቢነት ይኖረዋል ተብሎም ይገመታል። የለውጥ ንቅናቄ መሪዎች ሆኑ ሰባኪያን በተደጋጋሚ ከፍተኛው የሥነ ምግባር ደንብ የአንድ አገር ህግ ሊተካው እንደሚችል ይጠቁማሉ። የሥነ-ምግባር ደንቡና በፅሁፍ በሰፈረው ህግ መካከል አለመጣጣም ተፈጥሮ ሳለ ለመታዘዝም ሆነ ላለመታዘዝ የምንወስነው እንዴት ነው?

ኤም.ኤል

### ውድ ኤም.ኤል

ጥያቄህን እንዲህ በማለት ማቅረብ ደግሜ የምችል ይመስለኛል። የአንድ አገር ህግ ከሥነ-ምግባር ደንብ ጋር ባልተጣጣመ ጊዜ፣ አንድ ሰው ተነስቶ ተገዢ አልሆንም ቢል ለህግ ያለመገዛት ምክንያታዊ ነው ሊባል ይችላል ወይ? ከባድ ጥያቄ ነው። ምክንያቱም እርምጃ አልፎ-አልፎ፣ አንዳንድ ሰዎች ብቻ የሚያደርጉት ነገር በመሆኑ ከዚህ ያልተለመደ ድርጊት ከሚፈጥረው ሁኔታ ተነስቶ ብዙሃኑን እንዲያደርጉ ወይም እንዳያደርጉ መምከር ትክክል ስለማይሆን ነው። ነገሩ የአንድ አገር ህግ ከሥነ-ምግባር መመሪያ፣ ከተፈጥሯዊ ሁኔታዎችና ምክንያቶች ጋር ተጣጥሞ እንዲገኝ እንጠብቃለን። አንድ ድንጋጌ ፍትሃዊነትንና ጠቃሚነት እንዲኖረው ከማስፈለግ አልፎ በአጠቃላይ ግራ የማንጋባበት እንዲሆን ይጠበቃል። አንድ ወንጀለኛ መቅጫ ህግ ለህይወት፣ ለነፃነት፣ ለንብረትና ለተቀሩት ሰብዓዊ መብቶች አደገኝነት ያላቸውን አዝማሚያዎች የሚያግድ እንጂ የሚፈቅድ አይሆንም።

አንድ ህግ ከሥነ-ምግባር ደንቦች ጋር የተጣጣመ መሆን ይገባዋል የሚል አቋም ያላቸው ፈላስፎችና የሥነ-መለኮት ምሁራን አንዳንድ የህጉ ክፍሎች ሚዛናዊነት ሊጐላቸው እንደሚችልም ይጠቁማሉ እንዲህ ያሉ ህጐችን ኦፍ-ሞልተን ህጐች ናቸው ለማለት እንቸገራለን ይላሉ። ፈላስፋው አውጉስቲን ይሄን ጉዳይ ግልፅ በሆነ አግባብ እንዲህ ይገልፀዋል። ‹‹ፍትሐዊነት የጐደለው ህግ በሥም ብቻ ያለ ህግ ነው።›› በማከልም የመንግሥት ኃይል ከበስተጀርባው ሊኖር ቢችልም ዋነኛው የሥነ-ምግባር ስልጣን ግን ይጐድለዋል፤ በመሆኑም አካላችንን እንጂ ህሊናችንንና መልካም ፍቃዳችንን ማዘዝ ይሳነዋል ይላል።

እንግዲህ አንድ ምግባረ ሰናይ ሰው እንዲህ ያለ የህግና የሥነ-ምግባር አለመጣጣም በገጠመው ጊዜ ምን ያደርጋል? ሁለት ዋና ዋና አማራጮች ፊት ለፊቱ ይጋረጣሉ። አንድም ለህግ ተገዢ አለመሆን፤ አለበለዚያም ለመለወጥ መንቀሳቀስ። የመጀመሪያው ለህግ ተገዢ የአለመሆን አማራጭ የሚቀነቀነው በሔነሪ ዴቪድ ቶሪዮ ነው። ቶሪዮ እንደሚለው አንድ ፍትሐዊነት ያለው ሰው ትክክል ያልሆነ ህግ እስከሚለወጥ ወይም እስከሚሻሻል ድረስ ተገዢ ሊሆን አይገባውም። የህጉ ትክክለኛ አለመሆን እንደተሰማው ተቃውሞውን ባለመገዛት መግለፅ አለበት። ለህግ ተገዢ አለመሆን የሚያስከትለው የመንግስት ቅጣት ቢኖርም እንኳን ፍትሐዊነት ለሌለው ህግ ለአፍታም ታዛዥ መሆን የለበትም ይላል።

እንደ አውጉስቲንና አኩዊናስ ያሉት ፈላስፎች ደግሞ የሥነ ምግባር ድጋፍ የሌለው ህግ በህሊና ሳይሆን በኃይል አስገድዶ የሚይዝ በሥም ብቻ ያለ ህግ ነው ይሉታል። ይሁንና እንዲህ ያለ ህግ ሲያጋጥም ፈጥኖ አለመታዘዝን አይደግፉትም። ምክንያታቸው ደግሞ ለአንድ ማህበረሰብ ደህንነት ከመጥፎ ህግ በላይ ያለመታዘዝ አዝማሚያ ጉጂ ስለሚሆን ነው ይላሉ።

ሌላኛው ፈላስፋ ጆን ሎክ ደግሞ ህዝቦች ትክክለኛነት የሌለውን ህግ የመቃወም መብት እንዳላቸው ይናገራል። ነገር ግን እንደ አኩዊናስ ሁሉ አንድ ማስጠንቀቂያ ጣል ያደርጋል። እሱም መንግሥት አግባብነት የሌለውን ህግ ለመለወጥ ፍላጐቱ እስካለው ድረስ ተቃውሞን ማስነሳት ተገቢ አይደለም። መጥፎ ህጐች እንዲሻሻሉ የሚያስችል ሁኔታ በሌለበት አግባብ ይላል ጆን ሎክ ግለሰቦች ለህግ ተገዢነታቸውን ቢያቆሙ መንግሥት ነገሮችን ላይታገስ ይችላል። ስለዚህ ሁኔታዎችን በማስተዋል ሥርዓተ-አልበኝነትን የምንቀንስበት አግባብ እንዲኖር ግድ ይላል።

ሎክ በመንግስት ላይ ለሚካሄድ ተቃውሞ አብዛኛው ህዝብ ተፈጥሯዊ መብቱን ያጣበትን ሁኔታ ብቻ መሰረት ቢያደርግ የተሻለ ውጤት ይኖረዋል የሚል እምነት አለው።

ሁሉም፣ በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ የፃፉ ሊቆች ፍትሐዊነት የሌለው ህግ ህዝቡን በህሊና ሊያስተሳስር እንደማይችል ይስማማሉ። ይሁንና ልዩነት ያላቸው ነገሮችን ለማሻሻል መወሰድ ያለበት እርምጃ ላይ ነው። ለሔነሪ ዴቪድ ቶሪዩ አፋጣኝ የሆነ ለህግ ያለመገዛት እርምጃ አንድ የሥነ-ምግባር ሰው ሊወስደው የሚገባ መብት ማስጠበቂያ ዘዴ ነው። በዚህ መንገድ ብቻ መጥፎ አዝማሚያዎችን መከላከል ይቻላል ብሎ ቶሪዮ ያምናል። ነገር ግን አኩዊናስና ሎክ ደግሞ ለህግ ያለመገዛቱን ንቃተ-ህሊና እና ፍትሐዊነት የሌለው ህግ ከአጠቃላይ ማህበራዊ-መዋቅሩ አንፃር ያለውን ጉዳይ መመዘንን ያስቀድማሉ። ሎክ ከአኩዊናስ አንፃር ሲታይ እጅግም የማይጨነቅ ይምሰል እንጂ ከቶሪዩ አንፃር ሲታይ ግን የተሻለ ጠንቃቃ ነው ማለት ይቻላል።

እነዚህ ሶስት አቋሞች በአለም ታሪክ ውስጥ የራሳቸው አስተዋፅኦ ከማድረጋቸው በተጨማሪ በዚህም ዘመን ተጠቃሽነት ያላቸው ናቸው። የአሜሪካ ቅኝ ገዢዎች ተቃውሞ የገጠመውን የእንግሊዝ ህግ ከጆን ሎክ አቋም ጋር ለማጣጣም ጥረት አድርገዋል። በአንፃሩ ደግሞ የነፃነት ጥያቄ በተነሳባቸው የየትኛውም ቋንቋ ደንጋጌዎች ውስጥ የተገናዘበ ተቃውሞን የሚፈቅደው የሎክ አመለካከት ግንባር ቀደም ተጠቃሽነት አለው። በአሜሪካን የፀረ-ባርነት ክርክርና ህግም ውስጥ እንዳስፈላጊነቱ እነዚህ ሶስት አቋሞች ጥቅም ላይ እንዲውሉ ተደርጓል።

## የሹክሹክታው ...

ከገፅ 5 የዞረ

ሚኒስትሩ ላይ ክስ ቢመሰርቱ እንኳ በታማኝነት በተገቢው የህግ አንቀፅ እውነተኛ ፍትህን ይሰጣል የሚባለው ፍርድ ቤት፤ ከጥፋታችን ጋር የማይገናኝ አንቀፅ ጠቅሶ ሲቀጣ በህግ አውጭው ላይ ብቻ ሳይሆን በህግ ተርጓሚውም ላይ እምነት ባንጥል በማን ይፈረዳል?

የሚመለከታችሁ ሀላፊዎችም ‹‹ባልተጣሰ አንቀፅ›› የመቅጣቱ ሁኔታ ምንአልባት በእኔ እና በአበበ ቀስቶ ብቻ የደረሰ ላይሆን ስለሚችል የዳኝነት አሰራሩን ደግማችሁ ደጋግማችሁ እንድትፈትሹት የሚያደርግ ነው ብዬ አስባለሁ።

መቼም የአጠፋሁት ጥፋት 449/2 ላይ የተጠቀሰው ሆኖ ሳለ ከዚህ የሚበልጥ የቅጣት መጠን ያለው አንቀፅ ተፈልጎ ባላጠፋሁበት አንቀፅ የተቀጣሁት ሆን ተብሎ ወይም በደካማ የህግ እውቀት የተመራ ዳኝነት ነው ብዬ ስለማላስብ ስህተቱ እንደሚታረም ተስፋ አደርጋለሁ። የዚህ ፅሁፋም አላማ ‹‹የቅጣት ውሳኔ የሚወስነው አጥፊውን ለማስተማር ነው›› በሚለው የፍትህ መርህ የተቀኘ መሆኑን በቀናነት ትረዱታላችሁ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ።

አሁን ደግሞ ወደ ሌላው አጀንዳችን እንሸጋገር ወደ ሹክሹክታው።

በአንድ ወቅት ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በፓርላማ ተገኝተው ተቃዋሚዎች በመንግስታቸው ላይ ህገ-ወጥ በሆነ መልኩ እያሴሩ እንደሆነ ገልፀው ‹‹መንግስት ማየት የተሳነው፣ መስማት የተሳነው›› አይደለም ብለው ነበር። በቅርቡም በዛው ፓርላማ የመምህራኖችን ተቃውሞ ሲያጣጥሉ ‹‹አመፁን የቀሰቀሱት አስተማሪዎች ከዚህ ቀደም ወላጆች እና መምህራኖች ብቃት የላቸውም፣ ስነምግባር የላቸውም አባሩልን ሲሉ አልሰማ ያልናቸው ናቸው›› አሉን። ይህን ከቅን እሳቤ ተነስተን እውነታቸውን ሊሆን ይችላል ብለን እናስብ (በግሌ ግን ፍፁም እውነት እንዳልሆነ እርግጠኛ ነኝ)

ነገር ግን ዜጎችን ሽብር ላይ የሚጥለው የጠቅላይ ሚኒስትሩ መንግስት ምን ጊዜም የሚሰማው ድምፅ ለስልጣናቸው የሚያሰጋውን ለይቶ ብቻ መሆኑን ያመላክታል። ባለፉት 21 የጭቆና አመታት እንዲህ የሚሉ የኢትዮጵያውያን ድምፆች ነበሩ፡- ‹‹…የመሬት ፖሊሲያችሁ ለህዝብ አይጠቅምምና ቀይሩት፣ የህገ-መንግስቱ አንቀፅ 39 ሀገሪቱን የሚበታትን ነውና አውጡት፣ የኤርትራና የአሰብ ጉዳይ የህዝብ እንጂ የፓርቲ ጉዳይ ስላልሆነ ብቻችሁን አትወስኑ፣ ምንም እንኳን አሸናፊዎች ብትሆኑም ከ50 አመት በላይ ሲገነባ የቆየውን የኢትዮጵያ ሰራዊት አትበትኑ፣ በሺዎች የሚቆጠሩ የቤተሰብ አስተዳዳሪዎችን ያቀፈውን ህንፃ ኮንስትራክሽን አታፍርሱ፣ በቋንቋ ላይ የተመሰረተው የፌዴራል ስርዓታችሁ ለአንድነታችን ፀር ነው፣ ከኤርትራ/ሻዕቢያ ጋር ያላችሁ ግንኙነት ከሌሎች ጐረቤት ሀገራት ጋር ባለን ግንኙነት መሰረት ይሁን፣ ምርጫ አታጭበርብሩ፣ የህግ የበላይነት ይስፈን፣ በተለያየ ጊዜ በጎዳና ላይ ለተገደሉ ዜጎች ተጠያቂው ለፍርድ ይቅረብ፣ የኢትዮጵያ ጦር ወደ ሱማሊያ አይዝመት፣ በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አትግቡ፣ ሀገሪቱን በሙሉ የፓርቲ አባል ለማድረግ የሚደረገው ሩጫ ጎጂ ነው፣ ኑሮ ተወደደ፣ የሸቀጦች ዋጋ አሻቀበ፣ ያልተጠና የዋጋ ማስተካከያ ከማረጋጋት ይልቅ ያባብሳል፣ ሃያ አንድ አመት አንድ ፓርቲ እና አንድ ሰው በስልጣን ላይ መቆየታቸው አምባገነንነት ነው….›› ወዘተረፈ ሰሚ ያላገኙ ወይም የባከኑ ድምፆች ናቸው።

እነሆ ዛሬ ዛሬ ከሞላ ጎደል እነዚህ ድምፆች ከሹኩሹክታ ያለፉ ቢሆኑም ማየት ያልተሳነው፣ መስማት ያልተሳነው መንግስት ማየትም መስማትም አልቻለም። ለዚህም ነው የቱኒዚያ ህዝባዊ ተቃውሞ ተቀስቅሶ ከተሳካ በኋላ የኢትዮጵያውያኖችን ቀለብ በፍጥነት ሊሰብ የቻለው። ይኸንንም ተከትሎ መሸቶ በነጋ ቁጥር ‹‹ሰላማዊ ለውጥ››ን ተስፋ ያደረጉ አንሾካሻኪዎች ድማፃቸውን ጎላ ማድረግ ጀመሩ።

በእርግጥም ሃያ አመት በከሸፈ ርዕዮተ-አለም፣ በጉልበተኛ ፓርቲ፣ በአምባገነን መሪ ስር መቆየቱ አሰልቺ ብቻ ሳይሆን አስከፊም ነው። ለዚህም ይመስለኛል የማንሾካሾኪያው የጊዜ ገደብ አልፎ ልክ እንደቱኒዚያዊው ጀግና ራስን በቤንዝን በማቃጠል ድምፅን በአሰቃቂ ሁኔታ ማሰማት ደረጃ ላይ የተደረሰው። ከወራት በፊት ከአዲስ አበባ በብዙ መቶ ኪሎ ሜትር በምትርቀው የዳውሮ ዞን መምህር የእኔሰው ገብሬ ‹‹ፍትህ የለም፣ ልማት የለም፣ ዴሞክራሲ የለም›› ሲል የዞኑ አስተዳደር ቅጥር ጊቢ ድረስ በመሄድ ራሱን በራሱ አቃጠለ። ሆኖም መንግስት የእኔሰውን የበላውን የእሳቱን ወላፈን ሊያየው አልቻለም፤ የሰቆቃና የስቃይ ድምፁንም ሊሰማው አልፈቀደም። ምንአልባት ዳውሮ ከአራት ኪሎ ቤተመንግስት ብዙ እርቀት ላይ ስለሚገኝ ይሆን ይሆናል። ይህን የሚያውቀው ‹‹መስማትና ማየት አልተሳነኝም›› የሚለው መንግስት ብቻ ነው።

ሰሞኑን ደግሞ ከአራት ኪሎ ቤተመንግስት አንድ ኪሎ ሜትር በማይሞላ ዕርቀት ላይ የሀገሪቱ እምብርት በሆነው የፒያሳ አደባባይ ዳዊት ለንዳሞ የተባለ የፌዴራል ፖሊስ አባል የነበረ ሰው ‹‹የምበላው አጣሁ፣ ኑሮ ተወደደ›› ሲል ራሱን በማቃጠል ድምፁ ይሰማ ዘንድ መስዋዕት ሆነ። መቼም ዳዊትን የበላው እሳት ወላፈንም ሆነ ጢስ ከቤተ መንግስቱ ቅጥር ሆኖ ላንጋጠጠ ማየት አይሳነውም። የግድ ቤተ መንግስቱ ውስጥ ገብቶ ካልተቃጠለ ‹‹አንሰማም፣ አናይም›› ካልተባለ በቀር።

የሆነ ሆኖ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ምላሽ መንግስታቸው የህዝን ብሶት እየሰማ ‹‹ጆሮ ዳባ…›› እንደሚል አረጋግጦልናል። ‹‹ወላጆች እና ተማሪዎች እነዚህ አስተማሪዎች (ያመፁትን ማለታቸው ነው) ችሎታና ስነ ምግባር የላቸውም ሲሉን ሰምተን ዝም ማለታችን ነው›› ብለውናልና። መቼም ይህ ብሶት ለአቶ መለስ ጆሮ በመድረስ የመጀመሪያው አይመስለኝም። የሌሎቹ ችግሮች ድምፅ እንደ መምህራኖቹ በተደራጀ ሁኔታ የስራ ማቆም አድማ በማድረግ ባለመታጀቡ ለመንግስቱ ስጋት አይደለም ብለው ይመስለኛል። አሊያማ ብንጮኽ፣ ብንጮኽ፣ ብንጮኽ… ‹‹አይሰማም›› ሲሉን የከረሙት አቶ መለስ ራሳቸው በአደባባይ ‹‹ሠምተን ዝም አልን›› ባላሉንም ነበር። ግና አሉን። የእምነት ቃላቸውን ሰጡን። የመልሳቸው መንፈስ የሰረፀው የመምህራኑ አድማ ቀጣይ ከሆነ ከሌሎች የሀገሪቱ ዘርፈ ብዙ ችግሮች ጋ ተደምሮ ‹‹ለመንግስቴ ጦስ ጥንቡሳስ›› ይሆናል ከሚል ስጋት ነው።

ምክንያቱም ሌላው ቢቀር ‹‹መምህራኖቹ ይባረሩልን›› ብሎ ወላጅ እና ተማሪው ከጠየቀ፣ የስነ ምግባርና የክህሎት ችግር ከነበረባቸው ለህዝብ የሚነገረው ከደሞዝ ጭማሪ ጋር የተያያዘ አገር አቀፍ አመፅ ሲያደርጉ ሳይሆን በወቅቱ ነው። ህግ ባለበት ሀገር እየኖርን ወንጀለኛ ከተበራከተ ‹‹መንግስት አልባ ወይም ህገ-መንግስት አልባ ናቸው እያልን ከምንሳለቅባቸው ሀገራት ከምን ተለየን?

በእርግጥ ኢህአዴግ ሃያ አንድ ዓመት ሙሉ መፍትሄ እንዲሰጥ ሲጠየቅ ለነበረው የህዝብ ችግር፤ እግር በእግር እየተከተለ ማስቀየሻ ሲፈጥርለት ነው ዛሬ ላይ የደረሰው። የመምህራኑ ጥያቄ ግን አንድም ድንገት ሆነበት፤ ሁለትም ከወትሮ የማስቀየሻ ስልቶች ገፍቶ ወጣ። እናም አዲስ ማስቀየሻ አልተበጀለትምና ጥሶ የመጣበት ቀዳዳ በርካታ የታፈኑ እውነታዎችን እንዲህ ዘርግፎ አወጣ።

እዚህች ጋ ግራ የሚያጋባው መምህራኖቹ ስነ ምግባር የጎደላቸውና ክህሎት የሌላቸው ከሆነ የጠቅላይ ሚኒስትሩ መንግስት በተዋረድ የሾማቸው ሀላፊዎች እንዴት መፍትሄ ሊሰጡት እንዳልቻሉ ነው። ምክንያቱም ከመምህሩ በላይ ዩኒት ሊደር፣ አስተዳደር እና ዳይሬክተር የሚገኙበት የበላይ መዋቅር አለ። ከእነዚህ አቅም በላይ ከሆነም የክፍለ ከተማው ትምህርት ቢሮ መፍትሄ መስጠት ነበረበት። ከእሱም አቅም በላይ ከሆነ የአዲስ አበባ ወይም የየክልሉ ትምህርት ቢሮ ኃላፊዎች አሉ። እነሱም ካልቻሉ ትምህርት ሚኒስትር ምን ይሰራል? ጠቅላይ ሚኒስትሩ ‹‹ሰምቼ ዝም አልኩ›› እስኪሉ ድረስ? ወይስ…

በአጠቃላይ ኢህአዴግን እስከምናውቀው ድረስ የመሬት ፖሊሲውን ለውጥ ‹‹በመቃብሬ ላይ ካልሆነ ወይ ፍንክች››፤ ህገ-መንግስቱ ይሻሻል ‹‹ሞቼ ነው ቆሜ›› ሲል ይሰጥ የነበረው ‹‹ተፈታታኝ›› ምላሽ በአዲስ ታሪክ እየተቀየረ ነው ወይስ አሁንም ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሰሙት ድምፅ በአድማ እና አመፅ የታጀበን ብቻ ነውን?... ይህ የእኔ ብቻ ጥያቄ አይመስለኝም።

ሹክሹክታዎችም ቀስ በቀስ ወደ አደባባይ ጩኸቶች የሚቀየሩት በሁለት ሁነቶች ተዛምዷዊ ክስተት ነው። የመጀመሪያው በቀስታ የሚያጉረመርሙት ሰዎች ቁጥር እየጨመረ መሄዱ ነው። ለሹክሹክታው መነሾ የሆኑት አምባገነንነት እና የኑሮ ውድነት እየገነገኑ መሄድ የሹክሹክታውን ተሳታፊዎች ቁጥር እየናረው ይሄዳል። የሹክሹክታው መስፋፋት ወደ አደባባይ ድምፅነት እንዲቀየር ግን አገዛዙን መሸከም ያንገፈገፋቸው ዜጎች ‹‹የእኛው መስቀል አደባባይ ከታህሪሩ አደባባይ ምን ያህል ይርቃል?›› የሚል ጥያቄ ሲያነሱ ሁለተኛው አስገዳጅ ምክንያት ይፈጠራል። የየእኔሰው ገብሬና የዳዊት ለንዳሞ ዘመነኞችም ከቡዓዚዝ ትውልድ በባሰ አምባገነንነትን የሚሸከም ትከሻ እንዴት ሊኖራቸው ይችላል? አቶ መለስ ሊሰሙት ባይፈቅዱም ትውልዱ ግን ወደ ታህሪር መመልከት ጀምሯል?

## መቼ ጉልበት ...

ከገፅ 4 የዞረ

ተሸንፎ በነበረበት ወቅት የነበረውን ሁኔታ በበቂ ማሳያ ላስቀምጠው እወዳለሁ። የተሃድሶው መስመር ፍሬ አፍርቶ ምልዓተ-ህዝቡን ተጠቃሚ ለማድረግ የቅድመ ዝግጅት ሥራውን በሚሰራበት ወቅት የተካሄደውን ምርጫ 97 ስናስታውስ ቅንጅት በአዲስ አበባ ማሸነፉን ተከትሎ ኢህአዴግ አስተዳደሩን ለማስረከብ ዝግጅቱን አጠናቅቆ ሲጠብቅ ለሰባት ወር ያሸነፈው ቅንጅት በሚገርም ሁኔታ መረከብ ባለመቻሉ የህዝብን ድምፅና በህግ የበላይነትን የሚያምነው ኢህአዴግ ቅንጅት ስላላስተዳደረ ላስተዳድር ብሎ አልገባም በዚህም አቋም በመፅናት አዲስ አበባ በባለአደራ አስተዳደር /a Caretaker administration/ እንድትመራ ሆነ።

እዚህ ጋር ዋናው ቁምነገር ኢህአዴግ የአዲስ አበባ ህዝብ በወቅቱ አልመረጠኝም ብሎ ቀጣ ወይስ ምን አደረገ የሚለውን በተጨባጭ መመልከት ነው፡ ፡ በዚህ ወቅት ብዙዎቹ ኢህአዴግ ይቀጣናል ብለው ሲያስቡ በፌደራሉ መንግስት አማካኝነት ግን ሁሉም የሠላም፣ የልማትና የዴሞክራሲ ፍሬዎችን ያለምንም መሸራረፍ ለህዝቡ በማድረግ ህዝባዊና ዴሞክራሲያዊ ድርጅት መሆኑን በተጨባጭ ያስመሰከረ ድርጅት ነው፡ ፡ ለኢህአዴግ የመረጠውና ያልመረጠው አንድና ያው ናቸው። ኢህአዴግ ያልመረጠውን ህዝብ የሚበቀል ድርጅት ሳይሆን ያልተመረጠበትን ምክንያት አጤኖ ከስህተቱ የሚማር ፤ ህዝቡ ስህተቱን እንዲነግረው መድረክ የሚፈጥር ህዝባዊ ድርጅት ሲሆን ይህም ከዴሞክራሲያዊ ባህሪው የሚመነጭ ነው።

ይህም በመሆኑ ነው አብዛኛው የሀገሪቱ የተማረ ሀይል በሚገኝበት አዲስ አበባ ከተማ የሚኖር ህዝብ ከሁለት ዓመት በኋላ በተደረገው ምርጫ የነፈገውን ካርድ ሙሉ በሙሉ መልሶ የሠጠው። ለዚህም ነው በምርጫ 2002ትም ከዚህ በፊት ታይቶ በማይታወቅ መልኩ ህዝቡ ኢህአዴግን የመረጠው።

3. “በአባላትና አባል ባልሆኑ መካከል ያለው ክፍፍል እንኳንስ የሚያስተሳስር የሚያቀባብር አይደለም” ተብሎ የቀረበውን ምን አልባት ፀሐፊው በመድብለ ፓርቲ ስርዓት ውስጥ ይቅርና በሃይማኖት እንኳ አባትና ልጅ፣ ባልና ሚስት፣ እናትና ልጅ፣ ጎረቤት ከጎረቤት እንዲሁም በሠራተኛው ሊኖር የሚችለው ዴሞክራሲያዊ ልዩነት በውል ሳይገነዘቡት ቀርተው አይመስለኝም። ግን ሁል ጊዜ እውነታውን ተናግሮ ታዳጊ የሆነውን የዴሞክራሲ ስርዓታችንን እናለማው በሚል መንፈስ ሳይሆን “የትኛው የቱን ያራግባል” በሚል አስተሳሰብ ይመስለኛል፡ ፡ ምን አልባት ፀሐፊው በገለፁት አግባብ የተፈጠረ ቅራኔ ካለ ፀሐፊው መፃፍ ያለባቸው የዴሞክራሲ ባህል ስር እየሰደደ ሲመጣ ሁሉም ሰው አንድ ዓይነት የፖለቲካ አመለካከት ሊኖረው እንደማይቻልና ቅራኔው ደግሞ ዳገት መውጣት የጀመረውን የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታን ቁልቁል የሚጎትት በመሆኑ መታረም አለበት ብሎ መፃፍ የነበረበት ይመስለኛል። ኢህአዴግ በሹመት ቦታም ሳይቀር አባል ያልሆኑ ሰዎችን በየደረጃው ከፌደራል እስከ ወረዳ ያስቀመጠ መሆኑን ስናይ የላቀ ውጤት ማስመዝገብን እንጂ አንዱን ዜጋ አባል ሌላውን አባል አይደለም ብሎ የሚከፍልም አለመሆኑን መገንዘብ ያሻል። የኢትዮጵያ ህዳሴን እውን ለማድረግ ብቃት ላይ ድርድር የሌለው ድርጅት ነው።

በሃገራችን አዲስ የልማት የመልካም አስተዳደር፣ የሰላም ምዕራፍ ጀምረን አቀበቱን በመውጣት ላለፉት ተከታታይ ስምንት ዓመታት ባለ ሁለት አሃዝ ዓመታዊ እድገት በማስመዝገብ በአፍሪካ ሶስተኛ የተባለውን በፍትሃዊነቱ ሁሉንም ተጠቃሚ ያደረገ እድገት ማስመዝገብ ችለናል። ለሠላምና ለመልካም አስተዳደር እምርታ ለማምጣት የተደረገው ትግል ብዙ እንድንጓዝ አስችሎናል። ይህም የአደባባይ ሚስጢር ነው። ከፊታችንም ዘርፈ ብዙ የፀረ-ድህነት ትግል የሚካሄድባቸው ሌትና ቀኖች ይገጥሙናል፤ በዚህም በተለይ በሃገራችን የተፈጠረውን ምቹ ሁኔታ በመጠቀም የላቀ ውጤት ማስመዝገብ ለድርድር አይቀርብም።

# ስለነፃነት ባህል ለመናገር ምክንያት የሆነን መፅሐፍ

የመፅሐፉ ርዕስ፡- የኢትዮጵያ ታሪክ፤ ኢጣልያ በኢትዮጵያ፣ ከወለወል እስከ ጎንደር፣ ግንቦት 1927 እስከ ህዳር 1934 ዓ.ም
ፀሐፊ፡- ተድላ ዘዩሀንስ
የገፅ ብዛት፡- 576

ነገ ሚያዝያ 27 ቀን 2004 የሰባ አንደኛውን ዓመት የነጻነት በዓል እናከብራለን፡፡ አምስቱ/ስድስቱ ዓመታት የጣልያን ይዞታ አገሪቱ በቅርብ ጊዜ ታሪኳ ከገጠሟት ቀውሶች አንዱ ሲሆን፤ የነጻነት በዓሉ ከቀውሱ የወጣችበትን ቀን የምታስብበት ከፍተኛ ሕዝባዊ በዓሏ ነው፡፡ ፖለቲካዊ መግፍኤ ኃሣብ በሚያንደረድረው ክርክርም ‹‹በትክክል አገሪቱ ነጻ የወጣችበት ቀን ሊባል የሚገባው መጋቢት 28(እንግሊዞች አዲስ አበባ የገቡበት) ቀን ነው፡፡›› ‹‹የለም ሚያዝያ 28 (ቀ.ኃ.ሥ አዲስ አበባ የገቡበት) ነው›› እየተባለም መንግሥታት በተቀያየሩ ቁጥር የክብረ በዓሉ ቀንም ሲለዋወጥ ቆይቷል፡፡ ደርግ የንጉሡ አስተዳደርን ክብር የነሳ መስሎት ቀኑን ሲቀይር፤ የሕወሓት/ኢህአዴግ አስተዳደርም ለንጉሡ ፍቅር ባይኖረውም ከደርጉ አስተዳደር ስለሚለየው ወደ ቀደመው ሲመልሰው አሁን ያለበት አድርሶታል፡፡ በተለይ አሁን ባለንበት ዘመን ማዕከላዊ ሥልጣን ላይ ያለው አካል የመንግሥትነት ሥልጣንን በመጨበጡ በዓሉን የማስከበር ጣጣ ውስጥ ቢገባም፤ ስለአገሪቱ ባለው ያልጠራ የታሪክ ትርጓሜ ክስተቱን ከልብ በመነጨ መልኩ የሚያወድሰው እንዳልሆነ ማስረጃ መጥቀስ አይከብድም፡፡ የዚህ ችግር ዋና መንስኤ ዶ/ር ዳኛቸው እንደሚሉት ሕወሓት/ኢህአዴግ ለመንግሥትነት ሥልጣኑ (ጎቨርንመንት) ቀናኢ፤ ስለ አገሪቱ (ዘ ስቴት) ግን ከግድ የለሽነት የዘለለ የአስተሳሰብ ተቃርኖ ያለበት መሆኑ ነው፡፡ የዓድዋ ድል በዓል በያመቱ ሲከበር ገዢው ቡድን በዓድዋ ድል ምክንያት ለ‹‹ቅኝ ግዛትነት›› ተዳርገናል ብለው ከሚማረሩት እና የነጻነት በዓል ሲከበር በአንጻራዊነት በአምስቱ ዓመታት አግኝተን የነበረውን ‹‹ነጻነት›› አጥተናል ብለው ከሚቆጩት ‹‹አጋሮቹ›› ጋር ያለው ትዳር የዚህ ግርምቢጥ አካሄዱ ማሳያ ነው፡፡ ለጊዜው በሥልጣን ላይ ያለው ቡድን ያነገበው መሣሪያውና የፈጠረው ቀመር እስከሠራለትና ሥልጣን ላይ እስከቆየ ድረስ እነዚህ ቅኝ ገዢና ተገዢ ብሎ የፈረጃቸውን ‹‹ሕዝቦች›› (ከኤርትራ ውጪ) አንድ ላይ ለማስተዳደር ከመታተር አይቦዝንም፡፡ ስለዚህም እንዲህ ዓይነቱን በዓላት አንድ ላይ ‹‹እንዲያከብሩ›› ሲጥር ይስተዋላል፡፡ ቡድኑ ከሥልጣኑ ቢወገድ ግን ምን ሊያደርግ እንደሚችል ለመናገር አንዳች ማስተማማኛ ሊኖረው የሚችል ሰው ያለ አይመስልም፡፡ በቅኝ ግዛትነት ነው ወደኢትዮጵያ የተቀላቀልነው የሚሉትና በአጋርነትም በአባልነትም ከዚሁ ቡድን ጋር ሥልጣን በመጋራታቸው ጥያቄዎቻቸውን ያዘገዩት ወገኖች ልሂቃንም ‹‹ቅኝ ገዢዬ›› በሚሉት ማዕቀፍ ውስጥ ለመካተት መፍቀዳቸው ግርምቢጣዊነትም አቋማቸው ሲጀመርም ሥልጣንን በመቋመጥ ላይ የተመሰረተ መሆኑን ያጋልጥባቸዋል፡፡ አሳሳቢው ነገር ደግሞ ልሒቃኑ የተጠቀሰውን ሥልጣን ቢያጡ ወዴት እንደሚሄዱ ለመገመት አስቸጋሪ መሆኑ ነው፡፡

### የመጽሐፉ አወቃቀር

በያዝነው ዓመት የታተመው ይህ መጽሐፉ 63 ምዕራፎች፣ 18 ፎቶዎች፣ 1 ቅጂ ሰነድ፣ 6 ሰንጠረዥ መረጃ፣ 4/5 አባሪ የተባሉ መጣጥፎችና መረጃዎች ያሉት ባለ 576 ገጽ ዳጎስ ያለ መጽሐፍ ነው፡፡ ይዘቱም ጣሊያን ኢትዮጵያን ለመያዝ ሰበብ ለመፍጠር ከቃጣችበት ከወልወል ግጭት አንስቶ የመጨረሻው የጣሊያን ጦር ሽንፈት እስከተመዘገበበት የጎንደር ፍልሚያ የሚያትት ነው፡፡ በተለይ ስለአርበኝነት ዘመኑ ከፍተኛ ሽፋን ሰጥቷል፡፡ እንደ ዳራም የጣሊያን ታሪክ ቅምሻን ከውህደት አንስቶ የኢትዮጵያን ከአድዋ ጀምሮ የሚፈነጥቅ ሲሆን፤ ከጦርነቱ ፍጻሜ በኂላ ስለነበሩ የመባቻ ሁነቶችም የጸሐፊውን አስተያየቶችና ምልከታም አካቷል፡፡

መጽሐፉ በአወቃቀር መጠነኛ መስተካከል ቢደረግበት ይመረጥ ነበር፡፡ አንዱ መንገድ ከስልሳ (ያውም በርካታዎቹ ሦስትና አራት ገጽ ብቻ የያዙ) በላይ ምዕራፍ ከማብዛት በክፍል አዋቅሮ ለየክፍሉ አካታች ርዕስ በመስጠት አላስፈላጊ ምዕራፎችን በአያሌው በመቀነስ ነው፡፡ ጸሐፊው በመደበኛው ውጊያ፣ በአርበኝነቱና በስደተኛው ዙሪያ የሚያጠነጥኑ ርዕሰ ጉዳዮችን እየመዘዙ ለትረካቸው ደርዝ ለማስያዝ ያደረጉት ጥረትም ስለዘመኑ ከተለያየ አቅጣጫ ለመመልከት የሚረዳ በመሆኑ እሰየው የሚያስብል ነው፡፡ ነገር ግን ይህን ሲያደርጉ የሚፈጠሩ ችግሮችን (ድግግሞሽ፣ አጠቃላይ ድምዳሜና ብዙ ማለት በማይችሉባቸውም አቅጣጫዎች ሳይቀር አዲስ ንዑስ ርዕሶችን መክፈት) ለመቆጣጠር ሳይቻላቸው ቀርቷል፡፡

ርዕሰ ጉዳዩ የቅርብ ጊዜ ክስተት በመሆኑ፣ ክስተቱ በአገሪቱ ታሪክ ውስጥ ባለው ቦታ፣ በእርሱ ምክንያት የተፈጠረ አነጋጋሪ ፖለቲካዊ ትርክትና በመሳሰሉት ምክንያቶች ስለ ጉዳዩ በጠቅላላውና ከርሱ ጋር በተያያዙ ንዑስ ጉዳዮች ላይ በማተኮር ብዙ መጻሕፍት በአገርቤት ተጽፎበታል፡፡ በተመሳሳይ ከጣሊያኑም ወገን በርካታ መጻሕፍት የተጻፈ ሲሆን፤ ከነዚሁ መጻሕፍትም ወደ አገርኛው ቋንቋ የተተረጎሙና እነዚህኑ መጻሕፍት እንደምንጭ የተጠቀሙ መጻሕፍት አሉ፡፡ የሕትመት ብርሃን ለማየት ባይታደሉም በርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ አካዳሚያዊ የታሪክ ምሁራንም የሠሯቸው ጥቂት ሥራዎችም አሉ፡፡ በሕይወት ተሞክሯቸው በዚህ ዘመን ያለፉ ባለታሪክ ኢትዮጵያውያንም በሕይወታቸው የማይዘነጋ አሻራ ያሳረፈባቸው ክስተት በመሆኑ በተለያየ ደረጃ ስለዘመኑ አትተዋል፡፡ የብዙዎችን ሕይወት የነካ እንደመሆኑ መጠን ርዕሰ ጉዳዩ ለተጻራሪ ትርጉሞችና ትንተናዎች የተጋለጠ መሆኑ አልቀረም፡፡

### የጸሐፊው አቀራረብ

ጸሐፊው ለሚያቀርቧቸው ትንተናዎችና አስተያየቶች የግድ ቀደምትነት ባያስጣቸውም አንዳንድ የተለዩ አቀራረቦችን አጠንክረው የገፉበት ስለመሆኑ መጽሐፋቸው ዋቤ ነው፡፡ የጸሐፊው የትንተና አቅጣጫ ከመጽሐፉ ርዕስ ጀምሮ የታየ ሲሆን፤ በዚህም በተለምዶ የጣሊያን በኢትዮጵያ ቆይታ አምስት ዓመታት ነው የሚለውን ለማረም ባሰበ መልኩ ከግንቦት 1927 - ህዳር 1934 ዓ.ም. በመውሰድ ወደ ሰባት ዓመታት በማስጠጋት 1928 እና 1933 (ጣሊያንም ሆነ ንጉሡ/እንግሊዞች በድል አድራጊነት አዲስ አበባ የገቡበት)ዓ.ም. የታሪኩ ማዕከል እንጂ መጀመሪያም ሆነ መቋጫ እንዳይደሉ ያስረግጣል፡፡ ስለመጽሐፉ ርዕስ ከተነሳም ርዕሶች በክፍልፋይ እንዲኖሩት መደረጉ (‹‹የኢትዮጵያ ታሪክ፤ ኢጣሊያ በኢትዮጵያ፣ ከወልወል እስከ ጎንደር፣ ግንቦት 1927- ህዳር 1934 ዓ.ም.››በሚል) የተንዛዛ/የተራዘመ እንዲሆን አስገድዶታል፡፡ በዝርዝር ይዘቱም ስለኢትዮጵያውያኑ ተጋድሎ በዋናነት ለሚተርከው ለዚህ መጽሐፍም ‹‹ኢጣሊያ በኢትዮጵያ›› የሚለው ርዕስ ተገቢነትም ማጠያየቁ አይቀርም፡፡ ስለጦርነቱ ባቀረቡት ዘገባ የጎንደር ውዝግብ ያለውን ቦታ ማስመራቸው፣ የወልወል ግጭትን ለሁለተኛው የዓለም ጦርነትም አይቀሬነት ምልክት አድርገው መውሰዳቸው፣ የልጅ እያሱን ልጅ መልአከ ጸሐይን ንጉሠ ነገሥትነት ቅቡልነት በተጠቀሰው ማዕረግ በመጥራት ማስረገጣቸውና የመሳሰሉት የጸሐፊው ለየት ያሉ ትንተናዎችን አቅጣጫ ጠቋሚ አድርገን ልንወስዳቸው እንችላለን፡፡ በቋንቋውም አልፎ አልፎ የሚታየው ለዛም የራሱ መልክ አለው፡፡

### ከመጽሐፉ ምን እንጠብቅ?

እንደመጽሐፉ ዳጎስ ያለ መሆን፤ ሌሎቹን መጻሕፍትና መጣጥፍ ለማንበብ ለታደለ አንባቢ የሚጨምርለት አዲስ ዕውቀት ውሱን ሊሆንበት ይችላል፡፡ በእርግጥ በተዘዋዋሪ የሚያውቀውን ተረክ እንዲደግመው የሆነ ቢመስለውም፤ ስለርዕሰ ጉዳዩ በተበታተነ መልኩ በተለያዩ መጻሕፍት የተነሱ ዝርዝሮችን በአንድ ላይ ተጨምቀው እንዲያገኝ የሚረዳው መሆኑን መካድ አይችልም፡፡ ስለዚህ ጸሐፊው ይህንን ለማድረግ በእጅጉ እንደተጉም ይረዳበታል፡፡ ይህንንም የመጽሐፉ ዋንኛ ፋይዳ ተደርጎ በመውሰድ ስለጦርነቱ የተጻፉ መጻሕፍትን/መጣጥፎችን አግኝተው ለማንበብ ለማይችሉት በተለይ ያለው ጠቀሜታ እጅግ የጎላ መሆኑን መመስከር ይቻላል፡፡ በአገሪቱ የተለያዩ ቦታዎች ስለተካሄዱት የአርበኝነት እንቅስቃሴ፣ ስለሚሸፍኑት ቦታ (በትግራይ፣ በጎንደር፣ በጎጃም፣ በባሌ በሐረርጌ፣ በሲዳሞ፣ በሸዋ፣ በወሎ፣በጋሞ ጎፋና ሌሎችም ቦታዎች) በብሔራዊ ደረጃ የተካሄዱ የአርበኝነት እንቅስቃሴዎችና ዋና ዋና ተዋናዮች በአንድ ጊዜ ለማወቅ ለሚፈልግ ከመነሻ በላይ የሆነ መረጃ ሊያገኝበት ይችላል ማለት ነው፡፡ ይህም ጸሐፊውንም ሆነ አሣታሚውን ባለውለታ ያደርጋቸዋል፡፡ መጽሐፉ ያለውን ዋጋ ሳንዘነጋ ጸሐፊው ስለራሳቸው ግለታሪክ ቢጽፉ ከዚህ ሥራቸው የበለጠና አዲስ ሕዝባዊ ዕውቀት የሚገነባ ትሩፋት ጀባ ይሉን እንደነበር ለመመስከር እገደዳለሁ፡፡

በዚሁ በቀረበልንም ከጉዳዩ ስፋት የተነሳ በሁሉም ቦታ የነበረው የአርበኝነት እንቅስቃሴ እኩል ተሸፍኗል ማለት አይቻልም፡፡ ለምሳሌ የሸዋው ሰፊ (ያውም አምስት በሚደርስ ምዕራፎች) ትኩረት ያገኘ ሲሆን ከአንድ ገጽ ብዙም በማይበልጥ መልኩ ‹‹የተሸፈኑም›› አሉ፡፡ (በነገራችን ላይ ‹‹ቀሪን ገረመው›› የተሰኘው የታደሰ ዘወልዴ መጽሐፍ በ1950ዎቹ 500 የሚጠጋ ገጽ ያለው ስለ ሸዋ የሚያትት መጽሐፍ መጻፋቸውን ልብ እንበል) በአንጻሩ በዛሬው መጽሐፍ በአንዳንድ አካባቢ ዝርዝሩ መሳሳቱ አንድም እንቅስቃሴው ይህ ነው የሚባልባቸው አይደሉም፡፡ አሊያም ጸሐፊው በቂ ምንጭ ማግኘት አልቻሉም፡፡ በመሰረቱ ቅኝ ገዢዎችን ለመቋቋም የተደረገውን ተጋድሎና የተከፈለውን መስዋዕትነት ያህል ከቅኝ ገዢዎች ጋር ተወላጆች የሚያደርጉት መተባበር እንደ አፍሪካ ባሉ የቅኝ ግዛት ታሪክ ባለባቸው አህጉራት በተደጋገሚ የተስተዋለ ነው፡፡ ተወላጆች ለሁለቱም መልሶቻቸው በርካታና የተወሳሰቡ ምክንያቶች ሊኖሯቸው ይችላል፡፡ በእኛው አገርም የተወላጆች ሁለቱም ምላሽ እንደመሰል አፍሪካውያን ወገኖች በተዛመደም በተለየም ሁኔታ ተከስቷል፡፡ በመጽሐፉ እንደወረዱ ከቀረቡት ትረካዎች (እንመን ወይስ እንሽፍት ብለው የያካባቢው ሰዎች ውይይት) የመጨረሻው አቋማቸውን በቀሊል ከሃዲነትና ጀግንነት ለመተርጎም ከባድ እንደሚያደርገው እንረዳለን፡፡ ስለጦርነቱ፣ አርበኝነቱና ተጋድሎው ከነጻነት በኂላ በሰፊው የተተረከው የአገር ፍቅርን ለመገንባት ያለመ በመሆኑ በክስተቱ ዙሪያ የሚኖረው ትርጉም ላይ የራሱን አሻራ እንደሚያሳርፍ ይጠበቃል፡፡ በየዘመኑ የሆነውን ሁሉ በዚያው ዘመን መነጽር ለማየት ለሚቸገር ለእንደእኛ ዓይነት ማኅበረሰብ ይሄን ከማድረግ የተሸለ አማራጭ መኖሩ ያጠራጥራል፡፡ በዚህ መጽሐፍ የቀረበው ተጋድሎውን ብሔራዊ ጠገግ የመስጠት ጥረትም የዚሁ ‹‹ቅን›› ጥረት ክትያ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡

የንጉሡ ጀግንነት/ሽሽት፣ ከጣሊያኖች ጋር ያበሩ ኢትዮጵያውያን አገር ከሃዲነት/ለድርጊታቸው አስገዳጅ ምክንያት የሆነ ነገር ስለመኖሩ፣ የአብርሃና ሞገስ እንቅስቃሴ ዓላማ፣ ጦሩ ተሸንፎ ወደኂላ ሲመለስ በተለያዩ አካባቢዎች የገጠሙት ዝርፊያና ዕልቂት፣ የስደተኞች፣ የአርበኞችና ከጣሊያን ጋር ያበሩ(ባንዳ/ከሃዲዎች) ስለኢትዮጵያ ይገባናል የሚሉት ጥያቄዎችና የመሳሰሉት ሁሉ ለትርጉሙ ልዩነት ማጠንጠኛ ናቸው፡፡ ይህም በመሆኑ ስለጉዳዩ ብዙ የተጻፈውን ያህል የተለጠጡ ትርጉሞች፣ የተድበሰበሱ ትረካዎችና የተጨቆኑ እውነታዎች ሞልተውበታል፡፡ በዛሬው መጽሐፍ ግን ጸሐፊው ከክስተቱ በጊዜ በራቁበት ሁኔታ ለማዘጋጀትና እንደገና ለመመልከት በመቻላቸው ማለት ይቻላል፤ በብዙ መጻሕፍት ከሚስተዋለው በከፍተኛ የስሜት ተጋቦት ከመዘፈቅ ለመዳን ሳይረዳቸው አልቀረም፡፡ ይህ ሲባል ግን ከጣሊያን ጋር ያበሩትን ‹‹አንተ›› (ራስ ኃይሉ ተክለ ሃይማኖት፣ አቡነ አብርሃም ወዘተ…) በአርበኝነት የዘለቁትን ደግሞ ‹‹አንቱ›› በማለት አልፎ አልፎም ቢሆን የብስጭታቸውን ስሜት ምልክት ማሳየታቸው አልቀረም፡፡ ጸሐፊው በልጅነት ዕድሜያቸው ለማየትና ለመሳተፍ እድሉን ያገኙባቸውን አጋጣሚዎች በመንተራስ ‹‹እዚህ ጋር ልመሰክር ይገባኛል›› እያሉ የሚገቡበት አጋጣሚ መብዛቱም የስሜት መቀላቀልን ሊያስከትል እንደሚችል ያሰጋል፡፡

ጸሐፊው ለመረጃቸው እንደምንጭነት የተጠቀሟቸው ዋንኛ ምንጮች ሕትመቶች ሲሆኑ፤ የቃል መረጃ የሰጧቸው እማኞችም አሏቸው፡፡ ይህንን መዘርዘራቸው የሚያስመሰግናቸው ሲሆን፤ የዋቤ መጻሕፍቱ ዝርዝር (የአማርኛው) ሥርዓት ያልጠበቀና የተዘበራረቀ መሆኑ ግን ተገቢ አይደለም፡፡ በይዘቱ ውስጥ የማጣቀሻው 13 ቁጥሮች ተቀምጠው የምንጩ ስም ሙሉ ለሙሉ ያልተካተተለት ምዕራፍ 63ን ጨምሮ ሌሎች ዝንጋኤዎችም ታይተዋል፡፡ በመጽሐፉ አባሪ ተብሎ ከገጽ 535-564 የተያያዙት ነገሮችም አባሪ ለመሆን የማይበቁ ይልቅስ ከውስጣቸው እየመረጡ በቦታው እንደ አስፈላጊነቱ ከዋናው ይዘት ጋር ተሰናስለው ሊቀርቡ የሚችሉ ጸሐፊው ከተለያዩ ምንጮች የቃረሟቸው መረጃዎችና በራሳቸው አጻጻፍ ያቀረቧቸው አስተያየቶች ናቸው፡፡ ይህ ቢደረግ የተጋነነውን የመጽሐፉን ገጽም ለመቀነስ ይረዳ ነበር፡፡ የምስሎቹ ጥራት ጉድለት ከሌሎች ብዙ በአገራችን የሚታተሙ መጻሕፍት ጋር የሚጋሩት ችግር ቢሆንም፤ በቀላሉ ሊቀረፉ የሚችሉ የአርትኦት ችግሮቹን ግን መዝለል አይቻልም፡፡ ለዚህም አሣታሚው ማንኩሳ ኃ/የ/ግ/ማ ወደዚህ ሥራ መግባቱ በዘርፉ ያለውን ክፍተት በአቅሙ ለመድፈን የሚረዳ አስተዋጽኦ ነውና እያደነቅን የአሳታሚነት ‹‹ፍዳ››ን ለመሸከምም ትከሻውን ማዘጋጀት እንዳለበት ማመልከት ግድ ይሆናል፡፡



በብርሀኑ ደቦጭ
(የታሪክ ተመራማሪ)

በመጨረሻም የዕለቱን በዓል አስመልክተን ለመነጋገር ምክንያት የሆኑንን ጸሐፊ እያመሰገንን ግለታሪካቸውን እንዲበረቱበት እንመክራለን፡፡ የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች ማኅበር ኃላፊዎችም (ልብ ይደረግ ሌሎች አባቶቻችንን አላልሁም፡፡) እንደ ካድሬ የዘመኑ ፖለቲካ መጠቀሚያ ከሚሆኑ የተመሠረቱበትን መሰረታዊ ምክንያት ለሆነው የቀደመው ትውልድ ውጣ ውረድ መታወሻ የሚሆኑ ሙዚዬሞችና መታሰቢያ ኤግዚቢሽኖች (የነጻነት ተጋድሎውን ያካተተ) ለማደራጀት ቢተጉ ቀጣዩ ትውልድ ከልቡ እያስታወሳቸው ሲኮራና ሲደመም ይኖራል፡፡



# የኢትዮ- ኤርትራ ግንኙነት ከኢሳያስ በኋላስ. . . .?



**በሙሉነህ አያሌው**
muleayalew@yahoo.com

ኢትዮጵያ አንዴ በመረጋጋት ሌላ ጊዜም እርስ በርስ በሚነሱ የምስራቅ አፍሪካ አገራት ግጭቶች ምክንያት ለዘመናት ስትታመስ ኖራለች:: ምንም እንኳን ለዘመናት የቆየና የተሻገረ የድህነት ታሪክ ቢኖራትም በወታደራዊ ጥንካሬዋና በአገር ማንነት ጉዳይ የነበራት የማያወላዳ አቋም፣ ጥንካሬ እና እምነት መገለጫዎቿ ናቸው::

የወታደራዊ አቅሟንም የውስጥ ደህንነቷን ለመጠበቅ ብቻ አልተጠቀመችም:: የደህንነት ስጋቶችን ቀድሞም ቢሆን ለመከላከል ሲባል ጦሯን ወደ ጎረቤት አገራት ሁሉ በመላክ ሥጋቶቹን እዛው በተነሱበት አካባቢ በማቆም የውስጥ ደህንነቷን በተደጋጋሚ ለማስጠበቅ ጥራለች:: እኒህ ድርጊቶቿ በነዚህ ረጅም ጊዜያት ሁሉ አገራችን በአለም አቀፉ ማህበረሰብ ዘንድ ክብርንና ሞገስን አትርፈውላታል::

ኢትዮጵያ በአካባቢው ላይ ያላት ጥንካሬ ሁሌም ቢሆን በአለም አቀፉ ማህበረሰብ ዘንድ ተፈላጊ ነው:: ለዚህ ጥቅም ሲባል በተደጋጋሚ በአገራችን የሚነሱ አምባገነን መሪዎችን የአለም አቀፉ ማህበረሰብ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ድጋፋቸውን ከመስጠት ሲቆጠቡ የማናየው:: ለዚህ ፖለቲካ ድጋፍ ተንታኞቹ የሚያስቀምጧቸው ምክንያቶች አሉ:: ውስጣዊ እና ውጫዊ ብለን በሁለት ከፍለን ልናያቸው እንችላለን::

**ውስጣዊው ምክንያት**:- አገሪቷ በውስጧ የተለያዩ የብሔር ብሔረሰብ ቡድኖችን ይዛለች:: የእነዚህ ብሔር ወካይ ነን የሚሉ ‹‹መሪዎች›› በተለያዩ አጋጣሚዎች የብሔሮቹን ጥያቄዎች ባለው የፖለቲካ ስርዓት አገዛዝ ባህሪ ምክንያት መብቶቻቸው ተጥሰው እንዳሉ የሚያምኑ ያኮረፉ ቡድኖች ስብስብ ሆነዋል:: በእንዲህ አይነት ቅራኔ፣ በገገርና ተገገር መንፈስ፣ በጨቋኝና ተጨቋኝ የታሪክ ድምዳሜ ምክንያት አገሪቷ በቀጣይ ሊነሱ በሚችሉ ግርግሮች ሳቢያ ልትታመስ ትችላለች የሚለው አንዱ ስጋት ነው:: ይህ አለመረጋጋት ዞሮ ዞሮ አገሪቷን ወዳልተፈለገ ውጤት ሊያደርሳት ይችላል የሚለው አለም አቀፋዊ መግባባት ምክንያት የአገሪቷን አንድነት ለማስጠበቅ ሲባል በጉልበትም ይሁን በውዴታ በደንብ ቀጥቅጦ ለሚገዛ መሪ ድጋፍ መሰጠት አለበት የሚለው አንደኛው ምክንያት ነው::

**ውጫዊው ምክንያት**:- የኢትዮጵያ አለመረጋጋት በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ውጤቱ አገሪቷን ከበው በሚገኙ የቀንዱ አገራት ላይ ይንፀባረቃል:: የቀንዱ አገራት ‹‹እንዲያውም ዘንቦብሽ.....›› እንደሚባለው አይነት ናቸውና የግድ አንድ ልዕለ ኃያል አገር ቀጠናው ያስፈልገዋል የሚል አቋም አላቸው:: የቀንዱ አካባቢ አገራትን ችግር ለመፍታት የኢትዮጵያ ሰላምና መረጋጋት የግድ ነው::

ከእነዚህ ሁሉ አለም አቀፍ ድጋፍና እርዳታ ጀርባ የኤርትራ መንግስትን የሚያበሳጩ ብዙ ምክንያቶች ሊኖሩ እንደሚችሉ ይታወቃል::የኤርትራ መንግስት ኢትዮጵያ በተለያዩ የአለም መንግስታት ፊት ያገኘችውን ክብርና ሞገስ፣ ወታደራዊ የበላይነት መጋራት ቢፈልጉም አልተሳካላቸውም:: ስለዚህ ያላቸው አማራጭ የኢትዮጵያ ውስጣዊውም ውጫዊውም ሰላም የማስከበር ተልዕኮ ለማጨናገፍ የቻሉትን ያህል መታተር የኢሳያስ መንግስት የውጭ ግንኙነት ስትራቴጂ አካል ከሆነ ሰነባብቷል:: ብዙዎቹም የኢሳያስ መንግስት ፍፃሜ እልባት ካልተሰጠው በስተቀር ጉዳዩ ማባሪያ እንደሌለው ግንዛቤያቸውን ሲያሰፍሩ ቆይተዋል:: ጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊም የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ በኤርትራ ላይ የነበረውን አቋም ሙሉ ለሙሉ መቀየሩን ይፋ አድርጓል:: የኢሳያስ መንግስትን ለመጣል ከሚንቀሳቀሱ ኃይሎች ጋር በመተባበር የሚያስፈልገውን ሁሉ ለማድረግ ቃል ገብቷል:: ለዚህ አንዱ ማሳያ የሆነው የኢሳያስ መንግስት ተቃዋሚዎችን እዚሁ ኢትዮጵያ ውስጥ ማደራጀትና መርዳት በመንግስት ደረጃ የተያዘ አቋም መሆኑ ነው::

## የኢሳያስ ቀለበቶች…

በአገራት የደህንነት ጉዳይ ላይ ጥናት ያደረጉ አብዛኞቹ ምሁራን የኢትዮጵያ ደህንነት ስጋት ናቸው የሚሏቸውን ዋና ዋና ነጥቦች በሶስት ማዕቀፍ ውስጥ ማየት እንደሚቻል ይናገራሉ::የኢትዮጵያ መንግስትም እነዚህን የደህንነት ስጋቶች እንደሚጋራ በውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤቱ በኩል ይፋ የሚያደርጋቸው ወረቀቶች ለዚህ ማሳያ ናቸው:: እነዚህን ስጋቶች ሶስቱ ቀለበቶች ይሏቸዋል:: በእነዚህ ሦስቱ የደህነት ሥጋት ቀለበቶች ውስጥ የኢሳያስ እጅ በቀጥታ ይታያል::

### የውጭ ቀለበት /Outer Ring/

የውጭው ቀለበት ሥጋት ተብሎ የሚጠራው አካባቢ ኢትዮጵያ ከምትገኝበት የአፍሪካ ቀንድ ክልል ውጭ ያሉ አገራትን የሚመለከት ነው:: እነዚህ ከቀንዱ ውጭ ያሉ አገራት ከኢትዮጵያ ጋር ቀጥተኛ የሆነ የድንበር መጋራት የሌላቸው ቢሆንም ኢትዮጵያ ላይ ባላቸው የጥቅም ፍላጐት አንፃር አይናቸውን ከኢትዮጵያ እንዳያነሱ ያደርጋቸዋል:: በዚህ ክፍል ውስጥ የሚመደቡት ግብፅ እና የአረብ ባህረሰላጤ አካባቢ ያሉ አገራት ናቸው::

ለግብፆች አባይ የህይወት እና የሞት ጉዳይ ነው::ግብፆች በአባይ ላይ ያላቸው ስጋት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ እየመጣ ነው:: የመጀመሪያው ምክንያት ግብፆች እራሳቸው በውሃው ላይ የመጠቀም ፍላጐታቸው በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ መምጣቱ ነው::እ.ኤ.አ. በ1955 ከተፈረመው የአባይ ውሃ አጠቃቀም ስምምነት በላይ ግብፃውያን ውሃ መፈለጋቸው ሲሆን ሁለተኛው ምክንያት የተፋሰሱ አገራት ቀድሞ የነበረውን ስምምነት ለመቀበል አለመፍቀዳቸው እና በውሃው ላይ የመጠቀም አዝማሚያ ማሳየታቸው እንቅልፍ የሚነሳ ጉዳይ ሆኖባቸዋል:: ለዚህ ሁሉ ስጋት ምክንያት የሆነችው አገር ደግሞ በዋናነት ኢትዮጵያ ናት:: ስለዚህ የግብፅ መንግስት በቀጥታ በኢትዮጵያ ላይ አደጋ የማድረስ እድሉን ባያገኝም በቅርብ ያሉትን የኢትዮጵያ ጠላት አገራት በመጠቀም ፖሊሲዋን ልታስፈፅም እንደምትችል ታምናለች:: ፕሬዝዳንት ኢሳያስ ለዚህ የሚመቹ ናቸው:: በተደጋጋሚም በአባይ ላይ በሚደረጉ ስምምነቶች የኢሳያስ መንግስት ሰልፉን ከግብፅ ጋር አድርጓል:: ማናቸውም አባይን በሚመለከት ግብፅ በምታራምደው አቋም ጐን ለጐን ቢያንስ የኢሳያስ ድጋፍ አላት:: በፖለቲካው መድረክ የኢሳያስ አመራር ከመንበሩ ገለል ማለት ለኢትዮጵያ ከግብፅ ሊቃጣ ይችል የነበረውን ስጋት ለመቀነስ አስተዋፅኦ ይኖረዋል::

በአረቡ ባህረ ሰላጤ አካባቢ የሚኖሩ አንዳንድ አገራት የአፍሪካ ቀንድ የፖለቲካ ብቻም ሳይሆን የሃይማኖት ርዕዮት አለም ማራመጃ እንዲሆን ይፈልጋሉ:: ፖለቲካውን እና ሃይማኖቱን በአንድነት አስተሳስሮ ለመቀጠል ያቀዱትን ስትራቴጂ አዳጋች የሚሆንባቸው ኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ ነው:: ሱዳን፣ ሶማሊያ (ሶስቱንም ግንጣዮች ጨምሮ)፣ ጅቡቲ… ሁሉም ሙስሊም አገራት ናቸው:: ኤርትራም በበኩሏ በአረብ ሊግ ውስጥ የሙሉ አባልነት ስልጣን ባይኖራትም በታዛቢነት የምትሳተፍበትን መብት አግኝታለች:: የሃይማኖቱን በፖለቲካ መድረክ ለማስረፅ የኤርትራ መንግስት አዳጋች እንደማይሆን እነርሱም ያውቁታል:: በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ የሚንቀሳቀሱ አክራሪ ቡድኖች ዋነኛው አላማቸው በምስራቅ አፍሪካ በአጠቃላይ እስላማዊ መንግስት(Islamic state) እንዲመሰረት ማድረግ ነው:: ይህንን ፖሊሲ ለማስፈፀም ከፍተኛው ድጋፍ የሚገኘው በነዳጅ ዘይት ከበለፀጉ ሀብታም አገራት ነው:: ኤርትራም ከእነዚህ አገራት ከሚገኝ የገንዘብ እርዳታ ድጐማ ተቋዳሽ ናት:: በቀጣይ በሃይማኖት አክራሪነት ምክንያት ሊነሱ የሚችሉ ስጋቶችን ለመቀነስ ሲባል የኢሳያስ መንግስት በስፍራው አለመኖር ጠቃሚ ነው::

### የመካከለኛው ቀለበት (Middle Ring)

በመካከለኛው ቀለበት ውስጥ ከሚካተቱ የደህንነት ስጋቶች መካከል በቀጥታ ከኢትዮጵያ ጋር ድንበር የሚዋሰኑ አገራትን ይመለከታል:: ኢትዮጵያ በአፍሪካ ቀንድ ከሚገኙ ከሁሉም አገራት ጋር ድንበር ትጋራለች:: እነዚህ ድንበር ከምትጋራቸው አገራት መካከል በአንፃራዊነት የኤርትራ መንግስት እና የሶማሊያ ታጣቂ ቡድኖች (አንዴ መንግስት ሲሆኑ ሌላጊዜም ሲባረሩ) ከሌሎቹ አገራት በበለጠ የስጋት ምንጮች ናቸው:: ሁለቱንም በአንድ አይነት የደህነት ስጋት መመደብ ባይቻልም ሁለቱም በኢትዮጵያ ላይ በሚያራምዱት አቋም ምክንያት የአላማ ተመጋጋቢነት አላቸው::

እነዚህ ጐረቤት አገራት ከውጫዊው ቀለበት ስጋት ይልቅ ለአገር ደህንነት ስጋት የሚሆኑበት ምክንያት አንዱ ለአገራችን ያላቸው ቅርበት ነው:: የድንበር ቅርበታቸው የተለያዩ አደጋዎችን እንዲጥሉ፣ ውጤቱም ወዲያው እንዲታይ ምክንያት ያደርገዋል:: እነዚህ ቅርብ አገራት በኢትዮጵያ ላይ በተለያየ መልኩ አደጋን በመጣል በቀጣይም የደህንነት ስጋት ሆነው ሊቀጥሉ የሚችሉባቸው ብዙ ማስረጃዎች አሉ:: የጐረቤት አገራት የቅርብ ደህንነት ስጋት ይሆናሉ ከሚባሉባቸው ምክንያቶች መካከል ቀጥታ ወታደራዊ ወረራ እና ማተራመስ፣ ሌሎች ጥቃት መፈፀም የሚፈልጉ ታጣቂ ቡድኖችን ወይም አገራትን በመርዳት በተዘዋዋሪ አገሪቷን ማዳከም (Proxy war)፣ የከተማ ውስጥ ሽብር… የመሳሰሉት ተጠቃሽ ናቸው:: በተለይ አሁን ካለው ነባራዊ ሁኔታ አንፃር የኤርትራ መንግስት ሁሉንም የቅርብ ደህንነት ስጋቶች አንድ በአንድ በኢትዮጵያ ላይ ሞክሯል:: የኢትዮጵያ ውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤትም የኤርትራን መንግስት ስጋት ከነዚህ ምክንያቶች አንፃር ነው የሚመለከታቸው:: የኤርትራ መንግስት በኢትዮጵያ ላይ በሚያራምደው የ‹‹ማተራመስ ፖሊሲ›› ጋር በተያያዘ ብዙ ግለሰቦች በእስር በመማቀቅ ላይ ይገኛሉ:: (ተባብረው ይሁንም አሁንም ገና በፍርድ ቤት የሚጣራ ጉዳይ ሆኖ ማለት ነው)::

ስለዚህ የኢትዮጵያ መንግስትም ይሁን ህዝብ የኤርትራን መንግስት በሚመለከት ተጋርጦብናል ተብሎ የሚታሰበውን የደህንነት ስጋት እልባት ለመስጠት ይቻል ዘንድ የኢሳያስ መንግስትን ማስወገድ የመጨረሻው መፍትሄ ነው::

### የውስጥ ቀለበት (Internal Ring)

የሶስተኛው የደህንነት ስጋት ተደርጎ የሚወሰደው በድንበር አካባቢ የሚነሱ ግጭቶች እና አለመግባባቶች አንዱ ሲሆን ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚነሳው ሌላው ጉዳይ ድንበር አካባቢ የሚነሱ የታጣቂ ቡድኖች እንቅስቃሴ ናቸው:: እነዚህ ግጭቶች መሰረታቸውን የሚያደርጉት በሁለት ጎረቤት አገራት መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን ታከው የሚነሱ መሆናቸው ነው:: ለኢትዮጵያ በዚህ ረገድ ከኤርትራ ጋር ያልተመለሱላት የድንበር ማካለል ጥያቄዎች አሏት:: በሁለቱን አገራት መካከል እስከአሁንም ድረስ ያለውን ያልተረጋጋ ግንኙነት (No peace No war)፤ የድንበር ማካለሉ እርምጃ ድጋሚ ይቀሰቅሰዋል የሚባለው የጦርነት ስጋት ነው:: የኢትዮጵያ መንግስት ከሌሎች የቀንዱ አገራት ጋር የድንበር ይገባኛል ጥያቄ የለበትም (ሙሉ በሙሉ ማለት ባይቻልም):: ከኤርትራ መንግስት ጋር በተፈጠረው የግዛት ይገባኛል ጥያቄ የኤርትራ መንግስት አቋሙን እስካልቀየረ ድረስ ስጋቱ አብሮ የሚዘልቅ ነው:: መደራደር፣ መወያየት በኢሳያስ አገዛዝ ጊዜ የሚታሰብ አይደለም:: ስለዚህ ኢሳያስ በስልጣን እስካለድረስ ችግሮቹ ያለ መፍትሄ አብረው ይዘልቃሉ::

ከላይ ከተጠቀሱት የደህንነት ስጋቶች አንፃር ካየነው አብዛኛው ስጋት የሚያተኩረው በኢሳያስ አስተዳደር ላይ ነው:: ሱዳን በራሷ በውስጥ ጉዳይ ተወጥራለች፣ ጅቡቲ የደህንነት ስጋት ተደርጋ እስከአሁን አልተቀመጠችም፣ ሶማሊያ አንፃራዊ በሚባል መልኩ በአሁኑ ጊዜ የአፍሪካ ህብረት ጦር በቦታው መገኘቱና የሶማሊያ ሽግግር መንግስት በመንበሩ መደላደል መጀመሩ፣ በአሸባሪነት የተፈረጀው አልሸባብ መዳከሙ ስጋቱን እያደበዘዘው ይገኛል:: ኬንያ ወዳጅ የምትባል አገር ስትሆን ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር የግጭት ተሞክሮ የላትም (ምን አልባት በግልገል ጊቤ ሶስት ፕሮጀክት እና በኦሞ ወንዝ አጠቃቀም ዙሪያ ወደፊት አለመግባባቶች እስካልተፈጠሩ ድረስ):: ስለዚህ የኢትዮጵያ መንግስት የአገሪቷን ደህንነት ስጋት ለመቀነስ አትኩሮቱን ማድረግ ያለበት በኤርትራ ላይ ነው::

የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት በተደጋጋሚ ጊዜ በሁለቱ አገራት መካከል የተፈጠሩ አለመግባባቶች ብሎም ጦርነቶች በሁለቱ አገራት ወንድማማች ህዝቦች መካከል የቆየውን ወዳጅነት እንደማይመለከት ተናግረዋል:: ኢትዮጵያ ከኤርትራ የሚሰደዱ ዜጐችን ተቀብላ በመጠለያ ከማቆየት ጀምሮ ኢትዮጵያውያን ዜጐች ሁሉ ያላገኙትን በየዩኒቨርስቲው በነፃ የመማርን እድል አመቻችቶላቸዋል:: የግጭቶቹ ምክንያት የሚመለከተው አስመራ ውስጥ ያለውን አምባገነን አመራር እንጂ በሁለቱን አገራት የሚኖሩ ህዝቦች እንዳልሆነ መንግስት በተደጋጋሚ መግለጫ ሰጥቶበታል::

ኤርትራ አሁን ያለችበት ፖለቲካ ግርግር እንደ ከዚህ ቀደሙ አይደለም:: ኤርትራ የምትባል አገርን ከመሰረቱ ሀሳቡን አምጥቸው ነፃ አገር ያደረጓትን ታላቁ መሪዋን ኢሳያስ አፈወርቂ አልጋ ላይ ጥላለች:: ሙሉ ለሙሉ የአገሪቱ የፖለቲካ አቅጣጫ በእኚህ ግለሰብ እጅ እንደሆነ ይታወቃል:: ይህ የማንም አምባገነን አገር መሪ መለያ ባህሪ ነው:: በሁሉም አምባገነን አገራት ውስጥ አድራጊና ፈጣሪ ከአናቱ ተፈናጦ የተቀመጠው ግለሰብ ነው:: የኛም አገር ፖለቲካ ተሞክሮ ይሄው ነው::

አሁን ያለው ዋናው ጉዳይ ኢሳያስ አፈወርቂ አገሪቷን በንቃት መምራት በማይችሉበት ደረጃ ላይ ነው ያሉት:: የኢትዮጵያ መንግስት የደህንነት ስጋት የነበረውም እኚህ ግለሰብ የማይጨበጥ ተለዋዋጭ ባህሪ የሚንፀባረቅባቸው ፖሊሲዎች በሚወጡ ትእዛዞች ሳቢያ መሆኑ ተነግሯል:: የግብፅ፣ የአረብ አገራት፣ የሶማሊያ፣ የተለያዩ ታጣቂ ቡድኖች፣ የድንበር ግጭት፣ ጦርነት፣ የህዝብ ስደት፣ አሸባሪነት… የመሳሰሉት ስጋቶች ሁሉ ተባባሪ ተደርገው የሚወሰዱት ፕሬዝዳንት ኢሳያስ የአልጋ ቁራኛ ሆነዋል:: ጥያቄው እርሳቸው ቢሞቱ (አንዳንዶቹ ሞተዋል ብለው እንደዘገቡት) ኢትዮጵያ ይህንን አመራር ሊቆጣጠር በሚችለው አመራር ላይ በቀጥታ እጇን ማስገባት አለባት የሚል እምነት አለኝ:: እስከ አሁን በመንግስት ይፋ ባይደረግም ከኢሳያስ ውድቀት በኋላ የሁለቱ አገራት ግንኙነት በምን አይነት መንገድ መቀጠል ይገባዋል በሚለው ዙሪያ የኢትዮጵያ መንግስት ጥርት ያለ ፖሊሲ ማዘጋጀት ይጠበቅበታል::

### ድህረ-ኢሳያስ

የፕሬዘዳንት ኢሳያስ አፈወርቂን በጠና መታመም የተለያዩ የዜና አውታሮች ተቀባብለው የዘገቡት ሲሆን በቀጣይ የአገሪቱን የመንግስት ስልጣን ሊረከቡ የሚችሉ ዋና ዋና ቡድኖችን ከወዲሁ መገመት ለቀጣይ በሁለቱ አገራት መካከል ለሚኖረው ጤናማ ግንኙነት መሰረት ይሆናል:: አሁን ካላቸው ቀረቤታ አንፃር የቀድሞ ታጋዮች በበላይነት የሚቆጣጠሩት ወታደራዊ ክፍሉ መንበረ ስልጣኑን ከሚረከቡት ውስጥ የመጀመሪያው ተሰላፊ መሆኑ አይቀሬ ነው:: ወታደራዊ ክፍሉ እንደተገመተው ስልጣን የሚጨብጥ ከሆነ በኢሳያስ ጊዜ የነበረውን ስርዓት እንዳለ እንዲቀጥል ማድረጉ የማይቀር ይሆናል:: ለኢሳያስ መንግስት ካላቸው ታማኝነት እና ኤርትራን እንደ አገር በማስቀጠል ላይ ባላቸው ተመሳሳይ አቋም ምክንያት ሥርዓቱ እንደነበረ እንዲቀጥል ማድረጋቸው አይቀሬ ነው:: ይህ አካሄድ ለኢትዮጵያ የቀደሙትን ስጋቶች እንደነበር ያደርገዋል::

ሁለተኛው ተተኪ ሊሆኑ ይችላሉ ብለን ልንገምት የምንችላቸው በኢትዮጵያ መንግስት የሚደገፉት የኢሳያስ መንግስት የተቃዋሚ ኃይሎች ናቸው:: እነዚህ ኃይሎች በአገራችን ቀጥተኛ ድጋፍ እየታገዙ የኤርትራን ጦር ኃይል በመደምሰስ አስመራ ሰተት ብለው ሊገቡ የሚችሉበት እድልም ይኖራል::

ሶስተኛው ተተኪ ሊሆኑ የሚችሉት ኃይሎች ኑሯቸውን በተለያዩ ምዕራብ አለም አገራት በስደት ያደረጉ የኤርትራ ልሂቃን ህብረት ይመለከታል:: እነዚህ ቡድኖች በጋራ በመሆን በቀጣዩ የኤርትራ ህልውና ላይ ወሳኝ ለመሆን የተለያዩ ኃያላን አገራትን ድጋፍ በእጅጉ ያሻሉ:: የኢትዮጵያ መንግስትም እነዚህን የአማራጭ ኃይሎች በሚገባ አጥንቶ በቀጣይ ሊደረግ በሚችለው መተካካት ዙሪያ የራሱን አቋም ሊያንፀባርቅ ይገባል::

በተለይ ከመጨረሻ ሁለቱ አማራጭ ኃይሎች ጋር የሚያደርገው አዎንታዊ ግንኙነት ወደፊት ከአገሪቱ ጋር የሚኖረውን የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ቀላል ያደርግለታል::

የኤርትራ መንግስት ውድቀት ሲታሰብ ኢትዮጵያ የምትቀርፀው ፖሊሲ ሁለት ነገሮችን ታሳቢ ማድረግ ይጠበቅበታል:: የመጀመሪያው እስከ አሁን ድረስ በኢሳያስ አቀነባባሪነት ምክንያት በኢትዮጵያ ላይ የተጋረጡትን የደህንነት ጥያቄዎች እና ስጋቶች ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እልባት የሚያገኙበትን ዘዴዎች መቀየስ የሚገባው ሲሆን፤ በሁለተኛ ደረጃ መታየት ያለበት ኢትዮጵያዊያኖቹ በተደጋጋሚ የሚያነሷቸው የይገባኛል ጥያቄዎችም እንዴት መፈታት እንዳለባቸው የመፍትሄ አቅጣጫዎችን ማመላከት ይጠበቅበታል::

በተለይ የድንበር ጥያቄ፣ የወደብ አጠቃቀም መብት ዙሪያ የሚነሱ ቅራኔዎች፣ የተለያዩ ታጣቂ ቡድኖችን የኤርትራ መንግስት ከሚያደርገው እርዳታ እንዴት መታቀብ እንደሚገባው፣ በሁለቱ ህዝቦች እና መንግስታት መካከል ዘላቂ የሆነ መግባባት ላይ ለመድረስ የሚገባቸውን ነጥቦች፣ የኢትዮጵያ ንብረት የሆኑ እና ኤርትራ ስትገነጠል በኤርትራ መንግስት የተወረሱ ንብረቶች ዙሪያ፣ የዜጐች ኃብትና ንብረት በጦርነት ሳቢያ ሲፈናቀሉ የደረሰባቸውን ውድመት በሚመለከት… በአጠቃላይ ሁለቱ አገራት ቀድሞ ወደነበሩበት የወንድማማች ህብረት የሚገቡበትን ዝርዝር ፖሊሲዎች መንደፍ ከኢትዮጵያ መንግስት የሚጠበቁ ጉዳዮች ናቸው::

ከኢሳያስ አፈወርቂ በኋላ በሚመሰረተው መንግስት ላይ ከማንም አገራት ቀድማ ኢትዮጵያ፣ ቀጥተኛ ጣልቃገብነት ማድረግ ካልቻለች ተመልሶ ወደነበርንበት የደህንነት ስጋት መዘፈቃችን አይቀሬ ነው:: የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ከአሁኑ ዝግጅቱን ማጠንከር ይጠበቅበታል::

ፕ/ር በረከት ኃብተስላሴ “Wounded Nation” በሚለው መፅሐፋቸው ላይ ኤርትራውያንን አስመልክተው አንድ ወሳኝ የጋራ እውነት ፅፈዋል::

‹‹አብዛኞቹ ኤርትራውያን የጋራ የሆነ አንድ መግባቢያ ቋንቋ አላቸው:: እንደምናያቸው ስርዓቱን በሚደግፉ እና በሚቃወሙ መካከል መከፋፈል ቢኖርም በአገር ጉዳይ ግን ተመሳሳይ አቋም አላቸው:: ሁሉም እናት አገራቸውን በጣም ይወዳሉ:: ለዚህም ነው ዲያስፖራ ኤርትራውያንም ይሁኑ የሳዋ ማሰልጠኛ ካምፕን ለቀው ድንበር አቋርጠው በረሃ የገቡትም ቢሆን የኢሳያስን መንግስት መቃወምም ይሁን ስርአቱ እንዲለወጥ የመጠየቅ አንዳችም አዝማሚያ የማያሳዩት›› ይላሉ:: ኤርትራውያንን በሚመለከት የሚወሰዱት የአማራጭ መፍትሄዎች ሁሉ ጥንቃቄን ይሻሉ::

# ኦ! አምላክ ሆይ ስለምን ተውኸን?



አናንያ ሶሪ
anania20006@yahoo.com

‹‹…እንደሚመስለኝ፡- ደጋግመህ ያየኸው የህልም ጤፍ የህዝባችን ምልክት ይመስለኛል። ጤፍ ማለት ህዝብ ማለት ነው። ጐተራው ደግሞ ሀገር ማለት ነው ልጄ። በየቦታው ቡድሽ እያለ የሚታየው የጐተራው ቀዳዳ ደግሞ የአገሪቷ ሊያዝ ሊጨበጥ የማይችል፤ አንዱን ቀዳዳ ስትደፍነው በጐን ሌላው ብቅ፣ ያኛውን ቀዳዳ ሩጠህ ስትደፍነው ሌሎች ቀዳዳዎች ከግራም ከቀኝም ቡድሽ እያለ አቅመ-ቢስ ያደረገህ ተስፋ ያስቆረጠህ ሲሆን፤ የሚፈሰው ደሞ በጤፍ ተመስሎ ህዝቡ፤ የምትቀደው መጽሐፍ ማለት እየቆራረጥህ የጐተራውን ቀዳዳ የምትደፍነው-ያው የቀሰምኸው ትምህርት ማለት ነው ልጄ! እንደሚመስለኝ፡- …እ… በአንተ አይምሮ በህልም ደረጃ ሌት-ተቀን ሲያቃዥህ የምገነዘበው የህልም ምስጢር ቢኖር ትምህርትህን ከሁኔታው ጋር ስታመጣጥነው፤ ጥቅመ-ቢስ ሆኖ አግኝተኸዋል መሰለኝ።››

አንበርብር ተበሳጭቶ እና አዝኖ ቁሱን ከተቀመጡበት ትቷቸው ብድግ ብሎ ይሄዳል።

* * *

ከላይ የተጠቀሰው ንግግር ‹ጤዛ› በተሰኘ የፐ/ር ኃይሌ ገሪማ ፊልም ላይ የአንድ የሃይማኖት አባት ለህልም-ፍቺ ወደርሳቸው ዘንድ ለመጣው፤ አንበርብር ለተሰኘ ገፀ-ባህርይ ህልሙን/ቅዠቱን ሲፈቱ የተናገሩት ነው። አላሚው-አንበርብር ሌት በህልሙ፡- በቤታቸው ያለ የእህል ጐተራ ከውስጥ ሲበሳና የያዘው ጤፍ በቀዳዳው አፈትልኮ ወደውጪ ሲዘንብ፤ ያንን ቀዳዳ ሊደፍን ከመጽሐፉ ላይ ገፆች እየቀደደ ሲሞላ፤ በሌላ ጐን ሌላ ቀዳዳ ቡትርፍ እያለ ጤፉ እንደ ጋላቢ ጅረት ሽምጥ ሲፈስ፤ ሌሎች ብዙ ቀዳዳዎች ሲፈጠሩና ያንን ከሚያህል ግዙፍ ጐተራ የሚዘንበው የጤፍ ዶፍ የአንበርብርን ጥረት መና አድርጐ እስከአንገቱ ድረስ ጢም አርጐ ሲሞላው እና ለህይወቱም አደጋ ሲሆንበት ከመቅጽበት ከህልመ-እንቅልፍ ባንኖ ወደኚሁ የሃይማኖት አባት ሄዶ የተረከው መሆኑ ነው። የሆነው ሁሉ የሆነበት ወቅት ደግሞ፡- የደርግ ስርዓት በገነገነበት እና አገሪቱ በእርስ-በርስ ጦርነት በምትታመስበት በዚያ የጥፋት-ዘመን ነው።

ዛሬስ በአገር የተመሰለው ጐተራችን እንዴት ነው? በየማዕዘናቱ ያሉ ዙሪያ-ገቦቹ ሁሉ በሚገባ የተለሰኑ እና ቀዳዳ የሌላቸው፤ የሁሉም ሰብሳቢ መሆን የሚችል ጠንካራ ምሽግ ነው? ውስጣችን ገብተው ከሚበሉን አጥፊዎችስ ያስጥለናል?

በጤፍ የተመሰልነው እኛስ በምድር ላይ እንደጨው ዘር ሳንበተን ስብስብ ክትት ብለን እየኖርን ነው? ጐተራው ውስጥ ያለነውስ በነቀዝ ከመበላት ተርፈናል? …ይህንን ሁሉ ባሰብሁና ባሰላሰልሁ ጊዜ ትካዜ ገባኝ። ቀስ በቀስ እያለም ልቤ ሲሻክርና አይኔ እንባ-ሲያቀር ተሰማኝ። እፍኝ የማይሞሉ ሲባሉ እንደአሸን የፈሉ የአገራችን ችግሮችና ችግርተኞች ፊቴ ድቅን አሉና ሆዴን አስባሱኝ። አልቅስ አልቅስ፣ ጩኽ ጩኽ አለኝ። በአገሩ መሬትም በባዕዳን ምድርም መሰደድ እና መሳደድ ዕድል-ፈንታው የሆነው የወገኔ የእንግልት ኑሮ ህይወቴን ትርጉም አሳጣው። ባዶነት ተሰማኝ። ኦና ሆንኩ!

**እህህ… እስከመቼ… እህህ???**

ከየትኛው እንደምጀምር አላውቅም። ከየቱም ብጀምር ግን ሁሉም እህህ… አለበት። አዎ-ህልቆ መሳፍርቶች ርቦናል፣ እዕላፋት ታፍነናል፣ ሚሊዮኖች ተሰደዋል፣ ለቁጥር የሚታክቱም ወህኒ ናቸው። አሊያም ሞተዋል። አያሌዎችም በነገ ላይ ያላቸው ተስፋ ተሟጧል። ከእንግዲህስ ተስፋችን ማነው?

በአገሪቱ ማዕዘናት ሁሉ መልካም ዜና አይሰማም። ከጋምቤላ እስከአፋር፣ ከቤንችማጂ እስከአርሲ፣ ከኦጋዴን እስከዋልድባ፣ ከቤኒሻንጉል እስከ ባድመ የግድያ፣ የዕገታ፣ የመፈናቀል እና የጦርነት ዜናዎች ዛሬም እየጐረፉ ነው። የጐተራው ቀዳዳዎች እየበዙ ነው። መንግስት ደግሞ በአተርፍ ባይ አጉዳይ አላዋቂ አያያዝ ችግሮቹን ከቁጥጥር ውጪ እንዲወጡ እያደረገ ነው። በዚህ ሁሉ ላይ ደግሞ መምህራን እና አያሌ የመንግስት ሠራተኞች በተባባሰው የኑሮ ውድነት የተነሳ ከእጅ-ወደ-አፍ በሆነ ኑሮ በሞትና በሽረት መሃል በጣዕር-እስትንፋሳቸው ያዘግማሉ። እነርሱም ይርባቸዋል።

‹‹ደመወዙን የተቀበለ ሰው በቀዳዳ ከረጢት ያደርገው ዘንድ ደመወዙን ተቀበለ›› እንዲል መጽሐፉ፡- ብዙዎቻችን በኑሯችን በረከትና መቅኖ አጥተናል። ልጆቻቸውን የሚያበሉት ያጡ ወላጆች ወደልመናና ደጅ-ጥናት እየተገፉ በሰው ፊት መለብለብ ግድ ሆኖባቸዋል። እናቶች የልጆቻቸው ከትምህርት የመምጫ ሰዓት ደረሰ ብለው እየተሳቀቁ ነው-የሚያቀርቡላቸው ቁራሽ እንጀራ በቤቱ ጠፍቷልና።

ዳቦ፣ ዘይት፣ እና ስኳር ብርቅ የሆነበት ቤተሰብ ተቆጥሮ አይዘለቅም። ጉጆዎቻቸውን ዘግተው በረሃብ የሚረግፉ፣ ጧሪ ቀባሪ የሌላቸው አቅመ-ደካሞች በየመንገዱ ዳር ከተገነቡት የሚያማምሩ ህንፃዎች ጀርባ ተከልለው ወደሞት እየተነዱ ነው። ዕምነ-ርሃብ ይሄይስ ኩይናት! (ከረሃብ ጦርነት ይሻላል!) እንዲሉ አበው፤ አረጋውያን በፀጥታ ተሰቃይተው እየሞቱ ነው። በየመንገዱ ጥጋ-ጥግ በግራና በቀኝ የወዳደቁት አዛውንት እናቶች እና አባቶች ሰብሳቢ አጥተው ሲለምኑ ማየት መፈጠርን ያስጠላል። በየቤተክርስቲያኑ እና መስጂዱ ደጃፍ ኑሯቸውን የመሰረቱትም፤ የእኛን ምፅዋት በተስፋ እየተጠባበቁ እድሜያቸውን ይገፋሉ። ብዙዎች የሚላስ የሚቀመስ የላቸውም። በዋና ዋና አውራ-ጎዳናዎች አካፋይ ላይ እና በታወቁ አደባባዮች ዙሪያ በጠራራ ፀሐይ በደረታቸው ተዘርግተው የሚተኙ የጐዳና ተዳዳሪዎች መዲናችንን የረሃብ አሊያም የጦርነት ቀጠና አስመስለዋታል።

በሽተኛ ወይም አረጋዊ ሳንሆን በየቤቱ የምንገኝ ወጣት ገመምተኞች እጃችንን አጣጥፈን ያለስራ ተቀምጠናል። ልክ ህፃናት መዋያ እንደተበጀላቸው ሁሉ እኛም የአዋቂ-መዋያ ‘ተቀይሶልን’ በየጫት ቤቱ እንገኛለን። ግን ለምን? ለምን? ለምን? ጥላሁን ግዛው ለምን ለምን ሞተ? ማርታ ለምን ለምን ሞተች? የኔሰው ገብሬ ለምን ለምን ሞተ? ዳዊት ለንዳሞ ለምን ለምን ሞተ? ለቀረነው የዚህ ዓይነት ‘ህይወት’ ለመተው ነው? ይሄስ ‘ህይወት’ ለመባል የሚበቃ ነውን? መተንፈስና ቆሞ መሄድ ብቻ ‘ህይወት’ ሊባል ይችላል?

ቀኑ ለአይን ያዝ ማድረግ ከመጀመሩ፡- በየተዘጉ ደጃፎች ፊት የሚኰለኰሉ ህፃናት ሴተኛ-አዳሪዎች ቁጥር በየለቱ እየጨመረ ነው። ለአቅመ-ትዳር የደረሱ ሄዋኖችም ገላቸውን አራቁተው ለሽያጭ ቀርበዋል። የልጆቻችን እናቶች ሊሆኑ የሚገቡትን ቆነጃጅት በገንዘባችን ልንገዛቸው የምንችላቸው ሸቀጦች ሲሆኑ ማየት ምንኛ ያሰቅቃል?

በየአረብ አገራቱ ያሉ እህቶቻችን ስቃይም እዚህ ካሉቱ ቢከፋ እንጂ አያንስም። በሊባኖስ የኢትዮጵያ ቆንስላ ፊት-ለፊት በአሰሪዋ እንደአስከሬን እየተጐተተች እና እየተደበደበች ያየናት ዓለም ደቻሳ፡ - ኢትዮጵያዊነት በዓለም ህዝቦች ፊት የወደቀበትን እና የተዋረደበትን ደረጃ በግልፅ አሳይቶናል። በዚሁ በሊባኖስ ከጥቂት ወራት በፊት፡-ኢትዮጵያውያኖች ከነአየር መንገዳችን ጭምር ትቢያ ሆነን ቀርተናል። መንግስት እንደሌላቸው ህዝቦች፡- ማንም እያጠቃን፣ እያዋረደን፣ እየገደለን ያለአንዳች ፍትህ ለመኖር ወይም ለመሞት ተፈርዶብናል። በኩራት፡- አገራችን ኢትዮጵያ ነው! ስንል፤ ለካ አገራችን የኢትዮጵያ ምድር ነው። እሱም ስንሞት የምንቀበርበት ብቻ። እሱንም ካደለን! ከዚያ ወዲያ ኢትዮጵያችን ለኛ አይደለችም።

እንደ አገር-አልባ ወፍ-ዘራሾች ካገር አገር እና ከስፍራ-ስፍራ የሚባረሩ ኢትዮጵያውያኖች አሁንም ስደታቸው አላባራም። ከጉራፈርዳ የሚፈናቀሉ ወገኖቻችን ዛሬም እየተንገላቱ ነው።

በአፋር ጐንደር እና ትግራይ የሚኖሩ ሰላማዊ ሰዎች ባልታወቁ አካላት ታፍነው እየተወሰዱ ነው። ይህም የዕገታ እና ሰዎችን የመሰወር እኩይ ድርጊት ከለት-ወደ-ለት እየተለመደ እና የቀን-ተቀን ህይወት አንዱ አካል ወደመሆን እየተሸጋገረ ነው። በጋምቤላ ክልልም በቅርቡ የተገደሉ ሰዎች ሁኔታ የሚያሳየው ነገር ቢኖር በአካባቢው ሰላም እንዳልሰፈነ ነው። ከወራት በፊት በአሰቃቂ ሁኔታ በአውቶብስ ተሳፍረው ሲሄዱ የተገደሉ ተማሪዎች ሁኔታም በክልሉ አንዳች ችግር ለመኖሩ አመላካች ነው። መገዳደሉ አልበርድ ያለበት ምክንያትም የሚያሳየው በስፍራው ሥረ-መሰረቱ ያልተዳሰሰ እና ያልተለየ መነሾ መኖሩን ነው።

በአርሲ አሳሳ በተባለ ቦታም ሰዎች እንደተገደሉ እየሰማን ነው። መንግስትም በራሱ

ወደ ገፅ 10 ዞሯል

# የአዲስ አበባ ምርጫና የኢህአዴግ ሩጫ

ዳንኤል ተፈራ

አዲስ አበባ ቅልጥ ያለች የፖለቲካ ከተማ ናት። ለሌሎች የሀገሪቱ የክልል ከተሞች የደም ስር ብቻ ሳትሆን ልብ ናት። አዲስ አበባ ከሌሎች የኢትዮጵያ ከተሞች ጋር ያላት ተዛምዶ የአፍንጫና የአይን ዓይነት ነው። አፍንጫ የሆነችው አዲስ አበባ ስትመታ አይን የሆኑት ክልሎች ያለቅሳሉ። ያውም ስቅስቅ ብለው።

አዲስ አበባ የፖለቲካ ከተማ ሆና ፖለቲካ መፈትፈት ከተጀመረባት እነሆ 125 ዓመት ሆናት። ታዲያ የፖለቲካ ከተማነቷ ሞገሷን የጨመረውን ያህል አበሳዋን እንድትበላም ዳርጓታል። አፍ አውጥታ ብትነግረን ኖሮ ስንት ጊዜ እንዳነባች እናውቅላት ነበር። በቡትቶ (የጨርቅ) ኳስ እየቦረቁ ያደጉ ልጆቿ በዚሁ ፖለቲካ የተነሳ ጐዳናዎቿ ላይ ድፍት ብለዋል። በቀደመው የመንግስቱ አገዛዝ የቀይና ነጭ ሽብር እብደቶችን እየቆዘመች አይታለች። ምን የሄ ብቻ! ኧረ በንጉሱም ዘመን የጣሊያን ወረራን ተከትሎ ግራዚያኒ ዲስኩር ሲያሰማ አብርሃም ደቦጭና ሞገስ አስገዶም ለምን ቦንብ ወረወሩ ተብሎ ድፍን የአዲስ አበባ ፏሪን ከከተማዋ ገድለው በመጨረስ ለማጥፋት ሞክረው ሲደክማቸው አይደል እንዴ የተዉት። አዲስ አበባ በልጆቿ ትጨክን ይመስል፤ ጐዳናዎቿ የደም ግብር የለመዱ ይመስል ስታነባ ኖራለች። በ‹‹ነፃ-አውጭው›› ኢህአዴግ አገዛዝም ቢሆን የ1997 ምርጫን ተከትሎ የበርካታ ወጣቶች ደም ኮለል እያለ እንደ ውሃ በየጐዳናው ወርዷል።

ይሄ ግን ለምን ሆነ? ያልን እንደሆነ መልሱ ቀላል ነው። አዲስ አበባ የፖለቲካ ከተማ ስለሆነች ነው። ሸገር ልብ ናት። ልቧን በፍቅር የማረከ ጀግና መሪ ግን እስካሁን አላገኘችም። አዲስ አበባን በጉልበቱ እጇን ጠምዝዞ አንገቷን ያስደፋ እንጅ በጀግንነቱ ማርኮ በፍቅር ያንበረከካት ስርዓት አልተፈጠረም። አምሮቷ ያ ቢሆንም በጉልበት እይተሸነፈች አንገቷን ስትደፋና፤ እንደ ክረምት ፀሀይ ፈገግታዋ ብልጭ ድርግም ሲል መመልከት የተለመደ ነው። ፖለቲከኞች ሁሉ የአዲስ አበባን ልብ ይፈልጋሉ። ልቧን ለማግኘት ይራኮታሉ። ጉልበተኛውም እንደ ገጠር ሙሽራ ሽፋፍኖ ሊወስዳት ይከጅላል። ሁሉም ፖለቲከኞች የአዲስ አበባን ልብ ማግኘት የኢትዮጵያን የመክፈቻ ቁልፍ በአንገት እንደማንጠልጠል በመሆኑ ‹‹አዲስ አበባን ከሌሎች ከተሞች ሁሉ ከልብ ይሰሟታል›› ብለው ያምናሉ።

አዲስ አበባ ግን ጥርሷን እንጅ ልቧን ሰጥታ አታውቅም። ይሄን የምታደርገው ንፉግ ስለሆነች አይደለም። ንፉግነቱንማ አታውቀውም። ጥርሷን ብልጭ የምታደርግላቸው ጉልበተኞች ስለሆኑ ብቻ ነው። ሸገር ጉልበተኛ አይመቻትም። በዚህ የተነሳም በጥርጣሬ ያዩዋታል። አያምኗትም። ‹‹ሆዷ አይታወቅም!›› ይሏታል። ሆዷን የሚያገኙበትን ብልሃት ሳያውቁ እንዲሁ ያሚታል።

ኢህአዴግ መንግስት ሆኖ ማስተዳደር ከጀመረ እንኳን ልቧን ማግኘታቸውን እንጃ እንጂ ስድስት ከንቲባዎች ‹‹ተከንትበውባታል››። አቶ ሙሉዓለም፣ አቶ ተፈራ ዋልዋ፣ አቶ አሊ አብዶ፣ አቶ አርከበ ዕቁባይ፣ አቶ ብርሃነ ደሬሳና አቶ ኩማ ደመቅሳ ናቸው። የመጀመሪያዎቹ ሶስቱ ከንቲባዎች ለአዲስ አበባ ስም ያለው ነገ አልሰሩላትም። እሷም ብዙ አልተደሰተችባቸውም። ለጥቀው የመጡት ጊማቸውን ‹‹ኦ›› የሚቆረጡት አቶ አርከበ ዕቁባይ ናቸው። አቶ አርከበ የአዲስ አበባን ልብ ለመክፈት ብርቱ ትግል ቢያደርጉም ብዙ አልተሳካላቸውም። ጥረታቸው በእናት ፓርቲያቸው ዘንድም የተወደደ አይመስልም። ‹‹የምን ቀደም ቀደም ነው!›› ተብለው ትንሽ ኩርኩም ሳይቀምሱ አልቀረም። እንዴውም ዋናው የህወሓት ሰውየ ‹‹የምን አስር ቦታ ድስት መጣድ ነው? በአንዴ አስር ድስት ማማሰል አይቻልም።›› ብለው ገስፀዋቸዋል ይባላል። የፖለቲካ ሰዎች ግን የዋናውን ሰውዬ ተግሳፅ ከአቶ አርከበ ዕቁባይ የአዲስ አበባን የልብ ቁልፍ ከማግኘት ሩጫ ጋር አያይዘው ተችተውታል። የሆነው ሆኖ ‹‹ለስሟ መጠሪያ ቁና አሰፋች›› እንደሚባለው አርከበን እናስታውሳቸው ዘንድ ጥለውት ያለፉት ነገር ቢኖር ‹‹የአርከበ ሱቆችን›› ነው። እንቅፋት የሚመስሉ ሚጢጢዬ የጐዳና ሱቆችን ባየን ቁጥር አርከበ ትውስ ይሉናል።

በ1997 ዓ.ም. ግን ለፖለቲከኞች እንቆቅልሽና የማትጨበጥ የሆነችው ሙሽራ አዲስ አበባ በኢህአዴግ የ14 ዓመት ቆይታ ክፉኛ ተንገሽግሻ ነበርና ለገኘው ፓርቲ ድምጿን ነፈገች። የውሸት ፈገግታዋንም ቢሆን ደበቀቻቸው። በተፈጠረው ድንጋጤም የተከፈለው ዋጋ ተከፈለ እንደገና ወደ ቁዘማ… ከዚያ በኋላም አዲስ አበባ እስከ ሚሊኒየሙ መግቢያ ያላስተዳደር ቆየች።

የቀድሞ የፓርላማ አባልና ጠ/ሚ መለስን በመከራከር የሚታወቁት አቶ ተመስገን ዘውዴ እንደሚሉት ከ1997 የምርጫ ግርግር በኋላ የአዲስ አበባ ጊዜያዊ አስተዳደር የተሾመበትን ጊዜ እንደዚህ ያስታውሳሉ፡- ‹‹በመጀመሪያ ከተማዋ በተቃዋሚዎች የምትተዳደር ለማስመሰል ተፈልጐ ነበር። ለዚህም የተቃዋሚ ካባ በመልበስ አቶ አየለ ጫሚሶ ቅንጅት እንዲመስሉ ተደረገ። በጓሮ መንገድም የቅንጅት ሰርተፊኬት ተሰጣቸው። በመቀጠልም ‹ከዚህ በኋላ ቅንጅት ማለት እሳቸው ናቸው። እሳቸውንም ሰሟቸው።› በሚል ለመረከብ ተፍተፍ ቢሉም የአዲስ አበባ ተመራጮችን ይሁንታ ማግኘት አልቻሉም። ኮረም ሳይሞላላቸው ቀረ።›› ይላሉ።

በተቃዋሚ ስም አዲስ አበባን ለማስተዳደር ምኞት የነበረው ገኘው ፓርቲም ሳይሳካለት ቀረ ማለት ነው። በዚህ ላይ ሚሊኒየሙ እየተቃረበ ነው። አሁን ላይ ሆነን ስናየው ኢህአዴግ ሚሊኒየሙን ‹‹የፖለቲካ ውድቀት ማገገሚያ›› ጥሩ ካርድ (Smart card) አድርጐ ተጠቅሞበታል። ሚሊኒየሙን ተከትሎ የገቡት ህዳሴ፣ ትራንስፎርሜሽን፣ ልማት… የመሳሰሉት ‹‹ስማርት ካርዱ››ን የሚያዳብሩ ሀሳቦች ናቸው። ‹‹ስማርት ካርዱ›› ከፖለቲካዋ ከተማ አዲስ አበባ ውጭ የሚታሰብ አይደለም። እናም አዲስ አበባን ሙሉ ለሙሉ አሸንፌው ለማስተዳደር ሳይችሉ አመራሮቹ ወደ እስር ከገቡ በኋላ ሸገር አለቃ አልነበራትም።

ሚሊኒየሙን ትልቅ የፖለቲካ አጀንዳ ማድረግና እንደ አቶ በረከት ገለፃ ደግሞ ‹‹ከናዳ የማምለጥ ሩጫ›› ውስጥ የገባው ኢህአዴግ ሚሊኒየም የተባለው ‹‹ስማርት ካርድ›› ያለ አዲስ አበባ ብላሽ እንደሆነ ገብቶታል። ጉዳዩ አዲስ አበባን ማስተዳደር ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያን ልብ የመያዝ ነውና ‹‹ጊዜያዊ አስተዳደር›› በሚል አቶ ብርሃነ ደሬሳ በሚሊኒየሙ መባቻ ግድም ከንቲባ ሆነው ብቅ አሉ።

ለነገሩ ብቅ ያደረጓቸው አቶ መለስ ናቸው። አቶ መለስ ፓርላማ በመገኘት ‹‹የተማሩና የተመራመሩ ሰዎችን አዲስ አበባን በጊዜያዊነት እንዲያስተዳድሩ ሾሜያለሁ። ከንቲባውም ብርሃነ ደሬሳ ይባላሉ።›› አሉ ይሄን በሚሉበት ጊዜ ወደ 61 የሚጠጉት ፓርላማ የገቡ የቅንጅት አባላት ድንጋጤ የተሰማቸው ይመስላል። ድንጋጤያቸውን የፈጠረው ምንድን ነው? እስቲ አቶ ተመስገን ዘውዴን እንስማቸው፡- ‹‹የቅንጅት አመራሮች በታሰሩበት፣ ቅንጅት ራሱ ተገቢ ላልሆነ ሰው በተሰጠበት ሁኔታ እንዴት ጠ/ሚ መለስ የተማሩና የተመራመሩትን አመጣን ይሉናል? ‹‹ህዝቡ መተዳደር ያለበት በመረጠውና በመረጠው ብቻ ነው። ህዝቡ የመረጣቸው እስር ቤት ናቸው…›› ብዬ በተሰጠችኝ ሁለት ደቂቃ ተናገርኩና የቅንጅት ተመራጮች በጠቅላላ ፓርላማውን ረግጠን ወጣን›› ይላሉ።

እሳት በሆነ የፖለቲካ ወቅት የጊዜያዊ መስተዳደርነቱን የተቀበሉት አቶ ብርሃነ ድምፃቸው ሳይሰማ፣ ሳይጨምሩና ሳይቀንሱ የአደራ ጊዜያቸውን ጨርሰው ለአቶ ኩማ በማስረከብ ሹልክ ብለው ሄዱ።

አቶ ኩማ ይሄው ተረኛ ከንቲባ ሆነው እየሰሩ ነው። የተጠመዱበት ስራ ደግሞ የአዲስ አበባን ደሃ ጠርጐ በማንሳት መሬቱን መቸብቸብ ነው። ለወትሮው ‹‹የምታጐርሰው አታጣም›› እየተባለች የምትሞካሸው አዲስ አበባ በአቶ ኩማ ዘመን ጥርሰ ወላቃ ብቻ ሳትሆን ብዙዎች የሚቀምሱት አጥተው የሚቸገሩባት ሆናለች። አንዳንድ አስተያየት ሰጪዎች ‹‹የአቶ ኩማ ስኬት በከተማዋ በርካታ ካድሬዎችን በየመንደሩ በመሰግሰግ ህዝቡ በመፈራራትና በመጠራጠር እንዲኖር ማድረግ ነው።›› ይላሉ። የኢህአዴግን ፖለቲካ ተግባራዊ ካደረጉ ከንቲባዎች መካከል አቶ ኩማ የመጀመሪያውን ደረጃ የያዙ ይመስላል። እንዲያም ሆኖ ግን አዲስ አበባን በበርካታ ጉዳዮች አስኮርፈዋል። የኑሮ ውድነቱ ካልተቀረፈው የቤት ችግር ጋር ተደማምሮ ሸገርን ‹‹ዝም›› አስብለዋታል። ዝምታው ምን ይሆን? ይሄን ማንም አያውቅም።

በሚቀጥለው ዓመት ማለትም በ2005 ዓ.ም. እስካሁን በይፋ ባልተነገረና ባልታወቀ ወር የአዲስ አበባና የክልሎች ምርጫ ይካሄዳል። ኢህአዴግ የአዲስ አበባን ልብ አያውቅምና ሩጫውን ከጀመረው ሰነባብቷል። ለኢትዮጵያ መግቢያ ቁልፍ የሆነችው አዲስ አበባን በውድም በግድም ለመጠቅለል ቅድመ ዝግጅት እያደረገ እንደሆነ የሚያሳብቁ ምልክቶች እየታዩ ነው።

በይፋ ከታዩ ሩጫዎች መካከል ዲግሪያቸውን እየተማሩ የነበሩ ካድሬዎቹን ቀጠን ባለ ትዕዛዝ ትምህርት አቁመው ወደ ህዝቡ እንዲገቡ አድርጓል፤ የነ አቶ ኩማ መስሪያ ቤት ደግሞ ምናልባትም እስከምርጫው የሚቆይ የአዲስ አበባ የ125ኛ ዓመት ክብረ በዓል እያከበርኩ ነው ብሏል። ያው ጠርናፊና ተጠርናፊዎችም እንዳሉ ይሆናሉ። በምርጫው ዋዜማ የሚመረቁ ኮንደሚኒየም ቤቶች፣ አስፓልት መንገዶችና ምናልባትም የባቡር ሀዲድ እናያ ይሆናል።

መልካም! ይሁን። ሩጫው ግን ቀጥሏል። ሌላው ከምርጫው በፊት ማጥፋት የሚያስቡት ያሉትን ጥቂት ጋዜጦች ይሆናል። በጥቂት ተከራካሪ ጋዜጦችና ጋዜጠኞች ላይ ያለው ዘመቻ ተጧጡፎ ቀጥሏል። እነዚህን ጋዜጦች የማጥቃት ዘመቻ የተከፈተባቸው ዋናው ምክንያቱ ከፊታችን ያለው የአዲስ አበባ ምርጫን ታሳቢ አድርጐ ነው ይላሉ አንዳንድ ፖለቲከኞች። ይሄን ጥርጣሬ እንዲጐላ የሚያደርገው ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ያዘጋጀው ውል ነው። ብርሃንና ሰላም ‹‹የማትማቸውን ጋዜጦች ሳንሱር አደርጋለሁ፣ ከዚያም ሕግ ጥሰዋል ብዬ ካመንኩ አላትምም።›› ይላል። እኔ ግን ከብርሃንና ሰላም ጀርባ ያለ ሃይል ይታየኛል። ምናልባትም ሌሎች የሩጫ ውጤቶችን እንሰማ ይሆናል። አዲስ አበባ ግን መኖሯን ቀጥላለች፣ እያዘነች፣ እየቆዘመች፣ እየተደሰተች፣ እየወለቀች፣ እየገጠጠች… ትኖራለች። ያውም ከፖለቲካ ጋር። ያውም የፖለቲካ ከተማነቷ አስጠብቃ።

የፍትህ ዓምድ

በዚህ ዓምድ የአገራችንን ህጎች ፣ ዓለም አቀፍ ህግጋት ፣ በሀገራት መካከል የተደረጉ ስምምነቶችን እንዲሁም ለንፅፅር እና ለማገናዘቢያ ይረዳን ዘንድ ሌሎች ሀገሮችን ህጎች መሰረት በማድረግ ከማንኛውም አይነት የፖለቲካ ተፅዕኖ ነፃ በሆነ መልኩ ትንታኔ ይሰጣል።

# የሠራተኞች ማህበር ሚና የት ድረስ ነው? ፩

"Take the job on our terms. If you don't there are others waiting." (‹‹ስራውን በእኛ ፍላጎት መስራት ካልፈለክ ተወው ሌሎች ስራ ፈላጊዎች ሞልተዋል››)። ይህን ይሉ የነበሩት ከዛሬ 130 ዓመት በፊት በአሜሪካን የነበሩ ባለሀብቶች ወይም በስራ ቋንቋ አሰሪዎች ናቸው። በዚያን ወቅት ሰራተኛው በአልተገደበ የስራ ሰዓት አሰሪ በሚከፍለው አነስተኛ ክፍያ እንዲሰራ ይገደድ ነበር። በስራ ቦታ በሚደርስባቸው አደጋ ምክንያት አሰሪ ድርጅታቸው የህክምና ወጪያቸውን አለመሸፈን ብቻ ሳይሆን ደሞዛቸውን ይቆርጣሉ ሲፈልጉም ከስራ ያባረሩዋቸው ነበር። በጊዜው ሠራተኛው ምንም ዓይነት የስራ ዋስትና የለውም ነበር። በስራው የመቆየት ዕጣ ፈንታው የሚወስነው በአሰሪው በጐ ፍላጐት ብቻ ነበር። እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ የስራ ጫናዎች በአብዛኛው የዓለማችን ክፍሎች አሰሪዎች ሰራተኞቻቸው ላይ ይደረጉ ነበር። ይሁንና ሰራተኞች የአሳሪዎች ጫና ይብቃን ለመብታችን እንቁም ብለው ራሳቸውን በማህበራት በማደራጀት አሰሪዎቻቸውን መሞገት ጀመሩ፣ በመንግስታትም ላይ ጫናቸው በረታ፣ አቤቱታቸውን አደባባይ ይዘው በመውጣት መብታቸውን መጠየቅ ጀመሩ። የዛሬ 123 ዓመት ገደማ የተጀመረው ትግል ሰሚ አግኝቶ በፈረንጆቹ አቆጣጠር በወረሃ ግንቦት (May) የዓለም ሠራተኞች አሰሪዎቻቸውን በህግ የማስገደድ ፍላጐታቸው መሰረት ያዘ። ይህም ቀን በመላው ዓለም የሰራተኞች ቀን እየተባለ እንዲከበር ተወሰነ።

ከዚህ የሰራተኞች አብዮት ጀምሮ ሀገራት የአሰሪ እና የሰራተኛ ህጐቻቸውን እንዲመረምሩ ተገደደ። ሀገሪቱ መሬት እንቀጥቅጥ የሆነው የሰራተኞች ድምፅ የመብት ጥሰት ባለበት በማናቸውም ጊዜ በዙሪያቸው እንደማይነሳ እርግጠኛ መሆን አልቻሉም። ስለዚህ ለፊውዳሎች እና ለሀብታሞች ያደላ የነበረውን አገዛዛቸውን መመርመሩ ቀጠሉ፣ መፍትሔም አበጁለት። ሰራተኞች በመራራ ትግላቸው መብታቸውን አስከበሩ። ህግም ተደነገገላቸው። ይህ ሁሉ ሲሆን ግን አሰሪዎች እጃቸውን አጣጥፈው አልተቀመጡም፤ ባንኮኒ ተደግፈውም ቢሆን የሰራተኞቻቸውን ጉልበት በዝብዘው ባገኙት ገንዘብ ውስኪና ቢራ ፉት እያሉ አብዮቱን እንዴት መቀልበስ እንደሚችሉ ዶለቱ። የሰራተኛ ማህበር አባል የነበሩ አባላትን መግደል፣ ማስደብደብ፣ ማስፈራራት እንዲሁም ስማቸውን ስራ ሊቀጠሩ የማይገባቸው በማለት በጥቁር መዝገብ ውስጥ አስገቡ። ተፅዕኖ እንዲደረግባቸውም ለአሰሪዎች አሳወቁ። ነገር ግን የሰራተኞቹ ጥያቄዎች ሰሚ አግኝተው ማህበራቱ እውቅና የሚያገኙበት መንገድ ተመቻቸ። የሰራተኞች ማህበራትም ለሰራተኛው መብት መከራከር እንደሚችሉ እውቅና መሰጠት ተጀመረ። ይህ አካሄድ በአንድ ወገን ሰራተኛው ለመብቱ እንዲቆም በር የከፈተለት ሲሆን በሌላ ወገን መንግሥት ከጣልቃ ገብነት እንዲሁም ለሰራተኛው ሊያደርገው ይችለዋል ከሚባለው የመድሎ ጥርጣሬ ነፃ እንዲሆን ረዳው። ለምሳሌ በአሜሪካን እ.ኤ.አ በ1935 ‹‹ National labor relations act›› የሚል ህግ በስራ ላይ ዋለ። የአብዛኞቹ ሀገራት ህጐች በውስጣቸው ሰራተኞች ማህበራትን ለማቋቋም፣ መብታቸውን በህብረት ለመጠየቅና ከሚደርስባቸው አላስፈላጊ ጫና በራሳቸው አማካኝነት እንዴት ነፃ መውጣት እንደሚችሉ መንገዶችን አመቻቸላቸው ከዚህ። በተጨማሪም አሰሪዎች በማናቸውም መልኩ የማህበር አባልና አመራር በሆኑ ግለሰቦች ላይ ማናቸውም ዓይነት ጫና እና ስራን የማሳጣት ሻጥር እንዳይሰሩ አስጠነቀቁ። ይህ ብቻ ሳይሆን አሰሪዎች ከሰራተኛ ማህበር ጋር በቅን ልቦና /Good faith/ መደራደር እንዳለባቸው አሳሰቡዋቸው። የሰራተኞች የስራ ሰዓት በአሰሪዎች ‹‹…አሁን ግባ አሁን ውጣ…›› ትእዛዝ ሳይሆን በህግ በተገደበ በቀን ከ8 ሰዓት መብለጥ እንደሌለበት በመርህ ደረጃ ተቀመጠ። ሜይ ዴይ የዚህ ሁሉ መስዋዕትነት ውጤት ነው። ዛሬ ዛሬ የሰራተኛው መብት በትክክል በሚከበርባቸው ሀገራት አሰሪዎች ከሠራተኛው ማህበራት ጋር በጋራ ይንቀሳቀሳሉ። ምንም እንኳ የተለያየ አጀንዳ ያላቸው ቢሆኑም አንዱ የአንዱን መብት ሳይገፋ በህግ እና በህብረት ስምምነቶቻቸው አማካኝነት ይሰራሉ። ለመሆኑ የሀገራችን የአሰሪ እና የሰራተኛ ህግ ለሰራተኛ ማህበራት የሚሰጠው ቦታ ምን ይመስላል? በተግባርስ ያለው እውነታ ምን ይመስላል? ማህበራትን ለማቋቋም ከህጉ ውጭ ያሉት ተግዳሮቶች ምን ይመስላሉ?

ኢትዮጵያን በመሳሰሉ ታዳጊ ሀገራት በአሰሪ እና ሰራተኛ መካከል ያለው ተቃርኖ መንግስታትን መፈተናቸው አይቀሬ ነው። ባለሀብቶች ለህዝቡ የሚደጥሩት የስራ እድል ታሳቢ በማድረግ በሌላ ወገን ደግሞ ባለሀብቶች አግባብ ባለው የስራ ውል በመታቀፍ የህዝቡን ጉልበት ሳይበዘብዙ በቂ ትርፍ የሚያገኙበትን መንገድ ማመቻቸት አለበት። ሀገር የምትገነባው በባለሀብቶች ብር ብቻ ሳይሆን በሰራተኛው የነቃ ተሳትፎ ነው። ስለዚህ የሰራተኛው መብት ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። የኢትዮጵያ የአሰሪ እና የሰራተኛ ጉይ አዋጅ 377/1996 አንቀፅ 113 ማህበራት የማቋቋም መብትን ደንግጓል። የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 ‹‹ሠራተኞች እና አሠሪዎች እንደ አግባቡ የሠራተኞች ወይም የአሰሪዎች ማህበር ለማቋቋምና ለመደራጀት የማህበሩም አባሎች ለመሆንና በማህበሩም ለመሳተፍ መብት አላቸው›› ይላል። አንቀጽ 2 (ሀ) ደግሞ ‹‹የሰራተኞች ማህበር ማለት ሰራተኞች በአንድ ሆነው የሚያቋቁሙት ማህበር ነው›› ይላል። ይህ አዋጅ ሰራተኞች በመደራጀት ከአሰሪዎቻቸው ጋር የሚኖራቸውን ግንኙነት መስመር ለማስያዝ ማህበራትን የማቋቋም መብት ሰጥቷል። ይህ መብት ለአሰሪዎችም ተሰጥቷል። የዛሬው ትኩረታችን በሰራተኞች ጉዳይ ላይ ስለሆነ የአሰሪዎችን ማህበር ለሌላ ጊዜ እናቆየው። ምንም እንኳን ህጉ በግልፅ ለሰራተኛው ማህበር የማቋቋም መብት የሰጠ ቢሆንም በሀገራችን በአብዛኛው የሚገኙ የግል ድርጅቶቸ በአሰሪዎች ጫና ማህበራት እንዲያቋቁሙ አያደረጉም፣ ያሉትም ማህበራት በመንግስት አልያም በአሰሪዎች ጉትጎታ /ሎቢ/ ስለሚደረግባቸው ስለሚደረጉ የሰራተኛውን መብት በቅጡ ማስከበር አልቻሉም። በአንድ ሰራተኛ እና በአሰሪው መካከል ያለው ጉዳይ በህብረት ስምምነት በሁለቱ ወገኖች የስራ ውል በመብትና በግዴታ ማዕቀፍ የተቀመጠ እና ሰራተኞች በአሰሪው የሚደርስበትን ሕገወጥ አካሄድ ለማስተካከለና መብቱን ለማስከበር በግለሰብ ደረጃ አሰሪን የመክሰስ መብት አለው። ይሁን እንጂ በአሰሪና በሰራተኛው መካከል ያለው የፍርድ ቤት ክርክር ውሳኔ እስኪያገኝ ሰራተኛው መብታቸው በአሰሪዎቻቸው እየተደፈረ፣ ከፍተኛ የስራ መደራረብ እና ጫና እየተደረገባቸው አቤቱታቸውን አደባባይ ይዘው ሳይወጡ ዋጥ አድርገው በ19ኛ መቶ ክፍለ ዘመን በሌሎች ሀገራት የነበረው ጫና እየደረሰባቸው ይገኛሉ። ይህን የአሰሪዎች ጫና ለማርገብ የሠራተኞች ማህበራት ሚና ከፍተኛ ነው። ህጉም የማህበራትን መቋቋም በመብት ደረጃ ፈቅዷል። ነገር ግን ማህበራትን ማቋቋም ለሰራተኞች በመብት ደረጃ ተፈቅዶ አሰሪዎች ደግሞ ድርጅቶቻቸው ማህበራትን እንዲያቋቁሙ ቢያደርጉ የማህበራቱ ሚና ይበልጥ የጐላ ይሆን ነበር። በመሬት ላይ ካለው ሃቅ እንደሚስተዋለው ሰራተኞች እየደረሰባቸው ያለው የመብት ጥሰት፣ ህገ ወጥ የሆኑ የስራ የውል ስምምነቶች፣ ማህበራት እንዲያቋቁሙ የሚደረገው ማስፈራራትና ከስራ የማባረር ዛቻ ለአሰሪዎች-ሰራተኞች ማህበራትን እንዲያቋቁም በህግ ቢገደድ መፍትሔ ያገኙ ነበር። ከዚህ በተጓዳኝ ግለሰቡ በራሱ ደረጃ ሊያስከብረው ከሚችለው መብት በተጨማሪ የሰራተኛ ጉዳይ የሚመለከታቸው የመንግስት ተቋማት የሰራተኛው መብት መከበር አለመከበሩን ጥብቅ በሆነ አሰራር ክትትል ሊያደርጉበት ይገባ ነበር። ይህ ግን ሲሆን አልታየም። አግባብነት ያለው የመንግስት ተቋም ማህበራት በምን ደረጃ ላይ እንዳሉ ቢከታተል ባለሀብቶች ተገቢ ትርፍ በማግኘት የሰራተኞቻቸውን ጉልበት ሳይበዘብዙ በመግባባት ለሀገራዊ እድገት ዘላቂነት ያለው አስተዋጽኦ ባደረጉ ነበር። ያለሰራተኛው ህዝብ የነቃ ተሳትፎ ለባለሀብት ብቻ የሚደረግ እንክብካ በምንም ዓይነት መልኩ ሀገራዊ ግቡን ሊመታ አይችልም። ጉዳዩ የሚመለከታቸው የመንግስት ተቋማትም ያለ ማንም አስታዋሽነት የሰራተኛው መብት የሚከበርበትን መንገድ ተከታትሎ የማስፈፀም የሞራልም ሆነ የስራ ግዴታ አለባቸው። ቸረ እንሰንብት። ይቀጥላል።

# ኦ! አምላክ ሆይ

… ከገፅ 9 የዞረ

ሚዲያዎች ያመነው ጉዳይ ነው። ይህ በቅርቡ ከተነሳው የሙስሊሞች ጥያቄ ጋር የተያያዘው ግድያ ግን ነገሮችን ያባብስ እንደሆን እንጂ መፍትሄ ሊሆን ስለመቻሉ እጅግ አጠራጣሪ ነው። በኦጋዴን ስላለው የጦርነት ዘመቻም የሚገልፁ የውጭ ሚዲያዎች ነፍስን የሚያሰቅቅ የጭካኔ እርምጃዎች በስፍራው እንደሚካሄዱ ይነግሩናል።

ስለእነዚህ ውጥንቅጦች ሁሉ የሚፀልዩና የሚማልዱ የሃይማኖት ሰዎች ደግሞ በየገዳማቱ የሚገጥማቸው ፈተና ይህ ነው የሚባል አይደለም። በዋልድባና በዝቋላ የምናየው ሁሉ፡- አምላክ ሆይ፡- በወዴት አለህ? የሚያሰኝ ነው።

እኔም ይህንን ሁሉ በመፃፌ ምን ሊገጥመኝ እንደሚችል አላውቅም። በርካቶች ፀሐፍያን መልካም ነገር አልገጠማቸውም። እውነቱን መናገር ዋጋ ያስከፍላልና። በመሆኑም እንቅልፍ-አልባ ሌሊቶቼ እጅግ በዝተዋል። ዛሬ እያዝና እታሰር ይሆን? የሚል ሰቀቀን ህይወቴን የገደል አፋፍ ጉዞ አድርጐታል። ምንም አጥፍቼ አይደለም! ጥፋት እንዳይፈለግና እንዳይለጠፍብኝ ሰግቼ እንጂ። የሆነ ሆኖ ከዚህ በኋላ ወደኋላ መመለስ አልችልም። አንዴ በነፃነት የውስጤን መተንፈስ በመጀመሬም ይሄን የሰውነት ተፈጥሯዊ ማንነቴን ማቀብ አልሻም። እውነቱን ተናግሬ የመሸበትም ሆነ የጨለመበት ለማደር ዝግጁ ነኝ። ለአንዲት ሰከንድም ቢሆን ያለነፃነት መኖር ከቶም አልፈልግም። ታዲያ ያለነፃነት ይሄን ኑሮ ኑሮ ብዬ እንዴት እገፋዋለሁ?

ብዙዎች ወገኖቼ ግን በፍርሃት ተሸብበው እንደበታቸው ተለጉሟል። ታፍነዋል። በውስጣቸውም ሰላም የለም! በአፈና ውስጥ ሰላም የለምና። ነፍስም ያለነፃነት እስትንፋስ ብቻ ናትና። ፕ/ር መስፍን ወ/ማርያም በመጽሐፋቸው እንዳሉት፡-

‹‹ለብዙ ሰዎች ሰላም ማለት ጦርነት የሌለበት ሁኔታ ነው። ወገን ወይም ቡድን ለይተው ጦር መሳሪያ መዝዘው ካልተዳሙ፣ ካልተቆሳሰሉና ካልተገዳደሉ ሰላም ነው ይባላል። ይህ ሁኔታ የሰላም ሁኔታ ላይሆን ይችላል። አንድ አባት ልጁን በጥፊ ወይም በለበቅ እየደበደበ ‹‹ጭጭ፣ እስቲ ትንፍሽ!›› እያለ ማልቀስ እንኳን ቢከለክለው፣ ወይም አንድ ሰው አንድ ሌላ ሰው ደረት ላይ ቆሞ ትንፋሽ ቢያሳጣው፣ አንድ ሕዝብ በፖሊስና በጦር ኃይል ተሰንጎ ተይዞ ጭጭ ብሎ በደሉንና ጥቃቱን ቢችል ሰላም ነው ማለት አይደለም። ኃይለኛ ደካማውን ሲያጠቃ ሰላም የለም፤ ብዙዎች ጥቂቶችን ሲያጠቁ ሰላም የለም፤ ጥቂቶች ተደራጅተውና ታጥቀው ብዙዎቹን ሲያጠቁ ሰላም የለም። በማናቸውም በኃይል ወይም በጡንቻ ላይ በተመሰረተ የአገዛዝ ሥርዓት ውስጥ ሰላም የለም። ጸጥ፣ ለጥ ብሎ መገዛት ሰላም አይደለም።

ጦርነት ባለመኖሩ ብቻ ሰላም አለ ማለት አይቻልም። ኃይለኞች ደካሞችን አስገብረው፣ በጉልበታቸው የሰውን ልጅ መንፈስ ገድለው፣ አእምሮው ታዛዥና ተገገር ብቻ እንዲሆን አድርገው በድኑን እንደአሻንጉሊት በሚጫወቱበት ሁኔታ ሰላም የለም። እንኳን መሣሪያ አንስቶ ለመዋጋት መረረኝ፣ ደከመኝ ለማለት የሰው ልጅ የመንፈስ ኃይሉ ተሙዋጦ በድን፣ የቁም ሬሣ ሆኖ በሚንገላታበት የአገዛዝ ስርዓት ውስጥ ሰላም የለም። በእንደዚህ ዓይነቱ ሁኔታ ውስጥ ጥላቻ፣ ወፍራምና ልብን ሞልቶ የታፈነ ጥላቻ አለ። ጥላቻ ክፉ ጦርነት ነው። የተጠቃ፣ የተበደለ፣ የተበዘበዘና የሰውነት ክብሩን የተገፈፈ ሰው በልቡ ውስጥ የታመቀው ጥላቻ እያደገ ጊዜና ሁኔታው ሲፈቅድለት ግፈኞችን ይዋጋል። ስለዚህም ግልጽና ገሀድ አይሁን እንጂ ጦርነት አለ። ከጥላቻ ከሚመግል ቂም የሚመነጨው የደካማዎች ጦርነት በይበልጥና በተጨማሪ ራስን በመጉዳት የሚደረግ ጦርነት ነው። ጊዜ ይፈጃል እንጂ ምን ጊዜም ድል የደካማዎቹ ብዙኃን ነው።

እንግዲህ ሰላም አፍአዊ ጸጥታ ብቻ አይደለም ማለት ነው። ሰላም የውስጥና የመንፈስ ደስታና እርካታም ነው።…››

(ገፅ 81-ኢትዮጵያ ከየት ወዴት?)

ታዲያ ዛሬ በአገራችን ሰላም አለ? ከራሳችን ተጣልተን፣ ከህሊናችን ተሟግተን፣ ከነፍሳችን ተከራክረን፣ ከልባችን ተወዛግበን፣ ከቤታችን ተለያይተን፣ ከወገናችን ተኳርፈን እና ከእኛነታችን ተነጥለን ምን ዓይነት ሰላም ሊኖረን ነው? እህህአችንስ እስከመቼ ይቀጥላል?

የኢትዮጵያውያን አምላክስ ዝምታህ ስለምን ፀና? ስለእኛስ ግድ አይልህምን? የክፉዎች የግፍ አገዛዝ ስለምን እንዲህ ረዘመ? የጭቆናቸው ቀንበር በላያችን ላይ ሲከብድ እና ሲበረታስ በመከራ እንድንኖር የተውኸን ምን በድለንህ ይሆን? ምንም የማይታይበት ዛሬን እንደወይንጠጁ ተዓምር በመልካሙ ወይን የማትሞላውስ እውን ይህ ላንተ ተስኖህ ነው?

ኦ!....አምላክ ሆይ ስለምን ተውኸን?



## ኪነጥበብ

# ማሰብ መለያየት ማወቅ አንድ መሆን ፪

እግዜርና ዳዊት አብረው ተባደኑ
ብቻውን ታጠቀ ጎልያድ ምስኪኑ
አንዳንዱ ተገዶ ብቻውን ሲፈጠር
በጥቅሻ ይወድቃል እንኳንስ በጠጠር
በዕውቀቱ ሥዩም

ባለፈው ሳምንት በዚህ ግጥም ጀምረን ነበር። አሁን አሁን ስልጣኔ እየመሰለ የመጣውን ሀሳብን በዱላ ተቃውሞን በስድብ የመግለጽ አባዜ እናይበት ዘንድ። አቅመ ቢሶች ብቻቸውን ሆነው መኖር አይችሉም ፣መፍጠር አይችሉም፣ መስራት አይችሉም ፣ መጠበብም። እናም ጥግ ፍለጋ ቀን በጸሐይ ማታ በጨረቃ /በፋኖስ/ ይኳትናሉ። እምነት ይሉት ይሉኝታ ለእነሱ አይሰራም። ትምህርት ይሉት ፍለጋ ለእነሱ አያገለግልም ። ማወቅ እና ማንበብ ይሏቸው ቅመሞች ለእነሱ ገለባ ናቸው። የእነሱ የህይወት መሰረት ጥግ ፈልጎ መጠጋት ተቆርቋሪ መስሎ መታየት አዲስ ሀሳብ አፍላቂዎችን፤ ሲችሉ በስድብ ማሸማቀቅ ያለዚያ በዱላ ማሳመን ይህን ያልቻሉ እለት ‹ይታሰሩልን ፣ይደብደቡልን ፣ይገደሉልን › ብለው መታያ ይወስዳሉ። እኒህ አሜኪላዎች ለጠቢቡ ተግዳሮት የሚሆኑት ከካድሬነት ፈልሰው ብቻ አይደለም ። እንደጸሐፊው ብእር ይዘው ፣እንደ ተዋናይ መድረክ ላይ ቆመው ፣እንደ ሰዓሊው ብሩሽ ጨብጠው፣ ይህን ሸፍጥ ሊሰሩ ይችላሉ።

ወይም ለይቶላቸው ከካድሬነት ጎራ በግላጭ ተሰልፈው ጠመንጃ አነግተው ሳንጃ ወድረው ወንበር ላይ ሆነው ጸሐፊ ምን ጻፈ፣ ገጣሚ ምን ገጠመ፣ ባለቅኔ ምን ተቀኘ? የሚሉ የእለት ስራቸው ሰውን መኮነን የሆኑ ጥቂት አይደሉም ።

ለመሆኑ ይህን መሰሉ የጋጠወጥ ኑረት መቼ ይሆን የሚቀየረው ? የምናነባቸው መጽሐፍት የሚለውጡን መቼ ነው? የምንማራቸው ትምህርቶች የሚቀይሩን መቼ ነው? እስከ መቼ በመታበይ እና በመዋሸት እንኖራለን ? እስከ መቸስ የቅጥፈት እንጀራን እንቆርሳለን? ሰዎች ሁሉ በእኛ መንገድ ካልተጓዙ ስህተተኞች የሚሆኑብን ስለምድን ነው?

እስኪ ባለፈው እንደተመለከትነው ጥቂት ታሪካዊ አስረጅዎችን እንመልከት ። አቤ ጉበኛ አሰበ፣ ያሰበውን ጻፈ፤ ስለጻፈ ተወቀሰ፣ ቢወቀስም መልሶ ጻፈ በስልጣን ተደለለ እርሱ ግን ከስልጣን ብዕር ይሻላል ብሎ ሌላ ጻፈ ። ሀሳቡን በሃሳብ የገታ አልነበረም ። ወደ ግዞት ተላከ ። በሚከተለው ሸኝ ደብዳቤ ወደ ጎሬ።

« አቶ አቤ ጉበኛ የተባለው ሰው በወር ሃምሳ ብር እያገኘ በኢሊባቡር ጠቅላይ ግዛት ከጎሬ ከተማ ሳይወጣ በቀን ሶስት ጊዜ ማለትም ከጠዋቱ በ3ሰዓት ከምሳ በኋላ በ9ሰዓት እና በ12 ሠዓት ፖሊስ ጣቢያ እየፈረመ በብርቱ ቁጥጥር እና ጥበቃ ስር ሆኖ በግዞት እንዲኖር በአጃቢ ፖሊስ ስለላክነው መድረሱ እንዲረጋገጥልን። ግዞተኛው ከውጭ ሀገር ሰዎች እንዲሁም አድመኛ እና ተጠርጣሪ ከሆኑት የአገር ተወላጆች ጋር እንዳይገናኝ ብርቱ ቁጥጥር እንዲደረግበት እና ስለጠቅላላው ሁኔታው በየሶስት ወሩ አንድ ጊዜ ሪፖርት እንዲደርሰን በማክበር አስታውቃለሁ።»

ይህን ደብዳቤ የጻፉት የወቅቱ የአገር ግዛት ሚንስትር ደጃዝማች ክፍሌ እርገቱ ሲሆኑ የደብዳቤው ተቀባይ እና ግዞት አስፈጻሚው ደግሞ በዘመናዊ የአማርኛ ልብወለድ ድርሰት ውስጥ የመጀመርያ ረዥም ልብወለድ ደራሲ የሚባሉት ደጃዝማች ግርማቸው ተክለሃዋርያት መሆናቸውን የኤልያስ አያልነህ «የአቤ ጉበኛ ብእራዊ ተጋድሎ» ይናገራል።

የአርአያ እና የቴዎድሮስ ደራሲ የሆኑት ግርማቸው ተክለሃዋርያት ምንም በድርሰት ይታወቁ እንጅ ደራሲያንን ወይም የኪነጥበብ ሰዎችን በማዋከብም እውቅናን ያተረፉ ነበሩ። የተስፋዬ ሳህሉ /አባባ ተስፋዬ/ የቴሌቪዥርን ስራተኝነት ደሞዝ ሲጀመር በፈረንጆች የተፈቀደ ነበር። ፈረንጆች ከዚች ሀገር ዘወር ሲሉ ግን ግርማቸው ተስፋዬን ጠርተው « ወፍ እንዳገሯ ትጮኻለች» ብለው የተስፋዬን ደሞዝ ቀንሰው ቀንሰው ከነበረው አንድ አራተኛ አደረጉት።

አቤ በግዞት ወደ ግዛታቸው ሲመጣም «የስነ-ጥበብ ሰው ነጻነት» አላስጨነቃቸውም ። ደራሲ ይታፈን ከሚሉት ወገን ቆመው የሚከተለውን ትእዛዝ ለፖሊስ አዛዡ አስተላለፉ።

«በዕየለቱ ፖሊስ ጣቢያ ድረስ እየሄደ እንዲፈርም ፣በከተማ ውስጥ ሊዘዋወርበት የሚችላቸው ቦታዎች እና ሰአቶች ተለይው እንዲነገሩት፣ለጥበቃ ምቹ የሆነ ቦታ ፈልጎ እንዲከራይ ፣ በህዝብ መሰብሰቢያ ቦታ እንዳይገባ ፣ከአድመኞች እና ከተጥርጣሪዎች ጋር እንዳይገኛኝ ፣ከውጭ ሀጋር ሰዎች ጋር በፍጹም እንዳይገናኝ፣ ለቤተሰቦቹም ሆነ ለመንግስት መስርያ ቤቱ ደብዳቤ ቢጽፍ አሳይቶ እና አስገምግሞ፣ በፖስታም ሆነ በእጅ የሚደርሱት መልዕክቶች ቢኖሩ ፖሊስ አዛዡ ሳይመረምር እና ሳያሳውቅ እንዳይሰጠው፣በእጁ ገንዘብ ካለው ከሃምሳ ብር በላይ በእጁ እንዳይዝ ፣ተቆጣጣሪ እና ተጠባባቂ በስውር ተመድቦበት እንከታተለው።»

ኢትጵያዊው ደራሲ ለሌላኛው ኢትዮጵያዊ ደራሲ እንዲህ ያለ የግዞት ትእዛዛ አስተላልፈዋል። ዛሬም ዘመናችን ከዚህ የተለየ ታሪክ የሚስተዋልበት አልሆን ብሏል። ገዥውን ፓርቲ የሚያንቆለጳጵስ የኮብል ስቶንና የኮንዶሚኒየም ልማትን የሚያሞካሽ፤ አብዮታዊ ዴሞክራሲን የሚያቀጣጥል ጽሑፍ የማይጽፍ ደራሲ የጎሪጥ ይታያል ።ይህን የመሰለውን የማያቀነቅን የጥበብ ሰው የልማት ሃይል ካለመሆን አልፎ የጥፋት ሃይል እንደሆነ ይነገራል። ይህ ታዲያ ምንድን ነው ጎበዝ?

በዓሉ ግርማን ማን ሰወረው ? በእውቀቱ ሥዩምን ማን ደበደበው? ጋዜጠኞችን ማን አሰረ? ጋዜጦችን ማን ዘጋ? የመንግስት አለዚያም የተፈጥሮ ጉልበትን በመተማመን ማሰብ ሲያቅታቸው መሳደብ፣ መጻፍ ሲያቅጣቸው መደባደብን የሚመርጡ ናቸው።

ለነገሩስ ይህን መሰሉ ክስተት ከዘመናት በፊት ሁሉ የነበረ ነው። ስላሰበ ወይም ስለተቀኘ ወይም ስለገጠመ የተገደለ ብዙ ነው። የአጼ ቴዎድሮስ አዝማሪ በራሳቸው በቴዎድሮስ ተገድለዋል። አዝማሪው ግን ምህረት ይደረግለት ዘንድ እንደሚከተለው ራሱን አዋርዶ ለምኖ ነበር።

አወይ ያምላክ ቁጣ
አወይ የእግዜር ቁጣ
አፍ ወዳጁን ያማል ስራ ሲያጣ

እንዲህ ቢልም ግን አልቀረለትም ። በሽመል ደብድበው ገደሉት። ይሉናል ቀደምት የቴዎድሮስ ታሪክ ጸሐፊዎች።

በዚያውም ዘመን ይህን የመሰለ ደግሞ ታሪክ ተፈጥሮ ነበር። አለቃ ፈንታ ከአጼ ቴዎድሮስ ሃምሳ ብር ተሰጣቸው። አጼው ከስጦታው ጋር እንዲህ አሉ። « ይህን ወስደህ አትበላውም ከቤትህ ትቀብረዋለህ» ይህን ጊዜ አለቀ ፈንታ እንዲህ አሉ « ጃን ሆይ መሬት በእጀ ነው ብለዋል መቸም አያመልጥ» አጼው በዚህ አቄሙ። ደግሞ ሌላ ጊዜ ቤተክርስቲያን አሰርተው «ይህ ቤተክርስቲያን ስፋትና መጥበቡን እስኪ እየው» ብለው አለቃን ጠየቁ። አለቃም « ጃንሆይ ለአምስት ሰሞንኛ መቸም ይበቃል» ጃንሆይ ቂማቸው ገንፍሎ አለቃን አስረው አስገደሏቸው። ለመሆኑ የአለቃ ጥፋት ምንድን ነው። ሃሳብ ?!

ከዚያም ወዲህ ከዘመነ ምኒሊክ እስከ ዘመነ ሀይለስላሴ የነበሩት የመጀመርያው ኢትዮጵያዊ የተውኔት ባለሙያ በጅሮንድ ተክለሃዋርያት ተክለማርያም የዚህ የመገፋት ገፈት ቀማሽ ነበሩ።

ከአጼ ሃይለስላሴ ጋር ባለመስማማት እስራት እና የገንዘብ ቅጣት ቀምሰዋል። ከኢጣሊያ ወረራ በኋላም ቅራኔአቸው በመካረሩ በስደት በድህነት ኖረው በስተእርጅና ወደ ሃገራቸው ገቡ። እስከእድሜአቸው ፍጻሜም በግብርና ሙያ ሰነበቱ። እኒህ የድርሰት ሰው ፋቡላን ሰርተው ዘመነ ኢያሱን መተቸታቸው የሚታወቅ ሲሆን ለአጼ ሃይለስላሴም የሚመለሱ እንደማይሆኑ መገመት ይቻላል።

እንዲህ እየተገፋ የመጣው የጭቆና እና የአፈና ስርዓታችን ከግለሰብ እስከ ማህበረ መንግስት ድረስ ከዘውዳዊ እስከ አቢዮታዊ መንግስት ድረስ ቀጥሏል። ለመሆኑ መድረሻችን የት ይሆን?

# ጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ <<የመለስ አምልኮ>> የሚል መጽሐፍ አሳተመ የፍትህ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ የ4 ወር እስር ወይም 2000 ብር ተፈረደበት

**-ክንፈሚካኤል ደበበ (አበበ ቀስቶ) የ8 ወር እስራት ተፈረደበት**




በእነ አንዷለም አራጌ የክስ መዝገብ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት 3ኛ ወንጀል ችሎት እየታየ ባለው የፍርድ ሂደት ላይ የፍትሕና የነጋድራስ ጋዜጦች «ሚዛናዊ ዘገባን አላቀረቡም» በሚል አቃቤ ሕግ አቅርቦት ለነበረው አቤቱታ ፍ/ቤቱ ሰኞ ዕለት ውሳኔ ሰጠ።

በፍ/ቤቱ የመጀመሪያ ውሳኔ መሰረት አንዷለም አራጌና ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋን በሚመለከት በሁለቱም ጋዜጦች ላይ የወጣው ዘገባና ፅሁፍ በችሎቱ በቀጥታ እየታየ ያለ ዘገባን መሰረት ያደረገ በመሆኑና በዳኝነት አሰራሩ ላይ የሚያመጣው ችግር ባለመኖሩ ምክንያት የአቃቤ ሕግን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ የሁለቱም ጋዜጦች ዋና አዘጋጆች ነፃ መሆናቸውን ገልጿል።

ነገር ግን በእነ አንዷለም አራጌ የክስ መዝገብ 2ኛ ተከሳሽ የሆነው ናትናኤል መኮንን ክሱ በፍ/ቤት እየታየ ባለበት ሁኔታ መጋቢት 21/2004 ዓ.ም. በፍትሕ ጋዜጣ ላይ ያወጣው ፅሁፍ በሀገሪቷ ባለው በየትኛውም ሕግ መሰረት የሚቀርብበት ሁኔታ አለመኖሩን ፍ/ቤቱ ተናግሯል - «የጋዜጣው ዋና አዘጋጅ ኃላፊነት የቱ ጋር ነው?» በማለት።

5ኛ ተከሳሽ ክንፈ ሚካኤል ደበበ ሚያዚያ 5/2004 ዓ.ም. «ማቆሚያና ገደብ ያጣው የምስኪኗ እናቴ እንባ!» በሚል ርዕስ በፍትህ ጋዜጣ ላይ ያወጣው ፅሁፍ የዳኝነት ገለልተኝነትን በሚጐዳ መልኩ ጋዜጣዋን በመጠቀም ፍ/ቤቱ ጉዳዩን በሚሰማበት ወቅት ማቅረቡ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ 449/1 መሰረት «ፍ/ቤትን የመድፈር ወንጀል ነው» በማለት ጥፋተኛ ብሎታል። በዚህም መሰረት የተጠቀሰው አንቀፅ ከ1 አመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም ከ3 ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መዋጮ የሚያስቀጣ መሆኑ ተጠቅሷል።

በመሆኑም ተከሳሹ የወንጀል ድርጊት አፈፃፀም በቀረበበትና ክርክሩ በዚህ ፍ/ቤት በግልፅ እየተከታተለ ባለበት ሁኔታ በህገ መንግስቱ የተቋቋመውን ነፃ የዳኝነት አካል ላይ ጥርጣሬን ለመጫርና የህዝብ አመኔታን ለማሳጣት የተፈፀመ በመሆኑ የእስራት ቅጣት አማራጭን በመውሰድና የተከሳሹን ግላዊ ሁኔታዎች ግምት ውስጥ በማስገባት በ8 ወር እስራት እንዲቀጣ ፍ/ቤቱ ወስኖበታል።

እንዲሁም የፍትሕ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ተመስገን ደሳለኝ የወንጀል ሕግ አፈፃፀሙ በፕሬስ ስራ በዋና አዘጋጅነት የተሰማራና የሚታተሙትን ፅሁፎችና የህትመት ውጤቶች ይዘት የመቆጣጠርና ማንኛውንም ነገር ያለፈቃዱ እንዳይታተም ማድረግ ይገባው እንደነበረ ፍ/ቤቱ ዘርዝሯል።

ይሄም ለዳኝነት ስራው አካሄድ መሰናከል ሊሆን የሚችል ፅሁፍ በማተምና በማሰራጨት የተፈፀመ ስለሆነ የአራት ወር እስር ወይም በአማራጭ 2ሺህ ብር እንዲከፍል ተፈርዶበታል። የገንዘብ መቀጫው እንደአማራጭ የቀረበው የጋዜጠኛ ተመስገንን፣ የፕሬሱን ለህዝብ ብሎም ለፍትሕ ስርዓቱ የሚሰጠውን ጠቀሜታ ግምት ውስጥ በማስገባት መሆኑን ፍ/ቤቱ በውሳኔው ላይ ገልጿል። በወቅቱም ጋዜጠኛ ተመስገን የተጠቀሰውን ብር እስኪከፍል ድረስ በፍ/ቤቱ ቅጥር ግቢ የ«አንበሳ ቤት» ተብሎ በሚጠራው በብረት በተሰራ ማቆያ ውስጥ ለአንድ ሰዓት ያህል ቆይቶ ተለቅቋል።

በሌላ በኩል የፍትህ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ተመስገን ደሳለኝ በ2003 ዓ.ም. ተፅፈው በጋዜጣዋ ላይ ታትመው ከነበሩት ስራዎቹ ውስጥ የተመረጡ ፅሁፎችን «የመለስ አምልኮ» በሚል ርዕስ እንደአሳተመ ታውቋል።

መፅሐፉ የቋንቋ ተኮሩን ፌደራሊዝም ሀገራዊ ጉዳዮች፣ ስርዓቱን ስለሚመሩት ታላላቅ ባለስልጣናት ፖለቲካዊ ማንነት፣ ስለሰላማዊ አብዮቶች እንዲሁም የተቃውሞ ፖለቲካውን የተመለከቱ ፅሁፎች ተካተውበታል።

በመፅሐፍ ውስጥ የተካተቱት ጉዳዮች በይዘታቸው በአምስት ክፍሎች የተከፈሉ ሆነው በውስጣቸው በጠቅላላው ሰላሳ ሁለት አርቲክሎች ተካተውበታል።በክፍል አንድ «ሀገራዊ ጉዳዮች» በሚል ርዕስ ስር አምስት አርቲክሎች፣ በክፍል ሁለት «የገዥዎች ጦማርና ባህሪያቶቻቸው» በሚል ርዕስ ስር ሰባት አርቲክሎች፣ በክፍል ሶስት «ታላላቅ ሀገራዊ ክስተቶች» በሚል ርዕስ ስር ሰባት አርቲክሎች፣ በክፍል አራት «አንዳንድ ነጥቦች ስለፓርቲዎቻችን» በሚል ርዕስ ሰባት አርቲክሎችን እንዲሁም ክፍል አምስት «ህዝባዊ ብሶቶች» በሚል ርዕስ ስድስት አርቲሎችን ይዟል።

ስለመጽሐፉ አስተያየታቸውን ካሰፈሩት መካከል የአንድነት ለዴሞክራሲ እና ለፍትህ /አንድነት/ ፓርቲ ፕሬዚዳንት ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ «አገራችን እንደ ተመስገን ያሉ ብዙ ሚሊዮን ዜጎች ያስፈልጓታል» ሲሉ፤ ፕ/ር መስፍን ወልደማርያም በበኩላቸው «ተመስገን ደሳለኝ… በውይይትና በክርክር የዴሞክራሲን ባህል እያሰፋ ነው፣ የፍርሃትንም አድማስ እያጠበበ ነው…» በማለት ስለጋዜጠኛ ተመስገን የየግል እምነታቸውን በመፃህፉ ላይ ገልፀዋል። የመጽሐፉ ሃያ ሺ ኮፒ በመጀመሪያው ዙር መታተሙን እና በአጠቃላይ 255 ገፅ ይዞ በ39 ብር ለገበያ እንደቀረበ ታውቋል።

ይህ በአገሪቱ ዋና ዋና ከተሞች በትላንትናው ዕለት የተሰራጨው መጽሐፍ የመጀመሪያው ቅፅ ሲሆን «ለምን ትፈራለህ?» በሚል ርዕስ ሁለተኛው የመፅሐፉ ቅፅ በቅርብ ቀን ገበያ ላይ እንደሚውል ታውቋል።


# የኢትዮጵያ አርበኞች ማህበር አባላት በአመራሮቹ አለመግባባት ምክንያት ለችግር እየተጋለጡ ነው

በ1931 ዓ.ም የተመሰረተው የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኛ ማህበር አመራር ውስጥ ባለው አለመግባባት ምክንያት የማህበሩ ገንዘብ ለሙስና መጋለጡን እና አባላቱ ለከፋ ችግር መጋለጣቸውን በተለይ ለፍትህ ገለፁ።

በማህበሩ ውስጥ የተከሰተውን አለመግባባት አስመልክቶ የኢትዮጵያ ሰራተኞች ማህበራዊ ሚኒስቴር በህዳር 2004ዓ.ም ለማህበሩ በጻፈው ደብዳቤ ላይ «በኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማህበር ውስጥ በአሁኑ ወቅት መደበኛ ስራዎች ባለመከናወናቸው ምክንያት ማህበሩ በአጠቃላይ የሚጠበቅበትን አገልግሎት መስጠት ከማይችልበት ደረጃ ላይ መድረሱን ለመረዳት ተችሏል።» ብሎ የገለፀ ሲሆን አያይዞም «መንግስት የችግረኛ አርበኞችን ችግር ለመቅረፍ የመደበውን አመታዊ በጀት ለሌላ አላማ ማዋል ፈጽሞ የተከለከለ መሆኑ እየታወቀ ለግንባታ ስራ በሚል እንዲወጣ መደረጉ የተፈጠረውን ችግር ለመፍታት በጋራ ያስቀመጥናቸው የመፍትሄ አቅጣጫዎችን ያልተከተለ» በማለት በደብዳቤው ላይ ገልጿል።

የማህበሩ አባላት «የመጠለያ ችግር ለመፍታት ጧሪ ደጋፊ የሌላቸው አርበኞች የአዲስ አበባ አስተዳደር 25 ቤቶች ቢሰጠንም በማህበሩ ፕሬዚዳንት ምክንያት ልናገኝ አልቻልንም። ለደካሞች ድጎማ መሰጠት ሲገባው በተለያዩ ህገ ወጥ-መገዶች ገንዘብ ወጪ እየተደረገ በርካቶች ለችግር ተጋልጠዋል» ሲሉ በተለይ ለፍትህ ገልፀዋል።

# የጠቅላይ ሚኒስትሩ የልማት ሰራዊት የሀገሪቱን አንጡራ ሃብት ሲያባክን



**ከኢንጂነር ዓብደልወሃብ ቡሽራ**

**ከመቀሌ**

በትግራይ ክልል የልማት ሰራዊት እንዲሆኑ ተብለው የተመደቡ አካላት የወረዳና የቀበሌ አስተዳዳሪዎች በህወሓት ካድሬ መሪነት ነው የሚንቀሳቀሱት:: የታዘዙትን የሚፈፅሙ ናቸው:: እነዚህ አካላት የተሰማሩበት የሥራ ዓላማ በገጠር በተመረጡ ቦታዎች በመስኖ የሚለማ ግብርና ማፋጠን የሚል ነው:: ለዚህ ተብሎ የታቀደው የልማት አቅጣጫ ደግሞ በተመረጡ የገጠር መንደሮች እያንዳንዱ ገበሬ በእርሻ ማሳው የውሃ ጉድጓድ መቆፈር እንዳለበት ነው:: በተጨማሪም ከደደቢት የብድር ተቋም የዉሃ ሞተር በብድር መልክ በመውሰድ ከጉድጓድ ውሃ እየመጠጠ ወደ እርሻ ማሳ እንዲያሠራጭ ታስቦ ነው:: ለዚህ ጉዳይ የተመደበው ባጀት እንደሚከተለው ነው፡-

1. አንድ ጉድጓድ ለመቆፈርያ፣ ለድንጋይ ግንባታና ለሲሚንቶ መግዣ የተመደበ የገንዘብ ልክ ብር 50,000 ነው

2. የውሃ ሞተር ከደደቢት የብድር ተቋም ገበሬው በብድር መልክ ይሰጠዋል ዋጋው አልታወቀም በተጨማሪም በቅድሚያ ለማዳበርያ መግዣ ብር 1300 ገበሬው እንዲከፍል ይደረጋል

**ከተመረጡ ቦታዎችና የዉሃ ጉድጓዶች ከተወሰዱት መካከል፡-**

1. ዓዲጉዶ አካባቢ እጅግ በጣም ብዙ ጉድጓዶች ተቆፈረዋል
2. ይሓ ድብድቦ አካባቢ ብዙ ጉድጓዶች ተቆፍረዋል
3. ዉቕሮማራይና ዓቃብሰዓት አካባቢዎች ብዙ ጉድጓዶች አሉ
4. ደንሽም ከዓቐብ ሰርዐ በታች ያለ ቦታ 25 ጉድጓዶች አሉ
5. ማይ ንፅቢና ዓዲናጉል አካባቢ 30 ጉድጓዶች ተቆፍረዋል
6. በለስና አካባቢው ጉድጓዶች በብዛት ተቆፍረዋል
7. ዓዲኢታይና አካባቢው 25 ጉድጓዶች ተቆፍረዋል
8. ዓዲገዳድና አካባቢው 20 ጉድጓዶች ተቆፍረዋል
9. ፈረስ ማይ አካባቢ ብዙ ጉድጓዶች ተቆፍረዋል

ከላይ የተጠቀሱ ቦታዎችና የዉሃ ጉድጓዶች የተሰሩት በሰው ኃይልና ኤክስካቬተር በመጠቀም ነው:: በጉድጓዶች መካከል ያለው ርቀት ከ50 እስከ 100 ሜትር ብቻ ነው:: ሥራው ከተከናወነ በኂላ በሞተሮች ዉሃ በመሳብ ማሳውን ማጠጣት ከተጀመረ አንድ ሳምንት ሳይሞላው ጉድጓዶቹ በሙሉ ደረቁ፡፡ ውሃ የሚባል የላቸዉም:: ስለዚህ የተዘራው የእርሻ ሰብል ሁሉ አረረ ቦታው ደረቀ፡፡ ገበሬው ከድካም በስተቀር ምንም ፋይዳ አላገኘም:: ለምሳሌ ያህል በፈረስ ማይ አካባቢ ከጥንት ጀምሮ በመስኖ ነው ህዝቡ የሚጠቀመው:: በአካባቢው የዉሃ ጉድጓዶ ከተቆፈሩ በኂላ ህዝቡ ይጠቀምባቸው የነበሩ የዉሃ ምንጮችና ጉድጓዶች በሙሉ ደረቁ በአሁኑ ጊዜ ህዝቡ የዉሃ ችግር አለበት::

ከላይ በተጠቀሱ አካባቢዎች ጉድጓዶቹ ይቅርና ቀደም ብለው ህዝቡ ይጠቀምባቸው የነበሩ የዉሃ ጉድጓዶችና የዉሃ ምንጮች በሙሉ ደረቁ አካባቢው ሁሉ ደረቅ ሆነ:: ይህ የሚያሳየው የህወሓት ካድሬዎች አስተሳሰብ ሁልጊዜ እኛ ነን አዋቂዎች ባይነታቸው ነው:: የልማት ሰራዊቱ ምንም ፋይዳ ሳይፈፅም ሥራው ከንቱና እርባና የሌለው ሆኖ ቀረ:: ይህ ዐይነት አሰራር ደግሞ በህወሓት የተለመደ ነው ምክንያቱም፤ ከጫካ ጀምሮ ይዞት የመጣው ፈሊጥ የተማረና ባለሙያ መናቀና ማንቋሸሽ ነው:: የተማረ ሰው እንደጠላት ይቆጠራል:: መካከለኛ ትምህርት ያለው ደግሞ ወላዋይ ይባላል:: የህወሓት ወዳጅ ድሃ ገበሬና ተራ ሰራተኛ ነው:: ይህ ደግሞ የኮሚኒስት አስተሳሰብን ቁልጭ አድርጎ ያሳያል:: በዚህ ምክንያት ነው እነዚህ ቦታዎችና የተቆፈሩ ጉድጓዶች ያለ ምንም ጥናት በህወሓት ካድሬ አመራር በዘፈቀደና በግምት የተሰሩት:: ጠቅላይ ሚኒስትሩ አሁንም ካድሬዎችን እያስተማሩ ናቸው የሚመስለው:: የሃይድሮጂኦሎጂ ሙያ ሳይኖራቸው አይቀርም የሚል ግምት አለ:: ነገር ግን በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የህክምና ተማሪ ነበሩ ሲባል ሰምቻለሁ:: እግረ መንገዳቸውን የከርሰ ምድር ዉሃ ጥናት ተምረው ሊሆን ይችላል:: ያም ሆነ ይህ የጉድጓዶቹ በካድሬዎች መመረጥ ያስገርማል፡፡

ጉድጓዶቹ በቅርብ ጥልቀት ዉሃ የተገኘባቸው በቤድሮክ ላይ የተከማቸ ነው:: በላዩ ላይ ያለው አፈር (Overburden) ይባላል:: ከዚያ በታች ከሆነ ደግሞ በአለት ዉስጥ ይሆናልና በሰው ኃይል መቆፈር አይቻልም:: ስለዚህ ግራዉንድ ዎተር አክዩፈር ለማግኘት ከተፈለገ ማሽን ያስፈልጋል:: ይህን ሁሉ ለማድረግና የከርሰ ምድር ዉሃ ፀባይ ለማወቅ ባለሙያ ያስፈልጋል::

በወይን መፅሄት እንደአነበብኩት ጠ/ሚኒስትሩ የተናገሩት 1/3ኛ የትግራይ መሬት በመስኖ ለማልማት ማቀዳቸው ጥሩ ነው:: ነገር ግን የመስኖ ዉሃ ከየት ነው የሚገኘው? ከከርሰ ምድር ውሃ በህወሐት ካድሬ ተፈልጎ የሚገኝ አድርገው አስበው ከሆነ ዉጤቱ እንዳየነው ነው የሚሆነው:: ባለሙያዎች አሰማርተው ሥራው የሚካሄድ ከሆነ የሚደገፍ ሃሳብ ነው:: ነገር ግን በህወሓት ካድሬዎች የሚሰራ ከሆነ ትርፉ ድካምና ገንዘብ ማባከን ይሆናል:: ኂላ አንድ ቀን የትግራይ ህዝብ ይፋረዶታልና በሰፈሩት ቁና ይሰፈራሉ::

ህወሓት ምንጊዜም ከስህተቱ ተምሮ አያውቅም:: ለምሳሌ ከዚህ በፊት የህወሓት ካድሬዎች የሆነ ሃገር ይጎበኙና ሆረዩ የሚባል የእርሻ ዘዴ ይዘው መጡ:: ከዚያ በኂላ የፈረደበት የትግራይ ገበሬ የሆረዩ ጉድጓድ ቆፍር ተባለ:: በክረምት ጊዜ ዉሃ ለማቆር ታስቦ ጉድጓዶቹ በላስቲክ እንዲሸፈኑ ተደረጉ:: ነገር ግን ሁላችንም እንደምናውቀው ነገሩ ሁሉ ከሸፈ:: ያንጊዜም ገበሬው ላስቲኩን ከደደቢት የብድር ተቋም በብድር ተገዶ ነው የወሰደው:: ከዚያ በኂላ ብድርህን ክፈል ተብሎ ከብቶቹንና እህሉን እየሸጠ ከፈለ:: መክፈል ያቃተው ስንቱ ገበሬ ነው ሃገር ለቆ እንዳይታሰር በመስጋት የሸሸው:: በአሁኑ ጊዜ የሆረዩ ላስቲክ በየከተማው የ(DS-tv) ኣዳራሽ መስሪያ ሆኖ ይገኛል:: በገጠርም የእንስሳ ቤትና ለደሳሳ ቤቶች መጠገኛ ነው የሆነው::

(Hydrogeology and groundwater) ጥናት በህወሓት ፖለቲካ ትምህርት ቤት ይሰጣል መሰለኝ እነዚህ ካድሬዎች ስለከርሰ ምድር ዉሃ ጠለቅ ያለ ዕውቀት ያላቸው በመምሰል በዘፈቀደ ሥራ የሚከናወን ይመስላቸዋል:: የከርሰ ምድር ዉሃ እንቅስቃሴ በጣም አዝጋሚ መሆኑ አልገባቸውም:: እያንዳንዱ ጉድጓድ (pump-test) መደረግ ነበረበት፤ የሞተር አቅም ለማወቅና ከጉድጓዱ ዉሃ ብዛት ተመጣጣኝ ለማድረግ እንዲቻል:: ይህ ሁሉ ሳይደረግና ምንም ጥናት ሳይደረግ ወደ ግምታዊ ተግባር ይገባሉ:: የከርሰ ምድር ዉሃ ባህርይና ፀባይ ከቦታ ቦታ ይለያያል:: ዝምብሎ በመላምት የሚሰራ አይደለም:: ስለዚህ ነው የከርሰ ምድር ዉሃ ጥናት በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ትምህርት የሚሰጠው:: እንደዚህ መሆኑን ካድሬዎች አያውቁም::

በዚህ አጉል አስተሳሰብ ስንትና ስንት የሃገር ሃብት ያለ አግባብ ይባክናል፡፡ ምክኒያቱም እነዚህ ካድሬዎችን የሚቆጣጠራቸው ሰው የለም:: በጠቅላይ ሚኒስትሩ ስለሚመሩ ማን ደፍሮ ይነካቸዋል:: ከዚህ በፊት የሆረዩ ሥራ ውጤት አልባ በሆነበት ጊዜ ማንም የጠየቃቸው የለም:: አሁንም ማንም

ወደ ገፅ 13 ዞሯል »

# አጋር ያጣ ህዝብ



**አቶ አስገደ ገ/ስላሴ**

የኤርትራ መንግስት ከ1992 ዓ.ም. ከአልጀርሱ ስምምነት ጀምሮ እስከ 2004 ዓ.ም. ድረስ ለ12 ዓመታት ያህል ወደ ኢትዮጵያ በቀጥታ ዘልቆ በመግባት በሰሜኑ አገራችንና በሰሜን ምስራቅ አገራችን ከቡሬ ግንባር እስከ ሁመራ በ1300 ኪሎሜትር በተዘረጋው የኢትዮጵያ የመከላከያ ወረዳ ዘልቆ በመግባት በኢትዮጵያ ህዝቦች በተለይ ደግሞ የአፋርና የትግራይ ህዝቦችንና ወጣቶችን አፍሶና አፍኖ በመውሰድ በተጨማሪም የቀንድ ከብቶች፣ በጎችና ፍየሎች፣ የጋማ ከብቶች፣ እህልና ሌላ የህዝብ አንጡራ ሃብት በመዝረፍ ለሰራዊቱ ቀለብ አድርጎታል::

ይህ የሻዕብያ የወንጀል ተግባር የህወሓት ኢህአዴግ መንግስት ምንም የመቆርቆር ምልክት ሳያሳይ በአጋሜ፣ በአድዋ፣ በአክሱም፣ በሽሬ፣ በወልቃይትና በአፋር አውራጃዎች ማለትም የኤርትራ ኩታ ገጠም በሆኑ አካባቢዎች እየደረሰ ያለው የወጣቶች መታፈስ፣ መገደል፣ ንብረት መዘረፍ ከመጤፍ ሳይቆጥር ይህን የኢትዮጵያውያንን ችግር ወደ ጎን በመተው በሞቃድሾ፣ ባይደዋ፣ ዳርፉርና ደቡብ ሱዳን ያደረጋቸውን ክንውኖች በመዘርዘር ለዓመታት ያህል የኢትዮጵያን ህዝብ ለማምታታት ሞክሯል::

የአገራችን ከፍተኛ ባለስልጣኖችም ይህን የሻዕብያን ወንጀል በመሬት ላይ እንዳልተፈጠረ ሲናገሩ ቆይተዋል:: ለዚሁ እንደ ማስረጃ በ11/04/2004 ዓ.ም. የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዲኤታ አምባሳደር ብርሃነ ገ/ክርስቶስ የኤርትራ መንግስት እድሜው የሚያበቃው ለሁለተኛ ጊዜ ጦርነት የሞከረ ቀን ነው ብለውናል:: የሻዕብያ መንግስት ግን ላለፉት 12 ዓመታት ወደ ኢትዮጵያ ዘልቆ በመግባት ብዙ ግዜ ጦርነት አካሂዷል፡፡ወታደራዊ ጥቃትም ፈፅሟል:: በሺህ የሚቆጠሩ ወጣቶችን አፍሶ በኤርትራ የባሪያ አገዛዝ ግፍ እየፈፀመባቸው ይገኛል:: በብዙ ሚልዮኖች የሚገመት የህዝብ አንጡራ ሃብት ተዘርፏል:: ህዝብ አድኑን ቢልም መንግስታችን ግን ጥሪውን ሊሰማ አልቻለም::

በሌላ በኩል በጥር ወር 2004 ዓ.ም. መጀመሪያ አካባቢ የሻዕቢያ መንግስት ለጉብኝት ወደ አፋር ኤርታሌ ከተጓዙት መካከል 5 ሰው ገድሎ ሁለት ፈረንጆችና ሁለት ኢትዮጵያውያንን ጠልፎ ሌሎችን ሲያቆስል የአገራችን ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ በኤርትራ መንግስት ላይ የነበረን ትዕግስት ተሟጥጧል፤አስፈላጊ እርምጃም እንወስዳለን ሲሉ ሰነበቱ::

የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃንም አምባሳደር ብርሃነ ገ/ክርስቶስና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ የተናገሩትን በተደጋጋሚ ሲደሰኩሩ ባጁ:: በተለይ በአፋሩ ጥቃት ስለ ፈረንጆቹ ብዙ ሲነገር ስለተጠለፉት ሁለት ኢትዮጵያውያን ግን የተነገረ ነገር የለም:: የት እንዳሉም አይታወቅም፡ ፡ ጠፍተው ቀርተዋል:: ለዜጋ ተቆርቋሪነት ይህ ነው?::

በቅርብ ግዜም በሚያዝያ ወር መጀመሪያ ላይ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በፓርላማ በቀርቡበት ወቅት ስለ ኤርትራ መንግስት ብዙ ጥያቄ ቀርቦላቸው 70 ጊዜ ያህል ከሻዕቢያ ጋር መደራደራቸውን ተናግረዋል፡ ፡ እኔ እስከ ማውቀው ድረስ እንኳ 15 ጊዜ ድርድር ለማድረግ ተሞክሯል ብለዋል::

የሻዕቢያ መንግስት ከእንግዲህ ወዲህ አንደራደርም ብሎ ከተናገረ፤ የእኔ ጥያቄዎች:: መንግስታችን ለምን መደራደር ፈለገ? ድርድሩስ ለምን በግልፅ የኢትዮጵያ ህዝብ በሚያውቀው መንገድ አይካሄድም? ለምንስ ለሻዕቢያ ይህን ያህል መንበርከክ ያስፈልጋል? የሚሉ ናቸው፡፡

እንዲሁም በሌላ ወቅት ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ በሰሜን ምዕራብ ትግራይ በወርቅ ቁፋሮ ላይ ከተሰማሩት መሀከል ከ100 በላይ ዜጎች በሻዕቢያ መንግስት ታፍሰዋል ብለዋል:: በእዚህ ጉዳይ ላይ ለጠቅላይ ሚኒስትር መለስ የማቀርባቸው አንዳንድ ጥያቄዎች አሉኝ፦

1. ሻዕቢያ በሰሜን አገራችን በተለይ በትግራይና በአፋር አርማጭሆ 12 ዓመት ሙሉ በሺህ የሚቆጠሩ ዜጎችን አላፈሰም? በብዙ ሚሊዮን ስለሚገመተው የህዝብ አንጡረ ሃብት ዝርደፊያ ለምን አልተናገሩም?

2. በአድያቦ፣ በሁመራ፣ በዓዲዳዕሮ፣ በወልቃይት፣ በዓዲጉሽ፣ በባድመ አካባቢ የተቃጠሉ በመቶ የሚቆጠሩ ተሽከርካሪዎችስ ጉዳይ ለምን ይፋ አላደረጉም?

3. ለምን ከኤርትራ ተሰደው ለሚመጡ ኤርትራውያን የሚሰጣቸው ክብር ለኢትዮጵያውያንም አይሰጣቸውም? የታፈሱትን ከ100 በላይ የሚሆኑ ዜጎች ጉዳይ ተደብቆ ቆይቶ በፓርላማ ስብሰባ እንደተራ ንግግር አድርገው ያቀረቡትስ ለምንድን ነው?

99.6% የሚሆኑት የኢህአዴግ የፓርላማ ተወካዮች ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከ100 በላይ ዜጎች ታፍነዋል ሲባሉ ፊታቸው የንዴትና የዜጎች ተቆርቋሪነት ምልክት አላሳየም ነበር:: በአንፃሩ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በተቃዋሚዎች የቀረበን ጥያቄ በቁጣና በስድብ ሲመልሱ የሳቅ ጫጫታ ያሰሙ ነበር:: ለዚህም ነው በዚህ ፅሁፍ አጋር ያጣ ህዝብ በየተሰማራበት የመንግስት ስራ ዋስትና የተነፈገው ህዝብ ይሆናል ያልኩበት ምክንያት::

**የሻዕቢያ እርምጃና አገራዊ ድፍረት**

የአገራችን ባለስልጣኖች ጠ/ሚኒስትር መለስን ጨምሮ የሻዕቢያ መንግስት እድሜው የሚያበቃው ለሁለተኛ ጊዜ ጦርነት የከፈተብን እንደሆነ ከመናገር ባለፈ በኤርትራ ላይ የነበረን ትዕግስት ተማጥጧል፣ በኤርትራ መንግስት ላይ ተመጣጣኝ እርምጃ እንወስዳለን፣ ለኤርትራ መንግስት የመጨረሻ ማስታገሻ እንሰጠዋለን ብለዋል:: ይህን የማይተገበር ዲስኩር እያሰሙን ባሉበት በዚህ ወቅት ግን የሚከተሉት ጉዳቶች ተከስተዋል፡፡

1. በ13/8/2004 ዓ.ም. እለተ ዓርብ ሌሊት ለቅዳሜ አጥቢያ (ከሌሊቱ 5 እስከ 6 ሰዓት ባለው ጊዜ) ኑሯቸውን ለመግፋት ወርቅ በመልቀም በተሰማሩ ከ158 በላይ የሆኑ የዩኒቨርስቲ ምሩቃን፣ ከ8ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች፣ የገጠር ወጣቶች እና አዛውንቶች ታፍነው ተወስደዋል::

2. በ14/8/2004 ዓ.ም. በእለተ ቅዳሜ ለእሁድ አጥቢያ (ከለሊቱ 8 ሰዓት አካባቢ)እንደዚሁ በወርቅ ለቀማ ተሰማርተው የነበሩ 43 ዜጎች ታፍነው ኤርትራ ገቡ:: ተከዜን ተሻግረው ሊያመልጡ ከሞከሩት ውስጥ በጥይት የተመቱ አሉበት፡፡( ከነዚህም ውስጥ መረስዕ መኮንን ቆስሎ ሲያመልጥ ወንድሙ ኪዳነ መኮንን፣ አለምሸትና ይልማ የተባሉት ማምለጥ ችለዋል:: በአጠቃላይ ከታፈሱት 201 ወጣቶች መሀከል አንድ ሴት አለችበት::)

የነዚህ ዜጐች መታፈስና መታፈን በአሁኑ ጊዜ በአድዋ፣ በአክሱም፣ በሽሬ፣ በወልቃይት አውራጃዎች፣ ወረዳዎችና ቀበሌ ነዋሪዎች ላይ እጅግ ስጋት ፈጥሯል፡፡

በተጨማሪም አሁን ለአገራችን መሪዎች ደግሜ ልጠይቃቸው፣ ባለፈው 12 ዓመታት ብዙ ዜጎች ታፍነው ተወስደዋል ነገር ግን ይህ ዜና ከኢትዮጵያ ህዝብ ተደብቆ ቆይቷል:: እስከ አሁን ድረስ 301 የሚሆኑ ዜጐች እንደ እቃ ታፍሰው ተወስደው በሻዕቢያ የባርያ አገዛዝ ስር ሲወድቁ፦

1. የኢትዮጵያ መንግስት ለምን መግለጫ አልሰጠም?

2. መሪዎቻችን ሲናገሩ እንደ ነበረው በሻዕቢያ ላይ እርምጃ ለምን አልወሰዱም?

3. ዜጐቻችን ከታፈኑ ብዙ ቀናት ሆኗቸዋል፡ ፡ የመታፈናቸው ዜና ለምን መደበቅ አስፈለገ፡፡

4. አሁንስ ከአፋር እስከ ሑመራና መተማ ያለው ህዝባችን ሰርቶ ወደ መኖሪያ ቀየው ለመመለስ ዋስትናው ምንድን ነው?

የእስራኤል እና የአሜሪካንን መንግስታት ብንመለከት ለዜጎቻቸው ያላቸውን ጥልቅ ክብር እናስተውላለን፡፡ የአሜሪካ መንግስት በሶማሊያ ታጣቂዎች የታፈኑበትን ዜጎች በከባድ መስዋዕትነት እንዴት እንዳስለቀቁ እናስተውሳለን፡፡ እስራኤልም ለአንድ ወታደር ስትል የከፈለችውን መስዋዕትነት ተመልክተናል፡፡

የእኛ መንግስት ከ301 በላይ ዜጐች ሲታፈሱበት ምንም ሊያደርግ ካልቻለ ይህ ህዝብ ለማን ይጮኽ? የእነ አምባሳደር ብርሃነ እና የአቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ የተሟጠጠው ትዕግስት የትኛው ነው? ጠቅላይ ሚኒስትር መለስስ ተመጣጣኝ እርምጃ መቼ ነው የሚወስዱት?::

የኢትዮጵያ ህዝብስ ይህን ዘግናኝ የሻዕቢያ እርምጃ ሰምቶ እንዳልሰማ፣ አይቶ እንዳላየ ለምን ዝም አለ? ለምን አይጠይቅም? የኢትዮጵያ ህዝብ ኑሮውን ለመግፋት በተለያየ ቦታ ተበታትኖ ግድያና ግፍ ሲደርስበት ማን ጠበቃ ይሁንለት ዜጐች ለዜጐቻቸው ጥብቅና ካልቆሙ አንድነትና መተሳሰቡ የት ላይ ነው? በአፋር፣ በትግራይ፣ በኦሮሞ፣ በኣማራ፣ በሱማሌ፣ የደቡብ ህዝቦች አደጋ ሲደርስባቸው የኢትዮጵያ አደጋ አይደለምን? የኢትዮጵያ ህዝብ በ1990ዓ.ም ሻዕቢያ ሲወረን ጊዜ የነበረው ቁጭትና መነሳሳት የት ገባ? ሻዕቢያ በዜጐቻችን እየፈፀመ ያለው ዘግናኝ እርምጃስ መቋጫው የት ነው? ይህ ጉዳይ በመንግስትም፣ በ80 ሚሊዮን የኢትዮጵያ ህዝብም መልስ ማግኘት አለበት::

የአገራችን ምሁራን በተለይ የሕግ ባለሙያዎች በህዝባችን ላይ የሚፈፀመውን ጨካኝ ድርጊት ከሕግ አንፃር አይታችሁ ለፍትህና ለዜጐች ክብርና መብት ስትሉ ብትሟገቱለት ላስተማራችሁ ህዝብ ውለታ እንደ መክፈል ይመስለኛል::

የሚወስዱት? በጠረፍ የሚገኙ የኢትዮጵያ መከላከያ እና ሌሎች የፀጥታ ኃይሎች በተዘረጋው የቀበሮ ጉድጓድ መሽገው እያሉ በሻዕቢያ መንግስት ይህን ዘግናኝ እርምጃ በህዝባችን ላይ ሲወስድ፣ ሉዐላዊ ድንበራችንን ሲደፍር አስፈላጊ እርምጃ ባለመውሰዳችሁ በኢትዮጵያ ህዝብ የነበራችሁን ታማኝነት ጥያቄ ምልክት ውስጥ እንዳይጥለው የነዚህን 301 ዜጐች ህይወት ትታደጉት ዘንድ ህዝብ ይጠብቃችኂል::

በሌላ በኩል በአገራችን ያላችሁ ለፍትህና ለዲሞክራሲ ቁመናል የምትሉ ተቃዋሚዎች በዚህ በሰሜንና በሰሜን ምስራቅ አገራችን የሻዕቢያ መንግስት በህዝባችን ያደረሰውንና የሚያደርሰው ግፍና ዓፈና፣ መታፈስ፣ መገደል፣ ሃብት መዝረፍ የኢትዮጵያን መንግስት እንዝህላልነትና ቸልተኝነት በሚመለከት በመቃወም መግለጫ ከመስጠት በመቆጠባችሁ በህዝብ ዘንድ የሚኖራችሁን ታማኝነት በጥያቄ ምልክት ዉስጥ አስገብቶታል:: በዚህ ጉዳይ ያላችሁን አቋም ለሃገራችን ህዝብና የዓለም ማሕበረሰብ ብታሳውቁ መልካም ነው እላለሁ::

በዚህ ጉዳይ ቀጥተኛ ተጠያቂ የሚሆነው የትግራይ ክልል አስተዳደርና በሥሩ የተዘረጋው መዋቅር ሲሆን በአጠቃላይ ክስተቱ የክልሉ አስተዳደር ለትግራይ ህዝብ ደንታ ቢስ መሆኑን ያረጋገጠበት አጋጣሚ ነው$ ለምን ቢባል ዜጎቻችን በአገራቸው በሰላምና ደህንነታቸው ተጠብቆ እንዲኖሩ፣ ሰርተው ቤተሰቦቻቸውን እንዲያስተዳድሩ ጥበቃ ያደርግላቸው ዘንድ በተገባ ነበር፡፡ የሻዕቢያ መንግስት ሉዐላዊ ድንበራችንን ጥሶ በመግባት ዜጎችን አፍኖ እስኪወስዳቸው ድረስ የክልሉ መንግስት ለነዋሪዎቹ ሊደርስላቸው አልቻለም$ ዜጎች በግድ ከተወሰዱም በኂላ አስተዳደሩ ምንም ትንፍሽ አለማለቱ ነገሩን የበለጠ አሳዛኝ ያደርገዋል$ ይህ ክስተት ከአሁን በፊትም ለ12 ዓመታት ሙሉ የቀጠለ መሆኑ የቅርብ ጊዜ ተሞክሮ ብቻ ላለመሆኑ ማሳያ ነው$ በሰላማዊ መንገድ ለሚታገለው ‹‹ዓረና ትግራይ›› ፓርቲ በራሪ ፅሑፎችን ለማደል ሲፈልግ ለምን ከህዝብ ጋር ተገናኛችሁ እያለ ሲያስርና ሲያንገላታ ይውላል$ ከዚህ በተጨማሪም በአካባቢው የሚኖሩ የዓረና አባላት በፖሊስና ደህንነት ኃይሎች ጭምር እየታገዘ አባላቶቹ በገቡበት ሻይ ቤት ይሁን ሌላ ቦታ እየገቡ ከማን ጋር ተገናኙ ምን ብለው ተናገሩ እያሉ ይከታተላሉ$ ሌላው ይቅርና የክልሉ ፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር አቶ ዘአማኒኤል ለገሰ ለምን በሕጋዊ መንገድ የሚንቀሳቀሰው የዓረና ኣባል የፓርቲያችንን ልሳን የሆነው ወረቀት ሲያድል ትይዙታላችሁ ብለን ስንጠይቃቸው የሚያሳዝን መልስ ነው የሰጡን፡ ፡ ‹‹እያንዳንዱን እንቅስቃሴያችሁን ካላሳወቃችሁን አሁንም ታገኙታላችሁ›› ነበር ያሉን ፡፡ታድያ አሁን ኣቶ ዘኣማኒኤል ምን ነካቸው ሃይላቸውን በተገቢው ኣሰማርተው ለምን ፖሊሱ የህዝቡን ደህንነት እንዲጠብቅ ኣያደረጉም? አሁን ታፍነው የተወሰዱት 201 ወጣቶች አቶ ዘኣማኒኤል ለገሰ የትግራይ ክልል ፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር ለዚህ ቀውስ መፍትሄ ይፈሉግለት ይሆን? የትግራይ ክልል አስተዳደርስ?

አጋር ላጣው ህዝባችን ምህረቱን ይስጠው

# ይድረስ ለ/ወሮ አዜብ መስፍን … …ያንን ነገር እንዴት አደረጉልኝ?



አቤ ቶኪቻው
abeto2007@yahoo.com

ውድ የፍትህ ጋዜጣ አንባቢ ወዳጆቼ እንዴት አላችሁልኝ? "እኔስ አለሁ አለሁ አለሁ እንደምንም እግዜር ያመጣውን ሰው አልችል አይልም" የሚል ዘፈን የሚዘፍንልን ሁነኛ ሞዛቂ አጣን አይደል…? ለማንኛውም አንተ እንዴት ነህ ብለው የጠየቁኝ እንደሆነ እኔው ራሴ አዜማታለሁ!

ይህ ደብዳቤ ለቀዳማዊት አዜብ መስፍን በታላቅ ትህትና እና አክብሮት የተፃፈ ነው። ከሁሉም በላይ ግን ለቤተመንስግስቱ ቤተሰቦች ያለኝን የላቀ ፍቅር እና አክብሮት እንዲሁም ታማኝነት የሚያሳብቅ በመሆኑ ይህንን ሀሳብ የምትቃወሙ ወዳጆችን ከወዲሁ ይቅርታ መጠየቅ ተገቢ ነው።

ጀመርኩ፤

ክብርት ወ/ሮ አዜብ መስፍን እንዴት ሰነባበቱልኝ? ባለፈው ግዜ ይድረስዎ አይድረስዎ እንጃ አንድ መልዕክት ሰድጄልዎ ነበር። እርግጥ ነው ደብዳቤዬን በዌብ ሳይቶች ላይ እንዲታተም አደረግሁ እንጂ በአድራሻዎ አላኩሎትም። ታድያ እነዚህ ድረ ገፆች ደግሞ ወደ ኢትዮጵያ እንዳይገቡ ክልከላ የተደረገባቸው በመሆናቸው፤ ምናልባት ለገበያ፣ ወይም ቤተሰብ ጥየቃ፣ ወይም ደግሞ አንዱን ቅዳሜና እሁድ ንፋስ ለመቀበል ዱባይ ወይ ቻይና ወይም እንግሊዝና አሜሪካ ብቅ ካላሉ በስተቀር አራት ኪሎ ቁጭ ብለው በድረ ገፅ የታተመ ደብዳቤዬ ላይደርሶት ይችል ይሆናል ብዬ እሰጋለሁ።

አሁን አሁንማ ያው እንደሚያውቁት "ኢንሳ" የተባለው ዌብሳይቶችን በመዝጋት የሚተዳደረው መስሪያቤት እንኳንስ የተጠናከሩ ዌብ ሳይቶችን ይቅርና እንደኔ ያለን ምስኪኖች ወግ ይድረሰን እና ወግ እናወጋ ብለን የከፈትናቸውን ሚጢጢ ብሎጎች ሁሉ እየዘጋ ከምንወደውና ከሚወደን መንግስታችንም ሆነ ህዝባችን የማለያየት ስራ እየተሰራብን ይገኛል።

የምሬን ነው የምልዎ ይሄ ክፋት ነው። ለምን ከመንግስታቸው ጋር ተግባቡ… ለምን ደብዳቤ ተላላኩ ለምን ተስማሙ የሚል ምቀኝነት። እኔ በበኩሌ ዘወትር እርስዎን እና ጠቅላይ ሚኒስትሬን ጨምሮ መላው የኢህአዴግ አባላት በስራ የዛለ አዕምሯችሁን ዘና ለማድረግ እንደተጋሁ ነው። (እዝች ጋ ታይፕ አልገደፍኩም አይደል…? ይቺ የታይፕ ግድፈት እባክዎ ከብዙ ሰው እያቀያየመችኝ ነው። በተለይ ስራ እና ሴራ እየተመሳሰሉብኝ ስቸገር ባዩኝ…! የኛ ሰው ደግሞ ቶሎ ነው የሚከፋው። … አይ አሁን ግን ልክ ነኝ። ሴራ አላልኩም ስራ ነው ያልኩት።) እናልዎ በስራ የዛለ አዕምሯችሁን ትንሽ ዘና እንዲል የማላደርገው ጥረት የለም።

ታድያ ይገርምዎታል የእኔ ብሎግ እንኳ ሳይቀር ወደ ኢትዮጵያ እንዳይገባ ተከልክልዎሎታል። እኔማ የለም ተሳስተው ነው የእኔ ባይመስላቸው ነው… ብዬ ድጋሚ ስከፍት፤ አሁንም ሲዘጉት፣ አሁንም ስሞክር፤ አሁንም ሲዘጉት ቢያምኑኝም ባያምኑኝም አስራ አንድ ግዜ ተዘግቶብኛል። ከዚህ በላይ ከሄድኩኝ ከሀገሪቱ የእድገት ቁጥር ጋር መፎካከር ነው ብዬ ለግዜው ብሎግ ከፈታውን ተወት አድርጌዋለሁ።

እሜትዬ እኛ ኢቲቪ የፈለገውን ሲያቀርብ "ብሎክ" ማድረጊያ ሪሞቱ አጠገባችን እያለ ይሁን ለኛው ብሎ ነው በሚል ቅን አመለካከት ያሻውን ቢናገር ያሻውን ቢያወራ ዝም ብለን እንሰማለን እንጂ አንዘጋውም። በርግጥ ብዙ ግዜ የቴሌቪዥናችን ፕሮግራሞች እርሾ ይበዛባቸዋል መሰለኝ ሆድ ይነፋሉ። ቢሆንም ግን ተመልክተን ከጨረስን በኋላ ቀንዶ ወይም እናትና ልጅ አረቄ ጠጥተን እንበትነዋለን እንጂ ፕሮግራሙን "ብሎክ" አድርገን ወይም አቋርጠነው አናውቅም።

ውይ ኢቲቪን ሳነሳ ምን ትዝ አለኝ መሰልዎ አንዱ ፀሀፊ በቅርቡ የፃፈውን አይቼ እንዴት እንዴት ስበሳጭ እንደነበር ቢመለከቱኝ፤ ምን ያህል ተቆርቋሪዎ እና ወዳጅዎ እንደሆንኩ ይረዱልኝ ነበር። በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የሚተላለፈውን ገበና እና ሰው ለሰው ድራማ መቼም ሳይከታተሉት አይቀሩም…! እናልዎ በዛ ላይ ያሉ እኩይ ገፀ ባህሪ ሆነው፤ ነገር ግን ደግሞ ሁሌ ሲሳካላቸው የሚታዩ ሰዎች አሉ። የሰው ለሰዉ አስናቀ እና የገመናዋ ለምለም። ታድያ ይህ ያበሳጨኝ ክፉ ፀሀፊ አቶ አስናቀን ከአቶ መለስ ጋር ወ/ሮ ለምለምን ደግሞ ከእርስዎ ጋር አመሳስሎ አላየሁትም መሰልዎ…!? በእውነቱ በብስጭት ደሜ ከዋጋ ግሽበቱ በላይ ነው የጨመረው።

ታድያ ከላይ እንዳልክዎ በየድረገፁ የምንለጥፈው ፅሁፍ ወደ ኢትዮጵያ እንዳይገባ ሲከለከል ለእርስዎ እና ለጠቅላይ ሚኒስትሬም የምልከው መልዕክት ሳይደርስ ይቀራል ብዬ እሰጋለሁ። ወይስ ቤተ መንግስቱ ከኢትዮጵያ ውጪ ነው የሚገኘው…? አንዳንድ አሽሟጣጮች እንደሚሉት ከሆነ አገሪቷ ላይ የሚመጣ ችግር አንድም ግዜ ጎብኝቶት ስለማያውቅ ቤተመንግስቱ ኢትዮጵያ ውስጥ ነው ለማለት አያስደፍርም ይላሉ።

ለምሳሌ የገበያ ዋጋ መናር ለቤተመንስግስት ሰዎች ምናቸውም አይደለም፤ ምክንያቱም ገበያቸው ዱባይ እና ቻይና ነው እያለ ሰዉ ያልተጠየቀውን ሲያወራ ቢሰሙት ይደነቃሉ። ይቺ ይቺ እርስዎን ለመንካት ነው። እኔ ግን እከራከርልዎታለሁ። ለራስዎ "በአለም ላይ ደሃ ከሚባሉ መሪዎች መካከል አይደሉ እንዴ?" •ረ ይልቁንስ ሰሞኑን የሰማሁትን ሳልነግርዎ… እኚያ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ ደቡብ አፍሪካ የሄዱ ግዜልዎ… ወደ አስር ሺህ ዶላር አውጥተው ጌጣጌጥ ሲገዙ ነበር አሉ። ይሄ ነገር ግን ለድርጅታችን ስም ጥሩ ነው ይላሉ? ለአባይ መዋጮ ሰዉን በምናስጨንቅበት በዚህ ግዜ ባለስልጣኖቻችን ይህንን ያህል ወጪ ማውጣታቸው መልካም ነው…? በእውነቱ ጥሩ አይመስለኝም። በርግጥ እኔ በበኩሌ ግን ይሄንን የሰማሁ ግዜ ድሮ ድሮ በእንዲህ ያለው ነገር የሚጠረጠሩት እርስዎ ስለነበሩ ጎሽ ትንሽ ከሳቸው ራስ ላይ ገለል ይላሉ ብዬ ውስጥ ውስጡን ደስ ብሎኝ ነበር።

ምን ዋጋ አለው በነጋታው ሌላ ወሬ መጥቶ የእርስዎን ስምም አደባባይ አገኘሁት። በዕርግጥ እንደተለመደው ስምዎ ሲነሳ የሰማሁት ከቅንጦት ገበያ ጋር ተያይዞ ባለመሆኑ ተደስቻለሁ ቢሆንም ግን… በአደባባይ ስምዎ ሲነሳ ቅር ይለኛል። ምን መሰልዎ…? ነፍሱን ይማረውና ከቀድሞው የደህንነት ሹም አቶ ክንፈ የሚወለደው ልጅ… እ! እሱልዎ በየ ጋዜጣውና መፅሔቱ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ላይ ይዝታል አሉ። ኧረ እንደው ሌላ ሰው አይስማን እንጂ እንደርሱ አባባልማ ለአባቱ ሞት ሁሉ ተጠያቂ የሚያደርገው ጠቅላይ ሚኒስትራችንን ነው። እኔማ በየድረ ገፁ ላይ ይህንን ባየሁ ግዜ በእውነቱ ይሄ ጉርምስና ነው…! ብዬ ወቀስኩት። በምን አነሳሁት እቴ…

የኔ ነገር አንድ ግዜ ጨዋታ ከጀመርኩ እና እህ… ብለው ከሰሙኝ መቼም ማብቂያም የለኝ፤ ወደ ዋናው ቁም ነገሬ ስመጣ ያንን ነገር እንዴት አደረጉልኝ ወ/ሮ አዜብ? ጠቅላይ ሚኒስትሩን እንዲመክሩልን ጠይቄዎት ነበር። ባለፈው ግዜ እንዳልኩዎ በእርስዎ ያምራል። እኛ ያሻንን ያህል ብንለፋ እርስዎ በሚስት ብልሀት የሚመክሩትን ያህል አይሆንልንምና ባለቤትዎን በዘዴ በዘዴ ይምከሩልን! ብዬዎት ነበር።

እውነቴን ነው የምልዎ ወ/ሮዬ እኛ ከአንጀታችን በክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ ፍቅር የወደቅነውን ያህል ብዙ ሰዎች ደግሞ ከልባቸው እየተቀየሟቸው ነው። ይህንን በስንትና ስንት ስለላ ያገኘሁት መረጃ መሰልዎ…! ባለፈው እንዳልኩዎ የሰዉም ሁናቴ የሳቸውም ምላሽ በዚሁ ከቀጠለ ወደፊት እንኳንስ ህዝቡ እና የገዛ ጉርሻቸው እሺ ብሎ አልጠቀለል የሚላቸው ግዜ ሊመጣ ይችላልና ከአሁኑ ተመካክረን አንዳች ዘዴ እንዘይድ በሚል ነው ይህንን ደብዳቤ መፃፌ!

ይኸውልዎ ወይዘሮ አዜብ ህዝብ ሲከፋው፤ ህዝብ ሲበሳጭ ምን ሊያደረግ እንደሚችል ጠቅላይ ሚኒስትራችንም ጠንቅቀው ያውቁታል። እና ሳስበው ከእርስዎ ብዙ የሚጠበቅብዎ አይመስለኝም። እርሱን ብቻ ያስታውሷቸው እርሳቸው አንድም ስራ ስለሚበዛባቸው አንድም በሌላ ሌላ ምክንያት ሊረሱት ይችላሉ።

ቀዳማዊት እመቤት ሆይ መፅሐፍ ቅዱስ ላይ መፅሐፈ አስቴር በሚለው ምዕራፍ ውስጥ የአስቴርን ታሪክ አንብበውታል? "ምን ይሄ የቤተመንግስት ጣጣ እኮ ለእንዲህ ያለ መንፈሳዊ ምንባብ ግዜ አይሰጥም" ብለው እንደሚያጉረመርሙ በጠረጠርኩ። አይዞት እኔ እያለሁ ሀሳብ አይግባዎት ትንሽ ቀንጭቤ ከታሪኩ እንደሚከተለው እነግርዎታለሁ፤

በዛን ወቅት አርጤኬስ የሚባል ንጉስ በአስቴር ፍቅር ወደቀና ንግስት አደረጋት። እሷም በዛ እየኖረች ሳለ አሳዳጊዋ መርደኪዮስም ሆነ አጠቃላይ ህዝቧ እና ወገኗ ለታላቅ መከራ ተዳረጉ። ሐማ በተባለ የንጉሱ ሰው (ልክ በአሁኑ ግዜ እኛ ስራ አስፈፃሚ አካላት እንደምንላቸው ሹማምንት መሆኑ ነው) ህዝቡን ክፉኛ ስጋት ላይ ጣለው። እንደ እቅዱና አሳቡ አባቷን መርደኪዮስን ጨምሮ ህዝቡን በሙሉ ማጥፋት ነበር። በዚህ ግዜም ህዝቡ "አስቴር ወገናችን አንቺ በቤተመንግስቱ ውስጥ ነሽና እባክሽ ለምኝልን! ሊያጠፉን ቆርጠው ተነስተዋል…!" ሲሉ ወተወቷት። አባቷ መርደኪዮስም የሚመጣባቸውን መከራ በማሰብ የተነሳ ማቅ ለብሶ ሰነበተ።

የዛኔ አስቴር በንጉሱ ዘንድ ያላት አቅም እርስዎ ዛሬ በአቶ መለስ ላይ ያልዎትን አያክልም ነበር። እንደ ልቧም ገባ ወጣ እያለች "ያንን ነገር እንዴት አደረግሽው?" ብላ መጠየቅ አትችልም። በዚህም የተነሳ ለንጉሱ "በህዝቤ ላይ የተጫነውን መከራ አንሳልኝ" ብላ ጥያቄ ከማቅረቧ በፊት ለድፍረቱም ለስኬቱም እንዲሆን ህዝቡ ሶስት ቀን ሶስት ለሊት እንዲፆም አዘዘች። እርሷም ፆም እና ፀሎት አደረገች። ከዛም ለንጉሱ እራት ግብዣ ካደረገችለት በኋላ፤ "ወገኖቼ በአንተ ትዕዛዝና በአስፈፃሚህ ሐማ የተነሳ ሊያልቁ ነው እባክህን ይህንን አታድርግ አለችው።" ይገርምዎታል ወድያውኑ ልመናዋን ሰማት።

ወ/ሮ አዜብ ህዝብዎ ላይ መከራ ተጭኗል። አጠቃላይ የኢትዮጵያ ህዝብ በታላቅ አበሳ ውስጥ ነው። ከዛም ወረድ ብለን ይበልጥ ወደ እርስዎ ህዝብ ጠጋ እንበል ካልን የወልቃይት ጠገዴ ሰው መከራውን እያየ ነው። የመላው ትግራይ ህዝብ አበሳውን እየቆጠረ ነው። አማራው ጉራጌው ኦሮሞው ከንባታው ሃድያው እውነት እውነት እልዎታለሁ አንድም የደላው ሰው የለም። ድሎቱም ምቾቱም ያለው እዛቸው አራት ኪሎ ቤተ መንግስት ውስጥ ብቻ ነው።

በኑሮ ውድነት የሚጠበሰው አንሶ ለተለያዩ ልማታዊ መዋጮዎች በየቀኑ ገንዘብ አምጣ እየተባለ ነው። መሬቱ እየተወሰደ፣ እምነቱ እየተሸረሸረ፣ ቤት አምልኮው እየፈረሰ ያለው ህዝብ የእርሶው ህዝብ ነው። እናም እንደ አስቴር ከንጉሱ ዘንድ የተጫነብን እንዲነሳልን ለምኑልን ብለን አብዝተን እንጮሀለን። አይዞት ሶስት ቀን ሶስት ሌት ፁሙ ማለት አይጠበቅብዎትም እኛ ቀድሞውንም እየፆምን ነውና ሃሳብ አይግባዎ…!

ባለፈውም ግዜም ያልኩዎት ይህንኑ ነው። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከህዝቡ ሰላማዊ ሰልፍ በላይ ከህዝቡ ኡኡታ በላይ የእርስዎን ምክር እና ልመና ተግባራዊ እንደሚያደርጉ አምናለሁ። እናም እባክዎ ለእርስዎ ጠቅላይ ባለቤት ለእኛ ጠቅላይ ሚኒስትር የሆኑት አቶ መለስ በህዝቡ ላይ የጫኑትን መከራ ያነሱ ዘንድ ይምከሩልን ይለምኑልን!

ከዚህ ሁሉ ጭቅጭቅ ብላችሁ ሁለታችሁም ዘወር ብትሉልንማ የመከራዎች ሁሉ መከራ ቀለለ ማለት ነበር።

ብቻ ቀዳማዊ እመቤት ይምከሩ እና እንደሚሆን ያድርጉ እባክዎን ጉዳዬን ችላ አይበሉብኝ። ኋላ ጥሩ ላይመጣ ይችላል።

አክባሪዎ…!
ወዳጄ እስቲ ቸር ያሰማን!
አማን ያሰንብተን!

---

## የጠቅላይ ሚኒስትሩ …

ከገፅ 12 የዞረ

የሚጠይቃቸው አይኖርም ብዬ እገምታለሁ። ያለን ዕድልም ሩቅ ሆኖ መመልከት ብቻ ነው።

ባለፈው የትግራይ ገበሬው የሆረዮ ላስቲክ ዋጋ ዕዳውን መክፈል አቅቶት ከሃገር የሸሸው አሁን ደግሞ መከረኛው የትግራይ ገበሬ የዉሃ ሞተር ዋጋ ያለበትን ዕዳ እንዴት አድርጎ ይከፍለዋል? ስለዚህ ስንት የትግራይ ገበሬ ነው ሃገር ለቆ የሚሸሸው? ወዴት እንደሚሸሽ አይታወቅም። የህወሓት መንግስት ግን በየ መገናኛ ብዙሃኑ ለህዝብ ቁጫያለሁ እያለ ፕሮፓጋንዳውን ሲነዛና ዲስኩር ሲያሰማ ውሎ ያድራል።

የጠቅላይ ሚኒስተር የልማት ሰራዊት ስሙን ቢለውጥ ይሻለዋል። የልማት ሰራዊት መባል ቀርቶ የጥፋት ሰራዊት ነው የሆነው። የሃገር ሃብት ያለ አግባብ ሲያባክን ሁልጊዜ ይታያልና። የህወሓት ካድሬዎች የሰው ምክር አይሰሙም እንጂ የሚመክራቸው አልጠፋም ነበር።

የሚገርመው ነገር በትግራይ ያሉ ጂኦሎጂስቶችና ሃይድሮ ጂኦሎጂስቶች ምን እያደረጉ ናቸው? በሙያቸው እንዳይሰሩ ተደርገዋል? የተማራችሁትን ሙያ ሌሎች ሰዎች እየተጫወቱበት እያያችሁ ዝም ትላላችሁ? ይህማ ነውር ነው። ምንስ ስትሆኑ ነው እንደዚህ የሆናችሁት? ለሙያችሁ ጠበቃ መሆን አቃታችሁ ማለት ነው ወይ?። ሳይንሳዊውን ሐቅ መካድ የለባችሁም። ምንም ሳይንስ የማያውቁ የህወሓት ካድሬዎች በድፍረት ያን ሁሉ ብልሹ ሥራ ያለ ሃፍረት እየሰሩ እናንተ ምንው ዝም አላችሁ?

እውነት ለመናገር በትግራይ ብዙ ባለሙያዎች ያቀፉ ድርጅቶች የጂኦሎጂና የዉሃ ሃብት ጥናትና ፍለጋ እንዳሉ የሚታወቀው ነው። ታድያ እነዚህ ድርጅቶች ምን እየሰሩ ናቸው ተብለው ቢጠየቁ ምን መልስ አላቸው? ምንስ ምክኒያት ሊያገኙ ይችላሉ። ትምህርትና ሙያ ሃገርና ህዝብን ካላገለገሉ ምን ፋይዳ አላቸው ሊባል ይችላል። ማንም ሰው ዕድል አግኝቶ ከተማረ ያን ትምህርት ደሞዝ ለማግኘት ብሎ ካሰበ ይህ ሰው ተምሯል ለማለት ያስቸግራል። ትምህርት ለደሞዝ ብቻ ነው ከተባለ ምን ዐይነት አስተሳሰብ ያለው ዜጋ እየተፈጠረ ነው? ከላይ እንዳየነው ምንም ሙያና የከርሰ ምድር የጥናት እውቀት የሌላቸው ያን ሁሉ ጥፋት እየሰሩ ባለሙያዎች ዝም ብለው ሲመለከቱ ማየት አስነዋሪ ነው። እነዚህ ሰዎች አድር ባዮች ናቸው ከማለት ሌላ ስም ሊሰጣቸው አይችልም፡ ፡ የፈለገውን ምክኒያት ቢደረድሩ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም።

ጉልጉል ራያ ብዙ የሀይድሮጂኦሎጂ ጥናት ተሰርተዋል። ብዙ የከርሰ ምድር ዉሃ እንዳለው በሳይንስ ተረጋግጧዋል። ለምን ያንን ቦታ አይቆፍሩምና ለመስኖ እርሻ አያውሉትም? ያልታወቁ ቦታዎች በዘፈቀደ ከመቆፈርና ገንዘብ ከመባከን የተሻለ አማራጭ ነበር። ይህ ሁሉ የሚያሳየው የክልሉ አስተዳዳሪዎች ባለሙያዎችን ለማማከር ስለማይፈልጉ ነው። እኛ እናውቃለን ባይ የህወሓት ካድሬዎች በትዕቢት የተወጠሩ መሆናቸው ከኛ በላይ ላሳር ባዮች መሆናቸውና የትግራይ ህዝብ ያውቃል። አብሮ መመካከርና አብሮ መስራት የማይፈልግ የትግራይ ሰው የለም በማለት በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል።

ለምን እነዛ ጉድጓዶች ሊደርቁ ቻሉ ለሚለው ጥያቄ የሚኖሮት ምላሾች የሚከተሉት ናቸው፦

1. ጉድጓዶቹ እርስ በራሳቸው የተቀራረቡ በመሆናቸው (interference between water-wells) ተፅዕኖ ይኖራቸዋል። በሌላ አባባል አንድ ጉድጓድ ለሌላው ጉድጓድ የሚኖረው ተፅዕኖ በሁለቱ ጉድጓዶች ያለው ርቀት የሃይድሮጂኦሎጂ ሳይንስ ስርዓት ከሚፈቅደው ዉጭ ሲሆን ነው። ምክነያቱም ከሁለት ኪሎሜትር ያነሰ መሆን የለበትም።

2. የዉሃ ሞተር የመምጠጥ አቅምና የከርሰ ምድር ዉሃ ወደ ጉድጓዱ የሚፈስበት መጠን ወሳኝ ሚና አላቸው። ምክነያቱም ወደ ጉድጓዱ የሚገባ የዉሃ መጠንና ከጉድጓዱ የሚመጠጥ የዉሃ መጠን እኩል ካልሆኑ የጉድጓዱ ዉሃ ቶሎ ያልቃልና ሞተሩ በዉሃ ፈንታ አየር መምጠጥ ይጀምራል። ስለዚህ ጉድጓዱ ይደርቃል ማለት ነው።

እነዚህ ሁለት ነገሮች ግምት ዉስጥ መግባት አለባቸው። ስለዚህ ጥንቃቄ የጎደለው አሰራር እዚህ ዉስጥ መግባት የለበትም። ማለትም እንደማናቸውም ሥራ በዘፈቀደ መሰራት የለበትም ለማለት ፈልጌ ነው። ስለዚህ ሥራው ዉጤታማ ሊሆን ከተፈለገ በአግባቡ መሰራት አለበት።

በወይን መፅሄት እንደአነበብኩት በብዙ ቦታዎች የስኳር አገዳ እርሻና የስኳር ፋብሪካዎች ለማቋቋም በሃገር ደረጃ እንደታቀደ ያመለክታል። በጣም ጥሩ ሃሳብ ነው። ነገር ግን እንደሚታወቀው የስኳር አገዳ ሰብል ብዙ ዉሃ የሚያስፈልገው የእርሻ ሰብል በመሆኑ የሚያስፈልገውን የዉሃ መጠን አስቀድሞ መታወቅ ይኖርበታል። ከዚያ በፊት የዉሃ አጠቃቀማችን ምንጩ ከየት እንደሆነ በቅድሚያ ተጠንቶ ነው ወይ? የሚል ጥያቄ መቅደም አለበት። በዚህ ጉዳይስ የባለሙያዎች አስተያየት ቅድሚያ መሰጠት የለበትም ወይ? የማንም እቅድ ወይም ሊሰራ የተፈለገ ነገር በቅድሚያ መጠናት አለበት ምክነያቱም ያለ ጥናት የሚደረግ ሥራ ዉጤት አልባ ነው የሚሆነው። ከዚህ በፊት ያየናቸው በዘፈቀደ የተሰሩ ስራዎች ዉጤታቸው ያማረ አልነበረም። በዚያ ምክኒያት የሃገራችን ሃብት በከንቱ ይባክናል።

ከስህተታችን መማር መቻል አለብን። የመመካከር ባህል ሊዳብር ይገባዋል። ሁሉ ነገር በፖለቲካ ዐይን መመዘኑ ይቅር። የአስተዳዳሪዎቻ አስተሳሰብ በፖለቲካ ብቻ የተገነባ ነው የሚመስለው። ሁሉ ነገር በፖለቲካ ዐይን መታየት አለበት ባዮች ናቸው ነገር የሚያበላሹት።

አንድ የዓለም ባንክ ሰራተኛ ወደ ነበርኩበት መስርያ ቤት በየጊዜው ሲመጣ እኔ ላስተናግደው እመደብ ነበር። ለልመና እንዲመች በጥሩ ሁኔታ እንዳስተናግደው እታዘዝ ነበር። በዚያን ጊዜ አሉ የተባሉ ሆቴሎች እጋብዘው ነበር። አንድ ቀን ምሳ ከበላን በኋላ ቡና እየጠጣን እያለን ኢትዮጵያን በመጥፎ ቃላቶች መስደብ ጀመረና በጣም ተሰማኝ። እንዳልሰድበው የልመናው ነገር ሊበላሽ ነው፤ ዝም እንዳልለው ደግሞ ሃገሬ እየተሰደበች አልቻልኩምና ቁጭቴን በውስጤ አምቄ እንዴት አድርገህ እንደ ኢትዮጵያ ያለችውን ድሃና ኋላ ቀር ሃገር ከሃገርህ አሜሪካ ጋር ታነፃፅራለህ አልኩት፤ ሰዉየው በጣም ተናደደና ኢትዮጵያ ድሃ አይደለችም፤ ኋላ ቀርም አይደለችም። እኛ እንኳ የ200 ዓመት ታሪክ ያለን ህዝብ ነን። ኢትዮጵያ ግን በሺ የሚቆጠር ዓመታት ታሪክ ያላት (Ethiopia is undermanaged country) ሀገር ናት ሲለኝ አፈርኩ። ምክነያቱም የሚናገረው እውነት ስለሆነ ነው። ይህን የሰዉዬው አባባል ምንጊዜም አልረሳዉም። እኔ ሶስት መንግስታት ያየሁ ሰው ነኝ። ሰዉዬው እንዳለው ምንጊዜም አስተዳደራችን ሲመዘን ባዶ ነው። የአስተዳደር ድሆች ነን። የጥሩ መንግስት ድህነት እንጂ ሌላ ችግር የለብንም። እንዴት ሃገራችንን እናስተዳድር ብለን በጥሞና ማየት አለብን ብዬ ለብዙ ጊዜ አሰብኩ። እንቅልፍን እስከማጣ ድረስ አሳሰበኝ። ምን ያልታደልን ህዝብ ነን?

አሁን በኋላ ወደ ኋላ ዘወር ብለን ማየት ያስፈልገናል። ያደረግነው ሁሉ ትክክል ነበር ወይ? ስህተት አለው ብለን ራሳችን መጠየቅና ረጋ ብለን ማየት አለብን። ስህተት ካለ ከስህተታችን ምን ተማርን ብለን ራሳችንን መጠየቅ አለብን፤ ወደ ሌላ እርምጃ ከመሄዳችን በፊት። ይህ ሊሆን የሚችለው አስተሳሰባችን ካስተካከልንና የሰዎችን ሃሳብ ከተቀበልን ብቻ ነው። በስሜት ሳይሆን ረጋ ብለን በማሰብ ወሳኝ የሆነ እርማት ማካሄድ ያስፈልጋል። ለወደፊት ያቀድነው ሥራ ካለ ጥንቃቄ በማድረግ የሃሳቡን ዙርያ ማየትና ማስተዋል ይኖርብናል። ሃሳቡንም በትክክለኛ ጥናት የተመሰረተ መሆን አለበት ብለን ማመን አለብን።

# ከእንግዲህ መቃብር በርትተህ ተማር፤ ጸመ ድጓ ይዞ መጣልህ መምህር፡፡



ከታዴዎስ ታንቱ

በጥይት ይደበደባሉ፡፡ ዛሬ ይፈፀማል፡፡ የፋሽስት ኢጣሊያ ወረራ ኃይል ሹማምንት ወስነዋል፡፡ ሐዋርያው የሐይማኖት አባት አልተነገራቸውም፡፡ ከፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ጭካኔ በመነሳት ሊሆን የሚችለውን ለመገመት ግን በአስተውሎት እጥረት አይታሙም፡፡ ሞት ደግሞ አይፈሩም፡፡ የአቤልን ፅዋ በልበ ሙሉነት ይጨልጣሉ፡፡ በሐዋርያዊ ተልዕኮአቸው ለምዕመናን የረጅም ዓመታት አገልግሎት ተስፋ ሰንቀዋል፡፡ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ክርስትና አስተምህሮ ተቀብተዋል፡፡ በአርበኝነት አቋማቸው ሣቢያ ግን በፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ትዕዛዝ አሁኑኑ የሞት ቅጣት ይፈፀምባቸዋል፡፡ ያለፍርድ በውሳኔ ያልቃል፡፡

ዛሬ ስምንት ቀናቸው ነው፡፡ ለብቻቸው ታሥረዋል፡፡ ሰሌን አንጥፈው ድንጋይ ይንተራሳሉ፡፡ በቀን አንድ እንጀራና ውኃ በቅል አልተነፈጉም፡፡ ከትናንት ወዲያ ማታ አንስቶ ግን እንጀራም ሆነ ውኃ አልገባላቸውም፡፡ ጾማቸውን ውለው አድረዋል፡፡ ከፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ሹማምንት በወረደ ትእዛዝ ምንም ነገር እንዳይገባላቸው ተወስኗል፡፡ የግድያ ቅድመ ግድያ ትእዛዝ ፀንቷል፡፡

ጧት ተነሥተው ሦስት ጊዜ አማተቡ፡፡ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን! ከውዳሴ ማርያም የዕለቱን ፀሎት አደረሱ፡፡ ብዙም አልቆዩም፡፡ በመጽሐፍ ቅዱሳቸው ላይ ውዳሴ ማርያምና መስቀላቸውን አስቀመጡ፡፡ የነተበች ጋቢያቸውን ተከናነቡና ሰሌናቸው ላይ ድንጋዩን ተንተርሰው ኩርምት ብለው ተኙ፡፡ አንድ ሰዓት ያህል ዕንቅልፍ እምቢ ብሏቸው በሐሳብ ቆዩ! ያስባሉ! ያስባሉ! ያስባሉ! በድንገት ግን ዕንቅልፍ ወሰዳቸው፡፡ ማንም ምንም አልቀሰቀሳቸውም፡፡ ግን ነቁ፡፡ በሐሳብ ባሕር ሰመጡ፡፡ በዚህ መካከል ሁለት ጣሊያኖች መጥተው የታሰሩበትን ክፍል ሳንቃ ብርግድ አደረጉ፡፡ አንዱ መኮንን ሲሆን ሁለተኛው የበታች ሹም ነበር፡፡ ሐዋርያው ጋቢያቸውን ከግንባራቸው ገለጥ አድርገው ወደ በር ተመለከቱ፡፡ ጣሊያኖችም ተመለከቷቸው፡፡ ጀግናው ሐዋርያ አንዲት ኢጣልያንኛ ቃል እንኳን አያውቁም፡፡ ኢጣሊያኖቹ ደግሞ አማርኛ ፈፅሞ አይናገሩም፡፡ ምን ማድረግ ይችላሉ? ቱርጁማኑ ሹምባሽ ገብረ ወልድ ሩፌ ዘግይቷል፡፡ መኮንኑ ተቁነጠነጠ፡፡ ትዕግሥት አጣ፡፡ ሹምባሽ ገብረወልድ ግን ብዙ አልቆየም፡፡ እየሮጠ ደረሰ፡፡ መኮንኑ ተናድዶ ነበር፡፡ አሁን ግን ቀዝቀዝ አለ፡፡ ሐዋርያው ለገናናው የኢጣሊያ መንግስት ለመገዛት ከፈቃደኝነት አቋም ደርሰው ይሆን? ሹምባሽ ገብረወልድ ሩፌ የመኮንኑን ጥያቄ ከኢጣሊያንኛ ወደ አማርኛ መነዘረላቸው፡፡ ‹‹እኔ ከሐይማኖቴና ከሰንደቅ ዓላማዬ ሌላ ማንንም አልቀበልም›› ፍርጥም ያለ መልስ ሆነ፡፡ ሹምባሽ ገብረወልድ የሐዋርያውን ፅኑ አቋም ለጌቶቹ ደግሞ ወደ ኢጣሊያንኛ መነዘረው፡፡ ጣሊያኖቹ ተናደዱና በሩን እላያቸው ላይ ዘግተው ተመልሰው ሄዱ፡፡ ጀግናው ሐዋርያም ኩርምት ብለው ተኙ፡፡ ቀጥሎ ምን ሊሆን ይችላል? ሐዋርያው በሐሳብ ሰምጠዋል፡፡ የአርበኞችን ድል ለማየት ቋምጠዋል፡፡

ከግማሽ ሰዓት በኋላ ጣሊያኖቹ ተመልሰው መጡ፡፡ ሹምባሽ ገብረወልድ በሩን ከፈተው፡፡ ሐዋርያው እንዲወጡ ተነገራቸው፡፡ መፅሐፍ ቅዱሳቸውን፤ መስቀላቸውንና ውዳሴ ማርያምን ይዘው ሊወጡ ሲሉ እንዲያስቀምጡ በሹምባሽ ገብረወልድ አስተርጓሚነት ተነገራቸው፡፡ ጀግናው ሐዋርያ ግን የጣሊያኖቹን ትዕዛዝ ለመቀበል ፈቃደኛ አልነበሩም፡፡ ‹‹እኔ የእግዚአብሔር ትእዛዝ ካልሆነ በስተቀር የሰውን አልቀበልም!›› ፅኑ አቋም አንፀባረቁ፡፡ ሹምባሽ ገብረ ወልድ ለጣሊያኖች ይህንኑ ነገራቸው፡፡ ጀግናው ሐዋርያ ቅዱስ ንብረታቸውን ይዘው ወጡ፡፡ አቅም አንሷቸው ሲንገዳገዱ ይስተዋላል፡፡ ኢጣሊያኖቹና ሹምባሽ ገብረወልድ ከኋላቸው እሳቸው ደግሞ ከፊት ነበሩ፡፡ አቅመ ቢሱ ግን ልበ ሙሉ ሐዋርያ ከተጠበቀው ፍጥነት በወረደ እርምጃ ተወስነዋል፡፡ ኢጣሊያኑ መኮንን ተናድዶ በጆርባቸው ላይ ባለ በሌለ ኃይሉ ረገጣቸው፡፡ ከመቅፅበት ወደቁ፡፡ መነሳት ተስኗቸዋል፡፡ ቀስ ብለው በሁለት እጃቸው መሬቱን ተመርኩዘው ተነሱ፡፡ ወዲያው መፅሐፍ ቅዱሳቸውን፤ መስቀላቸውንና ውዳሴ ማርያምን ሰብስበው ጉዟቸውን ቀጠሉ፡፡ ሐዋርያው የኢትዮጵያ ጀግና ሊገደሉ እንደሚወሰዱ ግን እስካሁንም አልተነገራቸውም፡፡ ብዙ ቤቶችን አልፈው አሁን ወደ አደባባይ ወጥተዋል፡፡ በጎሬ ከተማ ውስጥ ትልቁና ዋናው ሜዳ ይህ መሆኑ ይመዝገብልን፡፡ ሐዋርያው ከግድያ ስፍራ ደርሰዋል፡፡

የፋሽስት ኢጣሊያ ሹማምንት ቆመዋል፡፡ ምድረ ባንዳ ወዲያ ወዲህ ይላል፡፡ ሕዝቡ ከገጠር ጭምር በትእዛዝ ተሰብስቧል፡፡ ሕዳር 24 ቀን 1929 ዓ.ም. እንደ ነበር ይዘናል፡፡ ፈርቶ የተሰበሰበ ሕዝብ በሐዘን ተውጧል፡፡ በሐዘን የተዋጠ ሕዝብ ፈርቶ ተሰብስቧል፡፡ ከቆሙት የኢጣሊያ ሹማምንት አንዱ በስልጣን ይበልጣል፡፡ ጀግናው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሐይማኖት ሐዋርያ ቆመዋል፡፡ ሕዝቡ ከተወሰነው ርቀት በመቀነስ ወደ ፊት ከተጠጋ ይገደላል፡፡ ነፍሰ ገዳይ ቡድን በተጠንቀቅ ይስተዋላል፡፡ ሁለት አርበኞች ግን ገና አልመጡም፡፡ አንደኛው ቀኛዝማች ይነሱ ይባላሉ፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ግራዝማች ተክለ ሐይማኖት እንደ ነበሩ ታውቋል፡፡ ጀግኖቹ ከጀግናው ሐዋርያ ጋር አንድ ላይ ይገደላሉ፡፡ ሃያ ሜትር ጉድጓድ ተምሷል፡፡ አፏን ከፍቶ ይጠባበቃል፡፡ ጀግኖቹ አርበኞች አሁን ደረሱ፡፡ ሁለቱም እጆቻቸው በሰንሰለት ታስረዋል፡፡ በርካታ ባንዳዎች አጅበዋቸዋል፡፡ አርበኞቹ ከፊታቸው ፍርሃት አይነበብባቸውም፡፡ ከጀግናው ሐዋርያ አጠገብ እንዲቆሙ ተደረገ፡፡

የሚቀጥለው ሥነ ሥርዓት አሁን ቀጥሏል፡፡ ሹምባሽ ገብረ ወልድ ሩፌ ወደ አማርኛ ይመነዝረዋል፡፡ በጎሬ ትልቁ የፋሽስት ኢጣሊያ ሹም ንግግር ይሰማል፡፡ የሐዋርያውን ወንጀል በቅድሚያ ዘረዘረ፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የሁለቱን አርበኞች ጥፋት አመለከተ፡፡ የፋሽስት ኢጣሊያ ሹም ንግግር አበቃ፡፡ የግድያ ሥነ ሥርዓት አሁን ይከናወናል፡፡ ሁለት ባንዳዎች ጀግናውን ሐዋርያ በግራና በቀኝ ይዘው ከጉድጓዱ አፍ ላይ አስቀመጧቸው፡፡ ጀግናው ሐዋርያ በመስቀላቸው ሦስቴ አማተቡ፡፡ የመሸበር ሁኔታ አይታይባቸውም፡፡ ለእናት ሀገራችን ክብር ሞትን በፀጋ ለማስተናገድ ቆርጠዋል፡፡ ማን ይፈራል ሞት ማን ይፈራል? ለእናት ሀገር ሲባል! በመቀጠል ደግሞ ባንዳዎቹ ሁለቱን አርበኞች ከጉድጓድ አጠገብ አመጧቸው፡፡ ቀኛዝማች ይነሱ ከሐዋርያው በግራ በኩል እንዲቀመጥ ተደረገ፡፡ ግራዝማች ተክለ ሐይማኖት ደግሞ በቀኝ በኩል ሆነ፡፡

ስምንት አባላትን ያካተተ አንድ ነፍሰ ገዳይ ቡድን ቆሞ ትእዛዝ ይጠባበቃል፡፡ አሁን ትእዛዝ ሊሰጥ ነው! አስተኳሹ ተዘጋጅቷል፡፡ ሁሉም ሰው ትርዒቱ የሚያስከትለውን ትርዒት በሐዘን ይመለከታል፡፡ ‹‹ተኩስ!›› ወታደራዊ ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡ ድምምምምምም! ገቢራዊ ሆኗል፡፡ ሦስቱም የኢትዮጵያ ጀግኖች ከፊት ለፊታቸው በነበረው ጉድጓድ ውስጥ ወደቁ፡፡ አፈር ለመመለስ ከባንዳ ያነሰ ማን ይታዘዛል? ወዲያው ትእዛዝ ተሰጠ፡፡ በአካፋና በእጅ አፈሩ ተመለሰ፡፡ የብፁዕ ቅዱስ አቡነ ሚካኤል የግፍ አገዳደል በጎሬ፡፡

ብፁዕ አቡነ ሚካኤል በጎንደር ክፍል ሀገር በደብረ ታቦር አውራጃ በአፈረዋናት ወረዳ ውስጥ በ1874 ዓ.ም. ተወለዱ፡፡ ወላጆቻቸው በግብርና ሥራ ይተዳደሩ እንደነበር በሕይወት ታሪካቸው ላይ ተመልክቷል፡፡ ብፁዕ አቡነ ሚካኤል ዕድሜአቸው ለትምህርት ሲደርስ በግንድ አጠመም ሚካኤል የቤተ ክህነት ትምህርት ዕውቀት ገብይተዋል፡፡ እድሜአቸው ከፍ ሲል ወደ ገላውዴዎስ ደብር ተልከው ፅዋትወ ዜማ በሚገባ አጥንተዋል፡፡ በዚሁ ብቻ ተወስነው አልተቀመጡም፡፡ ከፍተኛ የትምህርት ፍቅር ስለነበራቸው ወደ ማህደረ ማርያም አመሩ፡፡ እዚያ ደግሞ በከፍተኛ ደረጃ ፀዋትወ ዜማ ትምህርት ተከታትለው አጠናቀቁ፡፡ ተገቢውን እውቀት ቀስመዋል፡፡ በደረጃው ደረጃው የፈቀደውን በሚገባ አሟልተዋል፡፡

የትምህርት ጥማታቸው ግን አልበረደም፡፡ የዕውቀት ጉጉታቸው ገደብ አጥቷል፡፡ አሁን ወደ ጎንደር ተመለሱ፡፡ መጽሐፍተ ብሉያትንና ሐዲሳትን ትርጓሜ በሚገባ ተማሩ፡፡ አወቁ፡፡ በዚህም ብቻ አላበቁም፡፡ ወደ ወሎ አመሩ፡፡ ቦረና ሜዳ ከአካለ ወልድ ጉባዔ ላይ ተገኝተው ትርጓሜ መጻሕፍትን አጠናቅቀው በመምህርነት ተመረቁ፡፡ የቅኔ ብቃታቸውም የሚደነቅ እንደነበር ታውቋል፡፡ በትምህርታቸው ሒደት በደብረ ሊባኖስ ትንሽ ቆይታ አድርገዋል፡፡ በመቀጠልም አዲስ አበባ መጥተው አሥራ አራቱን የቅዳሴ ትርጓሜ ተምረው ወጥተዋል፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ መመኪያ የሆኑት ሐዋርያው አቡነ ሚካኤል በ1923 ዓ.ም. በአድባራቱና በገዳማቱ በኃላፊነት ቦታ ተመድበው ተግባራቸውን በብቃት ተወጥተዋል፡፡

ጀግናው ሐዋርያ አቡነ ሚካኤል በ1923 ዓ.ም. አበው የጵጵስና ማዕረግ ሊቀበሉ ወደ ግብፅ በሔዱ ጊዜ እሳቸው አንዱ እንደነበሩ ታውቋል፡፡ ከማዕረገ ጵጵስናው በኋላ ተመድበው ወደ ጎሬ ሔዱ፡፡ ጎሬ ሳሉ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል እየገፋ መምጣቱን ሰሙ፡፡ ጊዜ አላባከኑም፡፡ ሕዝቡን እየሰበሰቡ ስለሀገር ፍቅር ያስተምሩ ገቡ፡፡ ሕዝቡ ለነፃነቱና ለሐይማኖቱ መሥዋዕት መሆን እንዳለበት ማስረዳት በተከታታይ ቅስቀሳ አደረጉ፡፡ የተቻላቸውን ሁሉ ፈፀሙ፡፡ ምዕመናንን በፀረ-ፋሽስት አቋም አነፁ፡፡

ለነፃነታችንና ለአንድነታችን እጅግ ቀናዒ የሆኑት ሐዋርያው አቡነ ሚካኤል በ1928 ዓ.ም. ግፈኛው የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል በመጣ ጊዜ በፅኑ-አቋም ከአርበኞች ጋር ተሰለፉ፡፡ አላወላወሉም፡፡ አርበኞች በርትተው እንዲዋጉ ቀሰቀሱ፡፡ አሁንም ሕዝቡ አንድነቱን አጠንክሮ በፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ላይ እንዲነሳ አሳሰቡ፡፡ ሳይታክቱ ሰሩ፡፡ በቁርጠኝነትና በዓላማ ፅናት ቆሙ፡፡ እንቅስቃሴአቸው የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይልን ማሳሰቡ አልቀረም፡፡ ወራሪው ኃይል ምን ማድረግ ይችላል? አሰበ! አሰበ! አሰበ! ለጊዜው ግን አዲስ የስልት ሐሳብ አልመጣለትም፡፡ አቡነ ሚካኤል ደግሞ ቅስቀሳቸውን ከማፋፋም አልተቆጠቡም፡፡ ያለ ነፃነት ሐይማኖት አይታሰብም፡፡ ውሎአቸው በሙሉ ከአርበኞች ጋር ሆነ፡፡ በእርግጥ ጠብመንጃ አልተኰሱም፡፡ ቦምብ አልወረወሩም፡፡ ሽጉጥ አልመዘዙም፡፡ በአቋም ግን ሁሉንም አድርገዋል፡፡ በሐሳብ ፈፅመዋል፡፡ ምን ቀራቸው?

## ከሥነ ቃል የተወሰደ

አይበገሬው አቡነ ሚካኤል ፈፅሞ የማይመለሱ ሆኑ፡፡ በሀገር ጉዳይ ለማንም እጅ አይሰጡም፡፡ ማን ማንን ይገዛል? የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ተጨነቀ፡፡ ግትሩን ጳጳስ ለማለዘብ አዲስ አበባ ውስጥ ከባንዳ ጳጳሳትና ካህናት ጋር ስብሰባ ተቀመጠ፡፡ በመጨረሻ ለአቡነ ሚካኤል ሽማግሌ ተላከ፡፡ ምዕመናኑን ለገናናው የኢጣሊያ መንግስት ተገዢነት ካስተባበሩ በሰማይ የሚጠብቋትን ገነት በምድር እንደሚያገኟት ተነገራቸው፡፡ ይህ የባንዳ ካህናት ድምፅ ነው! አቡነ ሚካኤል ግን ውድቅ አድርገዋል፡፡ እሳቸው ይኮነኑ ኢትዮጵያ ግን ነፃ ትውጣ! ይህ የአቡነ ሚካኤል ድምፅ ነው! ምድራዊ ገነትን መቼ ቋመጡ? ነፃነታቸውና ሐይማታቸው ስለተነካ አራስ ነብር ሆኑ፡፡ በዚህ ላይ የኢዮብን ትዕግስት አይቀበሉም፡፡ የዳዊትን ጀግንነት ታጥቀዋል፡፡ ለሀገራቸው ይሰዋሉ፡፡ ለሐይማኖታቸው ይሰየፋሉ፡፡ ትዕግሥታቸው አልቋል፡፡ አማላጅ ካህናትን በቁጣ ሸኟቸው፡፡ ዳግመኛ እንዳይመጡባቸው አስጠነቀቋቸው፡፡

ጀግናው አርበኛና ሐዋርያ አቡነ ሚካኤል ከጥቁር አንበሣ አርበኞች ጋር የጠበቀ ግንኙነት ፈጠሩ፡፡ ለአርበኞች የማበረታቻ መልእክት በየጊዜው ይልኩ ገቡ፡፡ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ሕዝቡን እንዲያስተባብሩለት በግምባር ጠርቶም አነጋግሯቸዋል፡፡ እሳቸው ግን ‹‹ለእናንተ የተገባ ርጉም ይሁን!›› በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡

ቆራጡ ብፁዕ አቡነ ሚካኤል ባሁኑ ሰዓት ሱጴ በተባለ ቦታ ከአርበኞች ጋር ይገኛሉ፡፡ ጦርነቱ ተፋፍሟል፡፡ ብዙ አርበኞች ተሰውተዋል፡፡ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪዎችም በብዛት ተገድለዋል፡፡ የደም ጎርፍ ይስተዋላል፡፡ አቡነ ሚካኤል ከጦርነቱ ወረዳ ገለል እንዲሉ ተነግሯቸዋል፡፡ እሳቸው ግን ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተዋል፡፡ በሞታቸው ቆርጠዋል፡፡ አርበኞችን እግር በእግር እየተከታተሉ ሲያበረታቱ ይስተዋላል፡፡ ጦርነቱ ቀጥሏል፡፡ ሱጴ የደም መሬት ሆናለች፡፡ ድም! ድም! ቡም! ድም! ድም! ቡም! ቡም! ሬሣ ተከምሯል፡፡ አቡነ ሚካኤል የተሰዉ አርበኞችን መሣሪያ ወራሪው ኃይል እንዳይማርክ በሚደረገው ተግባራዊ እንቅስቃሴ መሪ ተዋናይ ሆነዋል፡፡ ዝናር ያልታጠቁ አርበኛ ወጥቷቸዋል፡፡ ጦርነቱ እንደ ቀጠለ ነው! ድም! ድም! ድም! ድም! ቡም! ቡም! ቡም! ቡም! ድም! ድም! አሁን ለወራሪው ኃይል ተጨማሪ ተዋጊና የጦር መሳሪያ መጥቶለታል፡፡ ለአርበኞች ግን ማንም የደረሰላቸው አልነበረም፡፡ የሰው ኃይላቸው መንምኗል፡፡ ጥይትም አልቆባቸዋል፡፡ ግፈኛው ወራሪ የበላይነትን ይዟል፡፡ አርበኞች ተከብበዋል፡፡ ምን ለማድረግ ይቻላል? ጥይት አልቆባቸው በእልህ እየተናጡ ቆመዋል፡፡ ሁለት ናቸው፡፡ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል የአርበኞችን እጅ በሰንሰለት አሥሯል፡፡ አንድ ቡልቅባሽ ሽጉጥ ይዟል፡፡ ወደ አቡነ ሚካኤል ተጠግቷል! ከፊቱ ቁጣ ይነበባል፡፡ ምን ሊያደርጋቸው ይሆን? ሽጉጡን በግምባራቸው ላይ ደገነ፡፡ አቡነ ሚካኤል ምንም የፍርሃት ስሜት አላሳዩም፡፡ መለሰው፡፡ እንደገናም ደገነባቸው፡፡ ሞትን ንቀዋል፡፡ ዘና ብለው ቆመዋል፡፡ በካሚዮን ወደ ጎሬ ተጫኑ ሰማዕትነትን በፀጋ ተቀበሉ፡፡ አንድ! አንድ! አንድ! ለጀግናው ሐዋርያ ለአቡነ ሚካኤል አንድ ቋሚ መታሰቢያ ሐውልት በጎሬ ከተማ ለምን አልታነፀላቸውም? አሁንም ይቻላል! ኢትዮጵያዊነት ያሸንፋል!

ከእንግዲህ መቃብር በርትተህ ተማር፤
ጸመ ድጓ ይዞ መጣልህ መምህር፡፡

## የዳግማዊ ቴዎድሮስን ...

ከገፅ 3 የዞረ

ኩታቸውን ከትከሻቸው ገፍፈው የማልበስ፣ ተበድሮ የመመፅወት፣ ‹‹የእንግዶችን እግር ማጠብ ይገባናል›› እስከማለት የመጐናበስ ሥነ-ምግባራዊ ልቀት የአፄ ቴዎድሮስ ታሪክ ግርማ ነው፡፡ አይንህን ‹‹ለብርሃን›› ከፍተህ እንድትጓዝ ይሄን ያህል የታሪክ ሽኝት ከተደረገልህ በቂ ነውና ወደ አፄ ቴዎድሮስ የቴክኖሎጂ ስልጣኔ አባትነት እንሸጋገር፡፡

በፕሮፌሰር ዶናልድ ክራሚ ግምገማ እንጀምር

‹‹ማብራራቱና መተንተኑ ቢጐድለውም የዘመናዊ ስልጣኔ ሀሳብ የገባው የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ንጉሥ ነበር›› ይላል፡፡

ባህሩ ዘውዴ ይሄንን የአፄ ቴዎድሮስን የዘመናዊ ሥልጣኔ ቀደምትነት ተቀብለው ለውጥ ለማድረግ ልዩ ትኩረት የሰጡት ካስተዳደር ይልቅ በወታደራዊ መስክ ነው ይላሉ፡፡ ወታደራዊ ኃይልና የፖለቲካ ስልጣን ምንጊዜም ተወራራሽ እንደሆኑ የጠቆሙት ባህሩ ‹‹አገር አሰለጥናለሁ ያለ መሪ ሁሉ መጀመሪያ የሚያተኩረው በጦር ሰራዊቱ እንደሆነ ተደጋግሞ የታየ ነገር ነው፡፡ ...ቴዎድሮስ ሥልጣኑን ለማዳበር ሠራዊቱን በሦስት አቅጣጫዎች ማሻሻል አለብኝ ብሎ ተነሣ፡፡ በአደረጃጀት፣ በሥነ-ሥርዓትና በጦር መሳሪያ፡፡፡›› (የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1847-1983 ገፅ 33)

አፄ ቴዎድሮስ በወታደራዊ መስክ ሾልከው አገር ለማዘመን ያስችላል ያሉዋቸውን የአደረጃጀት፣ የሥነ-ሥርዓትና የትጥቅ ግቦች ወደተግባር ለውጠው ውጤት ማየት ጀምረው እንደነበር በብዙ የታሪክ ምሁራን ተመስክሯል፡፡ ሰራዊቱን ለማደራጀት የተበታተነውን የግብር አሰባሰብ ወደ አንድ ለማምጣት የወሰዱት እርምጃ የመጀመሪያ ሙከራቸው ነበር፡፡ በዚህ ሙከራ ወታደሩን ከተሰሪነት (በየባላገሩ ቤት እየገባ ከመቀለብ) እንዲወጣና በደምወዝ እነዲተዳደር አድርገው ነበር፡፡ በወር እስከ ሺ ብር የሚከፈላቸው ወታደራዊ መሪዎች ያሉበት ዘመናዊ ሠራዊት ለማቋቋምም ችለው ነበር፡፡ ይሄ ዘመናዊ ጦር ተጠሪነታቸው ለመሳፍንቱ የነበሩትን የተለያዩና የተበታተኑ ጦሮች በማሰባሰብ አንድ አገር አቀፍ ብሔራዊ ጦር ለመጀመሪያ ጊዜ ለማቋቋም የተቻለበት ነበር፡፡ ወታደራዊ አደረጃጀቱ የሰራዊቱን የተዋረድ ሹመት ተግባር ላይ ያዋለ እንደነበር ይነገራል፡፡ ባህሩ ዘውዴ አስር ዓለቃ፣ ሃምሣ አለቃ እና ሺ አለቃ... የሚል ወታደራዊ ማዕረግና አደረጃጀት የተጀመረው በአፄ ቴዎድሮስ እንደነበር ምስክርነታቸውን ይሰጣሉ፡፡

አፄ ቴዎድሮስ ከወታደራዊ ሥርዓት ባለፈ ሰራዊቱን ዘመናዊ ጦር መሳሪያ የማስታጠቅ ህልማቸውን ለመተግበር የተነሱት በግዢ ሳይሆን በአገር ውስጥ ምርት እንዲሆን መፈለጋቸው ታላቁ የስልጣኔ አርአያ ያደርጋቸዋል፡፡ አፄው ከሴባስቶፖል መድፍ አስቀድሞ ሌላ መድፍ የመስራት ገድልም ፈፅመዋል፡፡ ከደባርቂት ውጊያ ማግስት የግብፆችን መድፍ በመመልከት ግንድ አስፈልፍለው ባሩድ በመቅበር ከሩቅ የሚፈነዳ መድፍ ለመስራት ሞክረው ነበር፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የተለያዩ ብረቶችን በመቆራረጥና ከባሩድ ጋር በመደባለቅ የጠመንጃ አረር ይመረት ነበር፡፡ በዚህ አረር የማምረት ተግባር ላይ አፄ ቴዎድሮስ ቀጥተኛ በወዛደርነት ተሳታፊ ነበሩ፡፡

‹‹መጋቢት 6 ቀን 1858 ዓ.ም. ቴዎሮስ ለራሳም በፃፉት ደብዳቤ ‹‹...ቱርኮች አገሬን ይዘውብኝ ባላጋራ ሁነውኛልና መርከብ የለኝ በባህር አልችላቸው›› ብለው ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት የእንግሊዝ እስረኞችና ሚሲዮናውያኖቹ መርከብ እንዲሰሩላቸው ትእዛዝ ሰጡ›› ይሄን የሚለው ጳውሎስ ኞኞ ነው፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ በሞተር የሚንቀሳቀስ ጀልባ የተሰራው በዚሁ ዓመት በሚያዝያ ወር ነበር፡፡ ራሳም ስለመርከቦቹ ስራ ሲገልፅ፡-

‹‹...በስራው ቴዎድሮስም ተካፋይ ነበሩ፡፡ 60 ጫማ ርዝማኔ 20 ጫማ ስፋት ያላቸው ሁለት ጀልባዎች ተሰሩ፡፡ እነዚህ ሁለት ጀልባዎች እያንዳንዳቸው አንድ መቶ ሰዎች ሲጫኑባቸው ጀልባዋ ወደ ባህሩ ውስጥ ያዘቀጠችው አራት ኢንች ያህል ብቻ ነበር፡፡ ሚሲዮናውያኖቹና ሕዝቡ ተሰብስቦ በአድናቆት ጀልባዎቹን ሲመለከት ቴዎድሮስ ደግሞ በጣም ደስ ብሏቸው ነበር፡፡››

አፄ ቴዎድሮስ ፍፁም ደስታ የሚሰማቸው ያሰቡት ቴክኖሎጂያዊ ተግባር ተፈፅሞ ሲመለከቱ ብቻ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ለሚሰሩ እጆች ያላቸው አክብሮትና ፍቅር የንጉነታቸውን ደረጃ የሚያስት ስሜት ቅልቅል ነበር፡፡ ዎልድሜየር እንደፃፈው አዳዲስ ሥራዎች ተሰርተው በሚያዩበት ጊዜም ‹‹የሚያላዝኑ እጆች አሁን እነኚህንም አፈር ይበላቸው ይሆናል›› እያሉ ያደንቃሉ፡፡ አንድ ጊዜ እንዲያውም የዎልድሜየርን እጅ አገላብጠው ስምዋል፡፡

እኒህ ናቸው አፄ ቴዎድሮስ፣ እኛ የሚገቡንና የምናውቃቸው፡፡ በዕውቀቱ ‹‹ንፁሃንና ጨዋዎችን›› ለሚያጠቃው የፍርድ መሰናከያ ጉድባ እራሱን ያጋለጠው እነዚህን በመሳቱና ችላ በማለቱ ነው፡፡ በዕውቀቱ ባለፈው ሳምንት ፅሁፍ ከአንዲት አሰቃቂ ትረካው በኋላ እንዲህ በማለት ጥያቄ ጣል አድርጐ ነበር፡፡ ‹‹ዓለማየሁ ይህንን ከህዝቡና ከአካባቢው ጋር እንዴት እንደሚያገናዝበው ለማየት ጓጉቻለሁ፡፡፡››

የበዕውቀቱ ችግርም ይሄው ነው፡፡ ቁንፅል እውንታዎችን ይዞ ከህዝብና ከአካባቢ ጋር ማገናዘብ፡፡ አገር አቀፍ እንድምታውን ለመመልከት የሚችልበትን ‹‹ከፍታ›› አይመርጥም፡፡ ለምሳሌ አፄ ቴዎድሮስ መቅደላ ላይ በመጨረሻዋ የሽንፈት ሰዓት ላይ ሆነው ከአሽከሮቻቸው አንድ አማራጭ ቀረበላቸው፡፡ አማራጩን ያቀረቡት ራስ እንግዳ ነበሩ፡፡ ‹‹ለምን ያዝናሉ፣ እነዚህ ነጮች (እስረኞቹን) መልሰን እናምጣና ገድለናቸው እንሸሽ ወይም ተዋግተን እንሙት›› አሉ፡፡ አፄ ቴዎድሮስ ተስፋ በመቁረጣቸው ብቻ ይሄንን አጥፍቶ የመጥፋት አማራጭ አልተቀበሉትም፡፡ አፄው ለአላማ እንጂ ለበቀል አይገድሉም፡፡ በቁጣ ራስ እንግዳን እያዩ እንዲህ አሉ፡፡

‹‹አንተ አህያ ባለፈው ሁለት ቀን ውስጥ የፈጀሁት ሰው አይበቃምን? እነዚህን ነጮች እንድገድልና አበሻን በደም እንዳጥባት ነውን የምትፈልገው?››

በዕውቀቱ ያገነናቸውን የጭካኔ ተግባራት ከዚች የመጨረሻ የአፄው ውሳኔ ጋር ነው የማገናዝባቸው፡፡ አፄ ቴዎድሮስ አገር ለመግራት አላማቸው ብዙ የጭካኔ ዘለበቶችን በተገሪዎች ላይ አሳርፈዋል፡፡ ተራ ነፍሰ ገዳይና ደም የጠማቸው ግን አልነበሩምና አላማቸው ከጨነገፈ በኋላ የበቀል ሞትን በጠላቶቻቸው ላይ አልጠሩም፡፡ ወደ እራሳቸው አነጣጠሩ እንጂ፡፡ ይሄ ታላቅነት አይመስልህም፣ በዕውቀቱ?

# የእስክንድር ነጋን ሽልማት ባለቤቱ ሠርካለም ፋሲል በኒውዮርክ ተገኝታ ተቀበለች

የኢንተርናሽናል ፔን አሜሪካ ሽልማት የ2012 አሸናፊ የሆነውን የጋዜጠኛ እስክንድር ነጋን ሽልማት ባለቤቱ ሰርካለም ፋሲል በኒውዮርክ ተገኝታ ተቀበለች።

ከፔን አሜሪካ የፕሬስ ነፃነት ሽልማትን (Press freedom award) የተቀዳጀው ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ በኢትዮጵያ ጠንካራ ሰብዓዊ መብት አቀንቃኝ የነበረ ሲሆን ሽልማቱ ለባለፈው ስራው እውቅና ለመስጠትና መንግስት ጋዜጠኞች ላይ ማሳደዱን እንዲያቆም ጫና ለመፍጠር አቅም ያለው መሆኑን ኒውዮርክ ታይምስ ዘግቧል።

ከምርጫ 97 በኋላ በተነሳው ውዝግብ ከእስክንድር ጋር የታሰረችው ባለቤቱ ጋዜጠኛ ሠርካለም ፋሲል ማክሰኞ ምሽት በባለቤቷ ቦታ ሆና ሽልማቱን የተቀበለች ሲሆን ረቡዕ ዕለት ባደረገችው ቃለ-ምልልስ ላይ ‹‹የምንፈልገውን ሀገር ለመፍጠር መስዋዕት የሚሆን ሰው መኖር አለበት›› ስትል ተናግራለች።

ሽልማቱንም ስትቀበል ‹‹እስክንድር እዚህ ቦታ የመቆም እድል አግኝቶ ቢሆን ይሄን ሽልማት በተሰደዱ፣ በከፍተኛ ጫና ስር እየሰሩ ባሉና በታሰሩ ጋዜጠኞች ስም እንጂ ለግል ክብሩ አይቀበልም ነበር›› ብላለች።

‹‹ይህን ሽልማት በእስክንድር ቦታ ሆኜ የምቀበለው ሀሳብን የመግለፅ ነፃነትና የፕሬስ ነፃነት በኢትዮጵያ ዝቅተኛ በሆነበት ጊዜ ነው›› ያለችው ሠርካለም የአረቡ ዓለም አመፅ ከተቀጣጠለ በኋላ ፖሊስ ባሏን ማስፈራራት እንደጀመረ ገልፃለች። ‹‹በእንዲህ አይነት አደጋ ውስጥ እንደጋዜጠኛ ሆኖ መስራት አያስቸግር ነበር›› ብላለች።

ሠርካለም በዚህ ሳምንት መጨረሻ ከአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ቢሮ (State department) ባለስልጣናት ጋር እንደምትገናኝም ኒውዮርክ ታይምስ ዘግቧል።

ጋዜጠኛና የፖለቲካ ተንታኝ የሆነው እስክንድር ነጋ መንግስት በሽብርተኝነት ጠርጥሮት ከመስከረም 2004 ጀምሮ በቁጥጥር ስር ውሎ በቃሊቲ በእስር ላይ እንደሚገኝ ይታወቃል።

# ‹‹የኦሮሚያ ፍ/ቤቶች ከተፅዕኖ ሙሉ በሙሉ ነፃ ናቸው ማለት አይቻልም››

## /የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት አቶ ታደለ ነጊሾ/

የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በዝዋይና ወሊሶ ከተማዎች ከመጋቢት 19 እስከ መጋቢት 22 የዘጠኝ ወር የስራ ሪፖርት አቀረበ።

የኦሮሚያ ፍርድ ቤቶች በ19 ዞኖች ከፍተኛ ፍርድ ቤቶችና 269 የወረዳ ፍርድ ቤቶች ያሉት ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ ዘጠኙ ዞኖችና የኦሮሚያ ፍርድ ቤቶች፣ ሁለት ቅርንጫፎች፣ አዳማና ሻሸመኔ ፍ/ቤቶች የምስራቁ ክፍል በሚል በዝዋይ ከተማ ሪፖርት አቅርበዋል። የተቀሩት ደግሞ የምዕራቡ ክፍል በሚል በወሊሶ ከተማ ሪፖርት ማቅረባቸውን ለማወቅ ተችሏል።

የስብሰባው ዓላማ ባለፉት 9 ወራት ‹‹ፍ/ቤቱ ካቀደው ውስጥ ምን ያህሉ በጥሩ ጐን ተከናውኗል? ምን ያክሉስ ድክመት አሳይቷል?›› የሚለውን ለማወቅና ቀጣዩን አቅጣጫም ለመወሰን እንደሆነ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት አቶ ታደለ ነጊሾ ለፍትህ ገልፀዋል።

‹‹ከዳኞች ስነ-ምግባር ጋር በተያያዘ ከቀረቡ አቤቱታዎች 51 በመቶው እውነትም የዲሲፕሊን ችግር ተገኝቶ ዳኞች የተከሰሱበት፣ መልስ የሰጡበትና የተቀጡበት ሁኔታ አለ›› ያሉት ፕሬዚዳንቱ ‹‹የኦሮሚያ ፍ/ቤቶች ከተፅዕኖ ነፃ ናቸው ማለት ይቻላል?›› ተብለው ከፍትህ ጥያቄ ቀርቦላቸው ነበር። ‹‹ሙሉ በሙሉ ነፃ ናቸው ማለት አይቻልም። ከግለሰብ፣ ከባለሀብት እና ከመንግስት አካላት ተፅዕኖ ሊኖር ይችላል። ኦሮሚያ ላይ ብቻ አይደለም። ባደጉ አገሮችም የዳኝነት ነፃነት ሁሌም ቢሆን አደጋዎች ይጋረጡበታል። በኦሮሚያ ሁኔታ ግን እዚህና እዚያ በተለይ ደግሞ የታችኛው መዋቅር ላይ ከሚያጋጥመው በስተቀር ምንም ጫና የሌለበት ነው ማለት ይቻላል። ነፃ ሆነን እየሰራን ነው።›› ሲሉ መልሰዋል - ፕሬዚዳንቱ።

በኦሮሚያ በተለይም በቡራዩና ሰበታ አካባቢ ከመሬት ጉዳይ ጋር በተያያዘ በተወሰኑ የፍርድ ውሳኔዎች ላይ ያለውን ቅሬታ በተመለከተ ሲመልሱም፤ ‹‹የሰበታና የቡራዩውን ጉዳይ በቅርብ ስንከታተል ነበር። እናውቀዋለን፣ ነፃ የወጡት ሌላ ጫና ኖሮ ሳይሆን ማስረጃቸውና ክርክራቸው ነፃ እንዲወጡ ስላደረጋቸው ነው። የተቀጡትም የቀረበባቸው ማስረጃና ክርክር ሊያስቀጣቸው ስለሚችል ነው። እኛ እስከምናውቀው እዛ አካባቢ የተሻለ አፈፃፀም የተከናወነበትና ህብረተሰቡም ያረካበት ነው።›› ብለዋል።

# ፕሮፌሰር ገብሩ ታረቀ ከኃላፊነታቸው ተነሱ

በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም ዳይሬክተር የነበሩት ፕሮፌሰር ገብሩ ታረቀ ከኃላፊነታቸው መነሳታቸውን ምንጮቻችን ገለፁ። ተቋሙን ለአንድ ዓመት ያህል በዳይሬክተርነት የመሩት ፕ/ር ገብሩ ታረቀ ወርደው በቦታቸው ዶክተር አህመድ ሀሰን ተሹመዋል።

በጉዳዩ ላይ ሀሳባቸውን ለፍትህ ጋዜጣ የተናገሩት ፕ/ር ገብሩ፣ በቀደሞው የዩኒቨርስቲው ፕሬዝዳንት ፕ/ር እንድርያስ እሸቴ ከዓመት በፊት መሾማቸውን በማስታወስ ከኃላፊነታቸው የተነሱበትን ምክንያት ያልጠቆመ ደብዳቤ ሰኞ ወደ ቢሮ ሲገቡ ጠረጴዛቸው ላይ ተቀምጦ እንዳገኙት ተናግረዋል። በተለምዶ ተቋሙን ለመምራት የሚመረጡት ፕሬዚዳንቶች ለሦስት ዓመታት ያህል በኃላፊነታቸው ላይ እንደሚቆዩ የጠቀሱት ፕ/ር ገብሩ፣ ከትናንት በስቲያ ቢሯቸውን አስረክበው መውጣታቸውን በተለይ ለፍትህ ጋዜጣ ተናግረዋል።

ወደፊት ምን ለማድረግ አቅደዋል? ለሚለው የጋዜጣዋ ጥያቄም ከጥቂት የዕረፍት ጊዜ በኋላ ወደ ጥናት እና ምርምር ስራ እንደሚመለሱ ጠቁመዋል።

# ‹‹ሠማያዊ›› ፓርቲ ህጋዊ መሆኑን ይፋ አደረገ

በምስረታ ላይ የነበረው ‹‹ሠማያዊ›› ፓርቲ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ህጋዊ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ባይሰጠውም በአዋጅ ቁጥር 373/2000 መሰረት ህጋዊነቱ የተረጋገጠ ፓርቲ መሆኑን ሚያዚያ 24 ቀን 2004 ዓ.ም. በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ አስታወቀ።

‹‹የፖለቲካ ፓርቲዎችን የመመዝገብ ስልጣን ለኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ የሰጠው የተሻሻለው የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ አዋጅ፤ ቦርዱ የሚቀርቡለትን የምዝገባ ማመልከቻ በተቀበለ በ3 ወር ጊዜ የምዝገባውን ፎርማሊቲ አጠናቆ የህጋዊነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለአመልካቹ መስጠት እንዳለበት ይገልጻል። የምዝገባ ጥያቄ የሚያቀርብ ፓርቲም ሊያሟላው የሚገቡ ሰነዶችን ይዘረዝራል›› ይላል ፓርቲው ‹‹የኢትዮጵያ ምርጫ ቦርድ ለህግ ተገዢ ይሁን›› በሚል በሰጠው መግለጫ። መግለጫው አያይዞም ‹‹ቦርዱ በአዋጁ በተገለፀው መሰረት የምዝገባ ማመልከቻን በማስተናገድ በተገቢው ጊዜ መልስ ከመስጠት ይልቅ በግለሰቦ ፍላጐት እየተመራና በዘልማድ እየሰራ የአዋጁን ድንጋጌ ተፈፃሚ አላደረገም›› ሲል ፓርቲው ቦርዱን ወቅሷል።

የሰማያዊ ፓርቲ ሊቀመንበር አቶ ይልቃል ጌትነት ‹‹የተሻሻለው የፖለቲካ ፓርቲዎች አዋጅ መስራቾች የፈረሙበት ሰነድ ለህዝብ ይፋ ይሁን ቢልም መቼ፣ የት እና እንዴት ተፈፃሚ እንደሚሆን ግልጽ አይደለም። አዋጁን ለመፈፀምም የወጣ ደንብም ሆነ መመሪያ ባለመኖሩ ለአፈፃፀም የህግ አቅጣጫ የለውም። ስለዚህም ይህንን ለመተግበር በተንቀሳቀስንባቸው ቦታዎች በርካታ ችግሮች አጋጥመውናል። ይህንን አዋጅ የሚያስፈጽም ደንብና መመሪያ ሳይወጣ 4 አመት ሙሉ ሲሰራበት ቆይቷል። ለምን ደንብና መመሪያ እንዳልወጣ ግልጽ አይደለም›› ሲሉ ተናግረዋል።

ሊቀመንበሩ ለምን ወደ ፍርድ ቤት ጉዳያችሁን አልወሰዳችሁትም የሚል ከጋዜጠኞች ለቀረበላቸው ጥያቄ ሲመልሱ ‹‹ቦርዱ በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ ምላሽ ካልሰጠ የምዝገባ ማመልከቻ ያቀረበው የፖለቲካ ፓርቲ በዚህ ህግ መሰረት እንደተመዘገበ ይቆጠራል የሚለውን አዋጅ በመጠቀም ይፋ ማድረግን መርጠናል›› ሲሉ መልሰዋል።

# ‹‹ከአትላንቲክ ባሻገር›› ሰኞ ይመረቃል

በኢትዮውድ ኢንተርቴይመንት አቅራቢነት በደራሲና ዳይሬክተር ቅድስት ባየልኝ የተሰራው ‹‹ከአትላንቲክ ባሻገር›› የተሰኘው ፊልም ሰኞ ሚያዚያ 29 ቀን 2004 ዓ.ም. ከቀኑ 11:00 ሰዓት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቲያትር ይመረቃል።

ፊልሙ ሰሜን አሜሪካ ተሰርቶ የተጠናቀቀ ሲሆን ሰኞ ከ11:00 ሰዓት ጀምሮ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቲያትር በሚከናወን ልዩና ደማቅ የቀይ ምንጣፍ ስነ-ስርዓት ምርቃቱ እንደሚከናወን ተገልጿል።

# በመሀል ፒያሳ ራሱን ያቃጠለው ግለሰብ ሕይወቱ አለፈ

ባለፈው ሳምንት ማክሰኞ ዕለት ፒያሳ-ዳግማዊ ሚኒልክ አደባባይ በሚገኘው የስራ ማስታወቂያ በሚለጠፍበት ጉዳና አካባቢ ሰውነቱ ላይ ቤንዚን አርከፍክፎ ራሱን በማቃጠሉ ወዲያውኑ ለሕክምና የካቲት 12 ሆስፒታል ገብቶ የነበረው ዳዊት ለንዳሞ በሕክምና ሲረዳ ቆይቶ እሁድ ዕለት ሕይወቱ ማለፉ ታውቋል።

‹‹የፖሊስ አባል ነበረ›› የተባለው ዳዊት ለንዳሞ፣ ረቡዕ ዕለት ከድንገተኛ ክፍል ወደ ቃጠሎ ሕክምና መኝታ ኬዝ ቲም ተዘዋውሮ በሆስፒታሉ ሕክምና እየተከታተለ ነበር። ሆኖም ግለሰቡ የደረሰበት ቃጠሎ ጥልቀት ስለነበረው እሁድ እለት ከጠዋቱ 1:30 ሰዓት ገደማ ሕይወቱ እንዳለፈ የሕክምና ክፍሉ ኃላፊ ሲስተር ታደለች በቀለ ለፍትሕ አስረድተዋል።

ወደ ሆስፒታሉ ከገባ ጊዜ ጀምሮ ከጓደኞቹ በስተቀር ዘመዱ ነኝ ያለ ማንም ሰው እንዳልነበረ ያስታወሱት ኃላፊዋ ለቀናቶች የሕክምና ወጪውን የቻለለት ሆስፒታሉ መሆኑን ጨምረው ተናግረዋል።

በቃጠሎው ምክንያት ህይወቱ ያለፈው የዳዊት ለንዳሞ አስከሬን ወደ ዳግማዊ ሚኒሊክ ሆስፒታል መላኩን ሲስተር ታደለች ጨምረው ለፍትሕ ገልፀዋል።

ግለሰቡ በወቅቱ ራሱን ሲያቃጥል ‹‹የምበላው አጣሁ፣ ምን ልብላ?›› ሲል እንደነበረ በስፍራው የነበሩ የአይን እማኞች በወቅቱ በቦታው ደርሶ ለነበረው የፍትሕ ዘጋቢ መግለፃቸውን በመጥቀስ ባለፈው ሳምንት እትማችን ዜናውን ማስነበባችን ይታወሳል።

# ከሁመራ ከ50 በላይ ሰዎች በድጋሚ ታፍነው ተወሰዱ

## -አንድ ሰው ሞቷል

በምዕራብ ትግራይ ክልል በቃፍታ ሁመራት ወረዳ ተከዜ ወንዝ ዳርቻ ‹‹ከርቸሊት›› ከምትባል አካባቢ ከትናንት በስትያ ከ50 በላይ የአካባቢው ነዋሪዎች ታፍነው ወደ ኤርትራ መወሰዳቸውን፣ አንድ ሰው መሞቱንና አራት ሰዎች ከተያዙ በኃላ ማምለጣቸውን የአካባቢው ምንጮች ለፍትሕ ገለፁ።

በአካባቢው በባህላዊ መንገድ ወርቅ በማውጣት ስራ ላይ ተሰማርተው ከነበሩት በርካታ ሰዎች መካከል ከትናንት በስትያ ከጥዋቱ 4:00 ሰዓት ገደማ በግምት 58 የሚሆኑ ሰዎች ባልታወቁ የታጠቁ ኃይሎች ታፍነው ወደ ኤርትራ መወሰዳቸው ምንጮች ጨምረው ገልፀዋል።

በወቅቱም የተኩስ ልውውጥ እንደነበረ የጠቀሱት ምንጮቻችን፣ አቶ ገ/መድህን ተክላይና አቶ ገ/መድህን ገ/ኢየሱስ የተባሉ ግለሰቦች ከተያዙ በኃላ ሮጠው ማምለጥ እንደቻሉ ተናግረዋል። ፍትሕም አቶ ገ/መድህን ተክላይን በስልክ ለማነጋገር ችላ ነበር፡ ፡ እንደተባለው ከአፈናው ሮጠው ማምለጣቸውን የጠቀሱት አቶ ገ/መድህን በድርጊቱም አንድ የኤርትራ ተቃዋሚ ሃይልን በተጠርጣሪነት ጠቁመዋል።

መንግስት ስለጉዳይ ስላለው መረጃ ለመጠየቅ የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት ሚኒስትር ዲኤታ ወደሆኑት አቶ ሽመልስ ከማል ተንቀሳቃሽ ስልካቸው ላይ ብንደውልም ስልካቸው ስለማይነሳ የመንግስትን ምላሽ ማካተት አልቻልንም።

በተመሳሳይ ሁኔታ ሚያዚያ 13 ቀን 2004 ዓ.ም. በዚሁ አካባቢ ‹‹ሀገረ ሰላም›› በሚባል አዲስ ሰፈር ከ140 በላይ ነዋሪዎች ባልታወቁ የታጠቁ ሃይሎች ታፍነው ወደ ኤርትራ መወሰዳቸውን ሪፖርተር ጋዜጣ መዘገቡ ይታወሳል።

ከደቡብ ክልል ቤንች ማጂ ዞን ከጉራፈርዳ ወረዳ ‹‹አረን ዳገት›› ከሚባለው አካባቢ የተፈናቀሉ 47 አባወራዎች ሰኞ ሚያዚያ 21 ቀን 2004 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ለሰዓታት ካረፉ በኋላ ወደ ትውልድ አካባቢያቸው ደብረብርሃን መጓዛቸው ታወቀ።

ከስድስት ዓመታት በላይ መኖሪያቸውን በዞኑ ማድረጋቸውን የሚናገሩት ተፈናቃዮቹ በዞኑ በሌሎች አካባቢዎች ሲካሄድ የነበረው የማፈናቀል ተግባር ቀደም ባሉት ጊዜያት እንዳልነበረ ገልፀው፣ ነገር ግን ከሚያዚያ 11 ቀን 2004 ዓ.ም. ጀምሮ ‹‹ከዞኑ ጥላችሁ ውጡ›› ተብለው መገደዳቸውን ለፍትህ ገልጸዋል።

‹‹ለምን ብለን በመጠየቃችን ታስረን ተደብድበናል›› የሚሉት ተፈናቃዮቹ ‹‹ቤተሰቦቻችንን ወደከተማ በመሸሽግ እኛ እዛው ብንቆይም ከያለንበት በሦስት ቀናት ውስጥ ለቀን እንድንወጣና በአካባቢው ያፈራነውን ንብረት ለመሰብሰብ እንኳን ጊዜ ሳናገኝ እንድንባረር አስገድደውናል›› ብለዋል። የትውልድ አካባቢያቸው ሰሜን ሸዋ መሆኑን የሚናገሩት እነዚህ ተፈናቃዮች ወደ ደብረብርሃን በመሄድ የዞኑ አስተዳደሩ በሌላ ቦታ እንዲያሰፋራቸው ለመጠየቅ ከላይ በተጠቀሰው እለት ተጉዘዋል።

# ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ስለኢትዮጵያ ፖለቲካ ለማስተማር ወደ ጀርመን አቀኑ

የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ /አንድነት/ ፓርቲ ፕሬዚዳንት ስለኢትዮጵያ ፖለቲካ ለማስተማር ከትላንት በስቲያ ወደ ጀርመን መሄዳቸውን ምንጮች ለፍትህ ገለፁ። እንደ ፍትህ ምንጮች ዶ/ር ነጋሶ ወደ ጀርመን ፍራንክፈርት ከተማ የተጓዙት ስለኢትዮጵያ ፖለቲካ በተለይም ስለብሔር ፖለቲካ ለማስተማር ሲሆን ለሚቀጥሉት ሁለት ወራት ያህል እንዲያስተምሩ የጋበዛቸውን ዩኒቨርስቲ ስም ለማወቅ ያደረግነው ሙከራ አልተሳካም። እርሳቸው እስኪመለሱ ድረስ ፓርቲውን የተከበሩ አቶ ግራማ ሰይፉ ፓርቲውን በተጠባባቂ ፕሬዝዳትነት እንዲሚመሩ ለማወቅ ተችሏል።

# በኦሮሚያ መንጃ ፍቃዱ የሚያሽከረክሩ ፍቃዳችንን ተነጠቀ አሉ

በኦሮሚያ ክልል መንገድ ትራንስፖርት ባለስልጣን የማሽከርከር ብቃት ማረጋገጫ ተሰጥቷቸው የሚያሽከረክሩ ሹፌሮች በአማራ ክልል ትራንስፖርት ባለስልጣን በማሽከርከር ላይ እያለን መንጃ ፍቃዳችሁ ለምኔት አልሆነም በማለት ተነጥቀናል ሲሉ ለፍትህ ገልፀዋል።

አሽከርካሪዎች እንዳሉት በተለያዩ የአማራ ክልል ከተሞች በመንቀሳቀስ ላይ እያሉ መንጃ ፍቃዳቸው መቃማቱን ገልፀው መፍትሄ የሚሰጠን አካል አላገኘንም ሲሉ ገልፀዋል። ፍቃዳችንን ከተነጠቅን ከ3 ሳምንት በላይ በመሆኑ ሰርተን ቤተሰቦቻችንን ማስተዳደር እንዲሁም መኪኖቻችንን ማንቀሳቀስ አልቻልንም ሲሉ ጨምረው ገልፀዋ።

‹‹የኦሮሚያ ትራንስፖርት ቢሮ እስካአሁን እየሰጠ ያለው መንጃ ፍቃድ ህጋዊ ነው›› የሚሉት የቢሮ ህዝብ ግንኙነት ሃላፊ አቶ አለዩ ዑመር መንጃ ፍቃዳቹን ላምኔት ለማድረግ ማሽኖቹን በመግዛት ሂደት ላይ መጓተት በመፈጠሩ መሆኑን ገልፀው ማሽኖቹ በመገዛታቸው በቅርቡ ችግሩ መፍትሄ ያገኛል ብለዋል።

እርሳቸው እንደሚሉት እስካአሁን መንጃ ፍቃዱን የተቀማ ሰው መኖሩን እንደማያውቁ ገልፀው መንጃፍቃዳቸውን የተቀሙ ግለሰቦችን ህጋዊ መሆኑ ታውቀው ፍቃዱን የነጠቃቸው አካል መፍትሄ መስጠት አለበት ሲሉ ተናግረዋል።

# በስካይ ባስ አደጋ ላይ የፓናል ውይይት ይካሄዳል

ከአዲስ አበባ ወደ ጎንደር ጥር 8 ቀን 2004 ዓ.ም. በመጓዝ ላይ በነበረውና ንብረቱ የስካይ ባስ በሆነው የህዝብ ማመላለሻ አውቶቡስ ላይ በደረሰው አደጋ የተጎዱ ቤተሰቦች አስተባባሪ ኮሚቴ የፓናል ውይይት ሊያካሂድ መሆኑን ኮሚቴው ለፍትህ ገለፀ፡ ፡

ግንቦት 2 ቀን 2004 ዓ.ም. በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባህል ማዕከል በሚካሄደው ውይይት ላይ የሕግና የሰብዓዊ መብት ባለሙያዎች፣ ጋዜጠኞች እና ከአደጋው የተረፉ ተጎጂዎች እንደሚገኙ አዘጋጆቹ ገልጸዋል። በውይይቱ ላይም ለአደጋው ተጠያቂ ወገን ስለ መኖሩ? ስለ ተወሰደው እርምጃ? ከአደጋው ከተረፉት ሰዎች መካከል ስንቶቹ በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኙና ስለአደጋው ምን እንደሚሉ? የሚቀርብ ሲሆን ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ተነስተው ውይይት እንደሚደረግባቸው ለማወቅ ተችሏል።

# ‹‹የወሎ ደሴ›› ንግድ ትርኢትና ባዛር እንዲያዘጋጅ አምና ተመርጦ የነበረው ማህበር በደል እንደደረሰበት ገለፀ

ከግንቦት 20-28/2003 ዓ.ም. ድረስ ‹‹ወሎ ደሴ›› በሚል ስያሜ በደሴ ከተማ የንግድና ትርኢት እና ኤግዚቢሽን ባዛር እንዲያዘጋጅ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የንግድና ትራንስፖርት ቢሮ ፍቃድ አግኝቶ የነበረው ሲ ኤም ኤም ኤስ የሕብረት ስራ ማሕበር ‹‹ቢሮው ተገቢውን ነገር ነፍጐኛል፣›› በማለት ለሚመለከተው አካላት ያቀረበው አቤቱታ እስከአሁን መፍትሄ እንዳላገኘ ለፍትሕ ገለፀ።

ቢሮው በ15/6/2003 ዓ.ም. ለማህበሩ በፃፈው ደብዳቤ በደሴ ከተማ ዝግጅቱን እንዲያካሂድ ፍቃድ ቢሰጣቸውም በድጋሚ በ20/8/2003 ዓ.ም. ለማህበሩ በፃፈው ደብዳቤ የከተማው አስተዳደር ከንቲባ ጽ/ቤት በከተማው ሪፈራል ሆስፒታል ለማስገንባት በመታሰቡ ምክንያት የንግድ ትርኢትና ባዛር ለማዘጋጀት ጥያቄ ያቀረቡ ድርጅቶች ጥያቄያቸው ታግዶ ቢቆይም ለሲ ኤም ኤም ኤስ በመፈቀዱ በሌሎች ላይ ከፍተኛ ቅሬታ ማስነሳቱን ይገልፃል።

በመሆኑም ማህበሩ ከንግድ ትርኢትና ባዛር አላማዎች ውጪ እየተንቀሳቀሰ መሆኑንና የንግድ ትርኢትና ባዛር የሚዘጋጅበት ከተማ አስተዳደር እውቅና ባለመስጠቱ ሊያስከትል የሚችለውን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ቀውስ ከግምት ውስጥ በማስገባት የታሰበው ዝግጅት እንዳይካሄድ ከላይ በተጠቀሰው ቀን ቢሮው እግድ ጥሎ ነበር።

ነገር ግን ማህበሩ ስራውን ለሁለት ወር ከአምስት ቀን ያህል ከሰራ፣ የስራውን 90 በመቶ ካጠናቀቀና 380,000 ብር ወጪ ካወጣ በኋላ ዝግጅቱ መታገዱን ለፍትሕ የገለፁት የማህበሩ ሊቀመንበር የሆኑት አቶ ዘላለም ካሳው ናቸው።

# ‹‹ስለምን እርስ በርሳችሁ ትበዳደላላችሁ?›› ሐዋ.ሥራ ም.7 ቁ.26

እስራኤላውያን በግብፅ ምድር በባርነት ለበርካታ አመታት የስቃይ ኑሮን አሳለፉ:: ህፃናት በምድሪቱ እንዳያድጉ ወደ ውጭ ተጣሉ::ታላቁ የእስራኤል ነቢይ ሙሴም ከእነዚህ ህፃናት መካከል አንዱ ነበር::እግዚያብሔር ያለው ሆኖ ሙሴ የፈርኦን ልጅ አንስታ በንጉስ ቤት እንዲያድግ ሆነ:: ሙሴ ከሌሎቹ ወገኖቹ በተለየ እነዚህን ሁሉ ክብርና ሞገስ ቢያገኝም የዘመዶቹ ስቃይ በእጅጉ ያንገበግበው ነበርና በሁል ነገሩ ከግብፃውያን እና ከፈርኦን አገዛዝ ያፈነግጥ ጀመር:: ሙሴም እግዚያብሔር እንደፈቀደው ዜጎቹን ከባርነት ቀንበር ነፃ ለማውጣት ኃላፊነቱን ተረከበ:: ይህ ሁኔታም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ.7 ቁ.23-26 ላይ እንዲህ ተብሎ ተገልፆአል::

‹‹ነገር ግን አርባ አመት ሲሞላው ወንድሞቹን የእስራኤልን ልጆች ይጎበኝ ዘንድ በልቡ አሰበ:: አንዱም ሲበደል አይቶ ረዳው፣ የግብፅን ሰውም መትቶ ለተገፋው ተበቀለ:: ወንድሞቹም እግዚአብሔርን በእጁ መዳንን እንዲሰጣቸው የሚያስተውሉ ይመስለው ነበር:: እነርሱ ግን አላስተዋሉም:: በማግስቱም እርስ በርሳቸው ሲጣሉ አገኛቸው፤ሊያስታርቃቸውም ወደደ- ሰዎች ሆይ እናንተስ ወንድማማች ናችሁ ስለምን እርስ በርሳችሁ ትበዳደላላችሁ? አላቸው::››

እስከዛሬ ድረስ የመጣንባቸውን የታሪክ እውነቶች ወደኋላ መለስ ብለን ካየን አሁን ያለንበትን ጊዜ ለመረዳት አዳጋች አይሆንብንም:: በተለያዩ ጊዜያት ብሔራዊ በዓላትን በጋራ ዘክረናል:: እንደተለመደው ነገም የአርበኞች በዓል እናከብራለን:: ይህንን በዓል ስንዘክር አስቀድሞ ወደ ህሊናችን የሚመጣው ጣልያኖች ለአጭር ጊዜም ቢሆን በቅኝ ግዛት ባርነት የገዙንን ወቅት ነው:: ባርነት ምን ያህል አስከፊ እንደነበር በጨረፍታም ቢሆን ተቋድሰናል:: ህፃናት፣ እናቶች፣ አዛውንት ባዶ ቤት እየተቆለፈባቸው በእሳት ነደዋል:: ወጣቶች ለዛሬ ነፃነታችን ብዙ መስዋእት በመክፈል በዱር በገደሉ ተዋድቀዋል:: የሃይማኖት አባቶች ይህቺ አገር ከነሙሉ ክብሯ ትቆይ ዘንድ ለእውነት ስለእውነት ብለው በጥይት ተደብድበዋል:: ምንም እንኳን በጊዜው ለጨቋኙ ፋሽስት ገዢ አጋዥ የነበሩ ባንዳዎች ቢኖሩም አብዛኛው ህዝብ ግን ብሔርን፣ ቋንቋን፣ ኃይማኖትን፣ ፆታን.......ሳይለይ ለኢትዮጵያ ነፃነት በእኩልነት ተዋድቋል:: በግብፅ ምድር እስራኤላውያን ባሪያ የሆኑትን ያህል እኛ ደግሞ በገዛ አገራችን እና መሬታችን ላይ ባሪያ ሁነን ኖረናል:: እስራኤላውያን ያንን ግፍና መከራ በእግዚአብሔር ቸርነት፤በሙሴ መሪነት ተሻግረውታል:: የአምስት አመቱን የመከራ ታሪክ እኛም በእግዚአብሔር ቸርነት፣ በአርበኞቻችን ፅኑ ተጋድሎ አልፈነዋል::

እስራኤላውያንየመጀመሪያውንየባርነት ምዕራፍ ሲሻገሩ እርስ በርሳቸው ማጉረምረም ጀመሩ:: አስቀድሞ በግብፅ ምድር የደረሰባቸውን ግፍና መከራ ረሱ:: እግዚአብሔር ያደረገላቸውን ተአምር ማስተዋል ተሳናቸው:: እርስ በርሳቸው በመካከላቸው ስምምነት ጠፋ::ማስተዋል ከእነርሱ ራቀች:: ቀድሞ የነበረው የባርነት ህይወት ናፈቃቸው:: አስቀድሞ በመከራ ጊዜ አንድ ያደረጋቸውን የወንድማማችነት ህብረት ፈፅሞ ጠሉት:: አንዱ ሌላውን በአይነ ቁራኛ ይመለከተው ገባ:: መፅሐፉም እንዲህ ይላል:: ‹‹እነርሱ ግን አላስተዋሉም››

የእኛም እውነት ይኸው ነው::የአሁኑ ታሪካችን ወደ ኋላ ያለፍንባቸውን የፖለቲካ አገዛዝ ውጣ ውረዶች ዞር ብለን ለማየት ወኔውን አሳጥቶናል:: በታሪክ አንድነት ላይ ተመስርቶ የቆየልንን የአገር አንድነት አንስተን ለመወያየት፣ ለመከራከር በእጅጉ እንፈራለን፣ አብሮን የኖረ የአንድነት ታሪክ ሁሉ ያለን እስከማይመስለን ድረስ::

በታሪክ አባቶቻችን የውጭ ወራሪ ኃይሎች ለመደምሰስ የተሳተፉባቸውን ገድላት ሳይቀር ይባስ ብለን እኔን ይመለከተኛል በሚሉ እና አይ እኔን አይመለከቱኝም በሚሉ ቡድኖች መካከል ተወጥረን ተይዘናል:: የዘመናት የጋራ ታሪክ ያላት አገር ህዝቦች ሳይሆን ለመለያየት ዝግጅት የምታደርግ አገር ውስጥ ያለን እየሆንን መጥተናል:: የተሻገርናቸውን ተከታታይ የመከራ ጊዜያት፣ አብረን የተጓዝናቸው የስቃይ አመታት፣ የተራብናቸውን፣ የተጠማንባቸውን እነዛ ክፉ ዘመናት ዘንግተናቸዋል:: ከእስራኤላውያን ማስተዋል ጠፋ እንዳለው ሁሉ ከእኛም ዘንድ ይህ መንፈስ እርቆናል:: የሚያስተውል መሪ አጣን:: የሚያስታርቅ ፣ተቻችሎ እና አቻችሎ የማለፍን ስብዕና የሚያስተምሩ ግለሰቦች ከአደባባይ ከራቁን ብዙ ዘመናት አለፈን:: ይህንን አደርጋለሁ ብሎ የሚነሳ ቡድን ካለም አናት አናቱን ብሎ ለማስቀረት በምናደርገው ጥረት ወደር ያሌለን ሆነናል:: የሙሴም ተሞክሮ ይኸው እንደነበር መጽሐፉ ይነግረናል:: ሙሴ የኤርትራን ባህር ካሻገራቸው በኋላ የተፈጠረውን አለመግባባት ለማስታረቅ ብሎ ብዙ ነገሮችን ለማድረግ ጣረ:: እንዲህም ሆነ ይለናል መጽሐፉ:: ‹‹በማግስቱም እርስ በርሳቸው ሲጣሉ አገኛቸው:: ሊያስታርቃቸውም ወዶ-ሰዎች ሆይ እናንተስ ወንድማማች ናችሁ፣ ስለምን እርስ በርሳችሁ ትበዳደላላችሁ? አላቸው:: ያም ባልንጀራውን የሚበድል ግን-አንተን በእኛ ላይ ሹምና ፈራጅ እንድትሆን የሾመህ ማን ነው? ወይስ ትናንትና የግብፁን ሰው እንደ ገደልኸው ልትገድለኝ ትወዳለህን? ብሎ ገፋው:: ሙሴም ከዚህ ነገር የተነሳ ሸሽቶ በምርያም አገር መፃተኛ ሆኖ ኖረ :: በዚያም ሁለት ልጆች ወለደ››


በአገራችን ሽማግሌዎች የሚፈለጉት የታሰሩ ሰዎችን ማስፈታት ለሚል የፖለቲካ ድርድር ጨዋታ ማጣፈጫ ሲሆን ብቻ ነው:: ሁላችንም ኢትዮጵያውያን ነን ብለን እስከተቀበልን ድረስ ወደድንም ጠላንም ወንድማማቾች መሆናችንን መዘንጋት የለብንም:: በአንድ ብሔር መገፋት ሂደት ውስጥ መታሰብ ያለበት በጥቅሉ የተገፋው ብሔር ሳይሆን ከጥቅል ማእቀፍ ውጭ ያለው ግለሰቡ ነው:: የአሁኑ ፖለቲካ ስርዓት ከዚህ ቀደም የገነባናቸውን የጋራ እሴቶቻችን እጥፍቶብናል:: ፖለቲካው ከግለሰብ መብት ይልቅ የቡድን መብት ላይ በማተኮሩ የተነሳ ‹‹ሰው ተበደለ›› የሚለው ግንዛቤ ከአእምሮአችን ፈፅሞ እየጠፋ መጥቷል:: ይህ አልበቃ ብሎም የአንድ ብሔር አባላት የሚደርስባቸውን መድሎ እና መገለል የተገፋው የራሱ ብሔር ይወጣው ከማለት ውጭ የአገሬ፣ የእኔ ጉዳይ ነው ማለትን ትተናል:: አስቀድሞ ከደረሰብን መከራ የባሰ ሌላ መከራን እየናፈቅን እንገኛለን:: አንዱ ባንዱ ላይ ሲጨክን ‹‹ለምን እርስ በርሳችሁ ትበዳደላላችሁ›› የሚል ጎበዝ የለንም:: ቢኖርም ማንነቱን እና ምንነቱን ብቻ አይቶ ምን አገባህ ከማለት ውጭ ግለሰቡ የያዘውን ፍሬ ሀሳብ ለመቀበል ዝግጁ አይደለንም::በዚህ ምክንያት ብዙ ያፈራናቸው ምሁራን፣ ታዋቂ ግለሰቦች ለሌላ ባዕድ አገር መጠቀሚያ እየሆኑ መጥተዋል:: አገራችን የገፋቻቸው ታላላቅ ወንድሞቻችንን በብሔር መከፋፈል ምክንያት አጥተናቸዋል:: ተስማሙ፣ ታረቁ፣ በደል ይቅር ለሚሉን አስታራቂዎች ‹‹በእኛ ላይ ሹምና ፈራጅ እንድትሆኑ የሾማችሁ ማን ነው?›› እያልናቸው ነው::

በቅርቡ በተለያዩ አካባቢዎች እየተከሰተ ያለው የዜጎች መፈናቀል አሳሳቢ ደረጃ ላይ እየደረሰ ይገኛል:: በኢትዮጵያ አገራችን ላይ እየተዧዧርን ንብረት የማፍራት መብታችን ጥያቄ ምልክት ውስጥ እየገባ ይገኛል:: እንደ በፊቱ የአገሬ ልጅ፣ ከመባባል ይልቅ የብሔሬ፣ የክልሌ ልጅ ወደ መባባል ዝቅታ ወርደናል:: የኢትዮጵያዊነት ማንነት በክልል ማንነት ተለውጧል:: ከመቀራረብ ይልቅ መለያየታችን ሰፍቷል:: በደል የደረሰባቸውን ግለሰቦች እሮሮ ለመስማት እንኳን የፈጠነ ጆሮ የለንም:: አገሪቷ ወዴት እያመራች ነው? የሚለውን ጥያቄ ደፍረን በአደባባይ ለመነጋገር ወኔውን አጥተናል ታዲያ አባቶቻችን የከፈሉት መስዋት ዋጋው ስንት ነው?

ወንድሞች ቀን ተቀን እየደረሰ ባለው የኑሮ ውድነት ሳቢያ መተኪያ አልባ የሆነች ነፍሳቸውን በእሳት በማጋየት እየቀጠፉት ይገኛሉ:: ለምን ይህ ሆነ? ችግሩን ለመፍታት ምን ማድረግ ይገባናል? ብለን ለመወያየት ይቅርና ወሬውን እንኳ ለመስማት የተዘጋጀን አይደለንም:: እየሆነ ያለውን እኛም አላስተዋልንም:: እግዚአብሄር አምላክ አስተዋይ ልቦና ይስጠን:: አሜን ይስጠን::


## አስደናቂው የፋር ኢንፍራሪድ ጀርመንየም እና ማግኔቲክ ቴራፒ

እንደ ብራስሌት እጅ ላይ በማሰር በሽታን ማዳን እንዲሁም መከላከል ይቻላል




ለአርትራይተስ እና ቁርጥማት
ለጀርባ ህመም ለትከሻ ህመም
ለከባድ ራስምታት ለመተንፈሻ ችግሮች
ለሳልና ለአስም ለሪህ ለማቃጠል ስሜት
ከእንቅልፍ ጋር ለተያያዙ ችግሮች
እና ለሌሎችም በርከታ የጤና ችግሮች መፍትሔ ይሰጣል

HARNESS

ይደውሉልን
0910 035578, 0911 19 62 51
P.O.Box 26982 code 1000 Addis Ababa



## መኪና ገዥና ሻጭ እናገናኛለን

